ስንታገል ዝም ብሎ አያየንም:: ይልቁንም፣ በእኛ ውስጥ እንዲኖርና እንዲሰውጠን መንፈስ ቅድስን ይሰጠናል:: በሕይወታችን ባለው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፣ ኃጢአትን ድል እናደርጋለን:: መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በተመለከተ ያስንን አመስካከት በመሰወጥ፣ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደሚገዳ እንድንረዳ ያደርጋል:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንድንችል መስጠታችንን ይሰውጠዋል:: መንፈስ ቅዱስ በአንድ ወቅት ተቆጣጥሮን የነበረውን ኃጢአት ማሸነፍ የምንችልበትን ኃይል ይሰጠናል:: ኢየሱስን ስመታዘዝ በሙሉ ኃይላችን የመጠቀም ኃላፊነት ቢኖርብንም፣ ኃጢአትን ድል እንድናደርግና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የሚረዳን እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልንረዳ ይገባል:: እግዚአብሔር ነው ኢየሱስን እንመስል ዘንድ ልማዳችንና ፀባያችን እንዲለወጥ የሚረዳን:: ስመስወጥ የሚያስችል ኃይል በሚሰጥን በአግዚአብሔር እንጂ በራሳችን ችሎታ ልንተማመን አይገባም (ፊልጵ. 2:12-13)::

**3. ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መከተልና የሚለውን መታዘዝ ማለት ነው::** ኢየሱስ ጴጥሮስን «ተከተስኝ» ሲሰው፣ ጴጥሮስ ወዲያውኑ ነው የተከተሰው:: ስሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ጴጥሮስ ኢየሱስን እየተከተለ የኢየሱስ ተከታይ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ እየተማረ ቆየ:: ምንም እንኳን ኢየሱስ ጴጥሮስን በአካል ተገኝቶ እንዳስተማረው እኛን ባያስተምረንም፣ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝት ያስተምረናል:: እናም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆን ካሰብንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግ ካሰብን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ልናነብና ኢየሱስ ምን እንድናደርግለት እንደሚፈልግ ልንጠይቀው ይገባል:: ኢየሱስ የምትወዱኝ ከሆነ፣ ትእዛዜን ጠብቁ (ዮሐ. 14:23-24) ብሏል:: ኢየሱስ በእርሱ እንድናምን ብቻ አይደለም የሚጠይቀን፣ እንድንከተሰውም ጭምር ነው:: እርሱን የምንከተለው እርሱን ወደ መምሰል ስንሰወጥ ነው::



የምናስብበትን መንገድ እንለውጣለን:: የምንሠራበትንም መንገድ እንሰውጣለን::

ኢየሱስን መከተል ቀላል አይደለም:: ኢየሱስ ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር ዕለት ዕለት «መስቀሉን «ተሸክሞ ይከተለኝ» ብሏል:: (ሉቃ. 9:2፤ 314:27):: መስቀሉን መሸከም ማለት ስራሳችን ፍላጐትና ለራሳችን ደስታ መሞት ነው:: አሁን የምንኖረው የኢየሱስን ፍላጎት ስመፈጸም ነው (ገላ. 2:20):: ያ ማለት ኢየሱስን በመከተላችን የሚመጣውን ሥቃይ መቻል ነው:: ይህ ሥቃይ የሚመጣው ኢየሱስን የማይከተሉ ወዳጆቻችንና ቤተሰቦቻችን ሲያገልሉን ሊሆን ይችላል:: ወይም ራሳቸውን ለኢየሱስ አስገዝተው ከማይኖሩ ሌሎች ክርስቲያኖች ሊሆንም ይችላል:: ስደት ሊያመጣብን ወይም የሌሎች መቀለጃ ሊያደርገን ይችላል:: የኢየሱስ ተከታይ ማለት ዓለም አስፈላጊ ነው ብላ የምትመስከተውን ክብር ባያመጣልንም እንኳ፣ ኢየሱስ የሚፈልገውን ማድረግ ነው:: ትምህርት፣ ሐብት ወይም ዓለማዊ ክብር የመሳሰሉትንና ዓለም አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ነገሮች ላያመጣልን ይችላል::

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሉቃ. 9:23 እና 14 27ን በቃልህ አጥና:: ለ) ለራስህ ሞተሃል? መስቀልህን ተሸክመሃል? ኢየሱስን መተከል በአኗኗርህና በሕይወትህ ዓላማ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ሐ) ስለ ሕይወትህ ስማሰብ አሁኑኑ ጊዜ ውሰድ። ኢየሱስ ስሕይወትህ ያለውን ዓላማ እንዲያሳይህ ጸልይ:: እርሱን ስመከተልና ስመታዘዝ ፈቃደኛ ነህን? |

**4. የኢየሱስ ደቀ መዝሙር እንደ መሆናችን መጠን፣ ሕይወታችን ሁሉ ይለወጣል::** ጳውሎስ አንድ ጊዜ ኢየሱስን ካመንን አዲስ ፍጥረት እንደምንሆን ይናገራል (2ኛ ቆሮ. 5:17):: ሁሉ ነገር ይሰወጣል:: ኢየሱስ አስፈላጊ ናቸው ስለሚላቸው ነገሮች ማሰብ እንድንጀምር አስተሳሰባችን መቀየር አለበት:: እግዚአብሔር የሚፈልገውን ማድረግ እንሻለን:: ጳውሎስ በሮሜ 12:2 ላይ ይህንን ዓለም እንዳንመስልና በአእምሮአችን መታደስ

እንድንለወጥ ያሳስበናል:: ተግባራችን መለወጥ አለበት:: ኢየሱስን የማያስከብሩ ነገሮችን በሙሉ «እናወልቃለን»:: እግዚአብሔር በእኛ የሚፈልገውን ባሕሪና ተግባር «እንለብሳለን» (ቆላ. 3:5-14):: መንፈስ ቅዱስ በእኛ ሲሠራና ሲለውጠን፣ አዲስ የአስተሳሰብ መንዶችን እያዳበርን እንመጣለን፣ ያም ወደ አዲስ ልማድ ይመራናል:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላም አዳዲሶቹ ልማዶች የባሕርያችን ክፍል ይሆናሉ:: ባሕሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል ሲለወጥ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንበስላለን:: በእግዚአብሔር ቤት፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ብቁ መንፈሳዊ መሪ መሆን የምንችለው በተለወጠው ባሕሪያችን ነው::

| |
|---|
| 22ኛ ጥያቄ:- ሀ) በኢየሱስ ለማመን የግል ውሳኔ አድርገሃል? ካላደረግህ፣ ኃጢአትህን ለኢየሱስ ለመናዘዝና ያንጻህ ዘንድ ለመለመን ጊዜ ውሰድ:: ለ) መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ እንዲሠራና ሕይወትህን እንዲለውጥ ትፈቅዳለህ? አማኝ ከሆንክበት ጊዜ ጀምሮ በአስተሳሰብህና በተግባርህ ኢየሱስን ወደ መምሰል የተለወጥክባቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) ኢየሱስ በሕይወትህ እንዴት ጌታ እንደ ሆነ ግለጥ:: ኢየሱስ ይቆጣጠረው ዘንድ ያልሰጠኸው የሕይወትህ ክፍል ምንድን ነው? አሁኑኑ በጸሎት ያልተሰጠህበትን የሕይወትህን ክፍል ለጌታ አስረክብ:: |

## ሦስተኛ ቀን:- አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚበስለው እንዴት ነው (ክፍል 2)

በትላንትናው ዕለት የቤተ ክርስቲያን አመራር መንፈሳዊ አገልግሎትና መንፈሳዊ ድርጅት በመሆኑ መንፈሳዊ ሰዎች እንደሚፈልግ ተመልክተናል:: እምነታችንንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እስካላደረግን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ልንመራ አንችልም:: ኢየሱስን ለመከተልና ትምህርቶቹን ለመቀበል የምናደርገው ውሳኔ ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት የምናደርገው ጉዞ ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስናድግ ለመሪነት ብቁ እንሆናለን::

ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከመብሰላችንና በቤተ



ክርስቲያን ሳለው አመራር ከመብቃታችን በፊት በሕይወታችን ውስጥ ማድረግ የሚገቡን ነገሮች አሉ::

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- መዝ. 63:1-5ን አንብብ:: ሀ) የዳዊት የልብ መሻት ምን ነበር? ለ) ይህ በሕይወትህ እንዴት እንደ ታየ አብራራ:: |

**1.** ለረጅም ጊዜ ያክል ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ካለን በመንፈሳዊ ብስለት እናድጋለን:: እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ታላላቅ አገልጋዮች በሙሉ እግዚአብሔርን ለማወቅ በጣም በጠለቀ መንገድ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ጥማት እንደ ነበራቸው መረጃዎች አሉ:: የእግዚአብሔር ቃል፣ አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ታላላቅ ነገሮችን ያደርጋሉ ይላል (ዳን. 11:32):: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ አገልጋዮች በሙሉ እግዚአብሔርን ለማወቅና ከእርሱ ጋር ጥልቅ የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ቅድሚያ ይሰጡ ነበር:: [ለምሳሌ፣ ሙሴ (ዘጸአ. 33:15-23)፣ ዳዊት (መዝ. 63:1)፣ ጳውሎስ (ፊልጵ. 3:4-14)::] የቤተ ክርስቲያን አመራር የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን ኢየሱስን መከተል ነው:: መሪዎች ስንሆን እይደለም የእርሱን ድምፅ የምንሰማውና የምንከተለው:: ይልቁንም፣ መሪዎች ከመሆናችን በፊት ነው ኢየሱስን መስማትና መከተል ያለብን:: ኢየሱስ በጐቼ ድምፄን ይሰማሉ ይከተሉኛማል ብሏል:: (ዮሐ. 10:4-5) አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ማወቁ በቂ አይደለም፣ እግዚአብሔርን ማወቅ አለበት:: እግዚአብሔር ልዩ ኃይልና የአመራር ችሎታን የሚሰጠው እርሱን በሚገባ ለሚያውቁት ነው:: በአመራር ውስጥ በሚከሰቱ አስከፊ ነገሮች ውስጥ የማይማረሩትና የማያቆሙት እግዚአብሔርን ጠንቅቀው የሚያውቁት ናቸው:: «መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሂድ» (ኢሳ. 20:21) የምትለዋን ቃል የሚሰሙት እግዚአብሔርን ጠንቅቀው የሚያውቁት ናቸው:: እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ፣ ምን እንደሚያስደስተው፣ እውነትና ውሸቱን መለየት የሚችሉት፣ የሐሰት ትምህርትን የሚቋቋሙት ወይም መጠኑን ያልጠበቀ

ትምህርት መሆኑን የሚያውቁት እግዚአብሔርን የሚያውቁት ብቻ ናቸው:: ብርሃን ጨለማን እንደሚያሸንፍ፣ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን የሚጓዙት ሁሉ ኃጢአተኝነታቸውን፣ የተሳሳተ ልማድና ባሕሪያቸውንና ክፉ ተግባራቸውን ይለውጣሉ (1ኛ ዮሐ. 1:5-7)::

> 24ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ለአንተ የቅርብ ወዳጅህ ነው ወይስ ጠንረ ልውጥ ነው? ለምሳሌ:- አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ወዳጅ (ኢሳ. 41:8)፤ ዳዊት (1ኛ ነገሥ. 15:3)]:: ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን የቀረበ ግንኙነት ለመጠበቅ ምን ታደርጋለህ?

2. መንፈሳዊ ብስለት የሚመጣው መንፈሳዊ ሥርዓቶች በሕይወታችን ውስጥ አስከፊ ሲሆኑ ነው:: መንፈሳዊ ሥርዓቶች በመንፈሳዊ ብስለት እንድናድግ፣ ትኩረታችንን በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆንና የእግዚአብሔርን ቃል እውነትና ኃይልን ከእግዚአብሔር የምንቀበልበት መንፈሳዊ ልማዶች ናቸው:: እነዚህ መንፈሳዊ ሥርዓቶች እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ እንድናውቀው ይረዱናል:: ይህ ልንለውጣቸው የሚገባንን መጥፎ ልማዶችና ባሕሪዎች መመልከት ያስችለናል:: በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንድንራመድም ይረዱናል:: እነዚህን መንፈሳዊ ሥርዓቶች መደበኛ ልማዳችን እስካላደረግን ድረስ ለእግዚአብሔር ክብር የምንመራ መሪዎች መሆን አንችልም::

የትኛዎቹንም መንፈሳዊ ሥርዓቶች በተፈጥሮአችን እናገኛቸውም:: ከመራመድ ይልቅ በውሻ ላይ እንዳለች ቁንጫ ከቦታ ቦታ መወሰዱ ቀላል ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የመወሰድና በመንፈሳዊ ሕይወት ለመቆየት የሚበቃውን ያክል ብቻ ማድረግ ለዕድገታችን በቂ አይደለም:: በየእሑዱ ቤተ ክርስቲያን እንሄድና አልፎ አልፎ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም እንካፈል ይሆናል፣ ነገር ግን እውነተኛ የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን ያ በቂ አይደለም:: የትኛውም ሰው በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ወደ መንፈሳዊ ብስለት አይመጣም:: መንፈሳዊ ዕድገት «ራስን የመግዛት» ባሕሪ



የሚያስፈልገው ጠንካራ ሥራ ነው:: በ1ኛ ጢሞ. 3:2 ላይ የቤተ ክርስቲያን መሪ «ራሱን የሚገዛ» መሆን እንዳለበት ተነግሮናል:: ራሱን መቆጣጠር የሚችል ሰው ብቻ ነው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ ሲል ሥጋው የሚፈልገውን ነገር የሚያደርገው:: (ለምሳሌ:- ለመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ሲል የጠዋት እንቅልፉን ይተዋል::) በዛሬው ዕለትና በሚቀጥለው ሳምንት የምንዘረዝራቸው መንፈሳዊ ሥርዓቶች እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ለማወቅና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመበሰል ስንል በተፈጥሮአችን ማድረግ የምንፈልጋቸውን ነገሮች አለማድረግን ያጠቃልላሉ::

> 25ኛ ጥያቄ:- ሀ) በመንፈሳዊ ሕይወትህ ለማደግ የሚረዳህን ነገር ለማድረግ ስትል ራስህን የተማርካቸውን ራስን የመቆጣጠርና ማድረግ የምትፈልገውን ነገር ላለማድረግ የሚያስችሉ ነገሮችን ዘርዝር:: ለ) ይህ ራስን የመቆጣጠር ባሕሪ የአውነተኛ ለውጥና መንፈሳዊነት መሠረት እንደ ሆነ ግለጥ::

ቁልፍ የሚባሉ መንፈሳዊ ሥርዓቶች ምንድን ናቸው? (*<u>ማስታወሻ</u>:- በዚህ የት.መ.ማ መጽሐፍ ውስጥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ የሚያስችሉ ቁልፍ ነገሮችን ብቻ ነው የምናስተዋውቅህ:: ከሌሎች መጽሐፎች ላይ ውጤታማ ጸሎት እንዴት ማድረግ እንደሚቻል፣ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እንደሚጠና የመሳሰሉትን ነገሮች ማጥናት ያስፈልጋል::)

## ሀ. የጸሎት ሰዎች መሆን አለብን::

> 26ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዘጸአ. 17:10-13ን አንብብ:: ሙሴ እጁን ለጸሎት ሲያነሣ ምን ተፈጠረ? እጁን ሲያወርድስ ምን ተፈጠረ? ሐ) ነህ. 1:4፣ 2:4፣ 4:9፣ 6:9ን ተመልከት:: ነህምያ ከችግሩ በፊትና በኋላ ምን አደረገ?

በዓለም ላይ የመጨረሻ ኃያል የሆነ ሰው ልጅ ነህ እንበል:: እናም አባትህ በፈለግህበት ሰዓት፣ ችግር ሲኖርብህ ወይም ልታነጋግረው ብትፈልግ እርሱን ገብተህ ማየት እንድትችል

ይፈቅድልሃል:: እርሱ በሰብሰባ መሐል እንኳን ቢሆን፣ ለብሰባውን አቋርጦ አንተን እንደሚሰማ ቃል ይገባል:: እንዴት አስገራሚ መብት ነው! ያለውን ሥልጣንና ኃይል ተጠቅሞ የአንተን ችግር መፍታት እንዴት ይቀላል:: ይታይህ የእርሱ ታላቅ ጥበብ ሕይወትን ለመረዳት እንዴት ሊረዳህ እንደሚችል!

የእጽናፈ - ዓለማት ሁሉ ገዢ የሆነው የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ይህ አስደናቂ መብት አለን:: የእርሱን ትኩረትና እርዳታ በማንኛውም ሰዓት እንደምናገኝ በመረዳት በድፍረት በለማያዩው ዙፋኑ ሥር መውደቅ እንችላለን (ዕብ. 4:14-16):: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ራሱ ይሰብክና ያስተምር እንደ ነበረው መስበክና ማስተማርን እንዲያስተምራቸው ፈጽሞ አልጠየቁም:: ነገር ግን የኢየሱስ አገልግሎት ኃይል የተገኘው በጸሎት እንደ ሆነ ስለ ተገነዘቡ እንዴት እንደሚጸልዩ እንዲያስተምራቸው ኢየሱስን ጠይቀውታል:: ስለ ጸሎት ያልተገለጡልን በርካታ ነገሮች አሉ:: ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ለጸሎታችን «እዎንታን» አንዳንድ ጊዜ ደግሞ «ቆይ» ሌላ ጊዜ ደግሞ «አይሆንም» የሚል ምላሽን ለምን እንደምናገኝ አናውቅም:: ነገር ግን ጸሎትን በተመለከተ በርካታ ግራ አጋቢ ነገሮች ስላሉ፣ የሚከተሉትን እውነቶች ልናስታውስ ይገባል::

1) ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ብስለታችንን ለማሳደግ በጋራ ይሠራሉ:: ውጤታማ መሪዎች እንሆን ዘንድ ሁለቱንም አመጣጥነን መጓዝ አለብን:: በቃሉ ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት መጸለይ እንዳለብን የእግዚአብሔርን ቃል እንማራለን:: ለንጸልይ በእምነት የምንጠይቀውን እንደምናገኝ የተገባልን ቃል አለ:: ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዴት መጸለይ እንደሚቻል የሚያሳዩን የበርካታ ቅዱሳን ምሳሌ ተቀምጦልናል:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቃድ ብቻ ብናነብ ነገር ግን ባንጸልይ እውነቱን ልናውቅ እንችል ይሆናል እንጂ፣ ልዩነት ማምጣት



የምንችልበት ኃይል አይኖረንም:: በሌላ በኩል፣ ሁልጊዜ የምንጸልይ ከሆንና፣ የእግዚአብሔርን ቃል የማናነብ ከሆነ በቀናኢነት ብንሞላም እውቀት አይኖረንም (ሮሜ 10:2):: ለእኛና ለሌሎች ሰዎች ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካላወቅን፣ የምንጸልየው እንደ እግዚአብሔር መሻት ይሁን ወይም አይሁን የምናውቀው ነገር አይኖርም:: ስለዚህም ጸሎቶቻችን ኃይል-አልባ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ስለሚሆኑ፣ ያለንበትን ሁኔታ ሊለውጡ አይችሉም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እውቀታችንን (ኢያሱ 1:8) ሳያቋርጡ ከመጸለይ ጋር (1ኛ ተሰ. 5:17) ልናመጣጥን ይገባል::

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አብዛኛውን ጊዜህን የምታጠፋው በመጸለይ ነው ወይስ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ነው? ለ) እነዚህን ሁለት መንፈሳዊ ሥርዓቶችን በሕይወትህ ማመጣጠንን በተመለከተ ይህ ምንድን ነው የሚያስተምርህ?

2) ከጸሎት የምናገኘው እጅግ አስፈላጊ ውጤት ፈጣሪና የሰማየ ሰማያት ጌታ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ያስተካክልልናል:: ሁላችንም ልንኩራ፣ እጅግ አስፈላጊ ሰው እንደ ሆንን ልናስብና ያሉብንን ችግሮች በሙሉ መፍታት እንደምንችል ልናስብ እንችላለን:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ይቃወማል ይለናል (1ኛ ጴጥ. 5:5-6):: እግዚአብሔር፣ እርሱን ሊጠይቁት· የሚገባቸው ብዙ የሚጐድሏቸው ነገሮች እያሉ ራሱን ወይም ራሷን እንደ ቻለች የሚያስብ ሰውና የምታስብን ቤተ ክርስቲያን ይቃወማል (ራእይ 3:17-18):: ነገር ግን በምንጸልይበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መደገፍ እናሳያለን:: እርሱ ለሚያስፈልገን ነገር መፍትሔ ነው:: የእኛ ጥንካሬ የሚመጣው ከእርሱ ነው:: ስለ አገልግሎታችን ስንጸልይ በእኛ ላይ እንድትሠራ በእንተ ላይ እንደገፋለን ማለታችን ነው:: ጳውሎስ እንደ ተማረው፣ እግዚአብሔር በእኛ የሚበረታው እኛ ስንደክም ነው (2ኛ ቆሮ.

12:7-10)፡፡ ጸሎት እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለንን መደገፍ የሚጠብቅበት ዋና መሣሪያ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ለአባቱ በመጸለይና በአባቱ ላይ በመደገፍ ብዙ ሰዓቶችን በጸሎት ያጠፋ ነበር (ማቴ. 14:23)፡፡ ኢየሱስ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ተአምራቱና ትምህርቶቹ ሳይቀሩ ከእግዚአብሔር አብ እንደሚመጡ ተናግሯል (ዮሐ. 14:10)፡፡ ምናልባትም ወደ እግዚአብሔር በሚጸልይበት ጊዜ መመሪያዎችን ሳይቀበል አይቀርም፡፡

3) የጸሎት ተቀዳሚ ዓላማ የምንፈልገውን ነገር ከእግዚአብሔር ማግኘት አይደለም፡፡ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ጥያቄዎቻችንን መስማት ደስ ቢለውም፣ በጸሎት ውስጥ ሁለት ታላላቅ ዓላማዎች አሉ፡-

ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ፡- እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት ማድረግ ይፈልጋል፡፡ አዳምና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ፣ በእያንዳንዷ ቀን ከእነርሱ ጋር ይገናኝና ይነጋገር ነበር (ዘፍጥ. 3:8-9)፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ኃጢአት ሲሠሩ በመጀመሪያ የተፈጠረው ነገር የእነርሱ ከእግዚአብሔር መሸሽና ከእርሱ ጋር ግንኙነት ማቋረጥ ነበር፡፡ በኋላ፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያን የማደሪያውን ድንኳን እንዲሠሩለት ሲናገር፣ በመካከላቸው መኖር እንደሚፈልግ ነው የነገራቸው (ዘጸአ. 25:9)፡፡ ለዚያ ነው «የመገናኛው ድንኳን» ተብሎ የሚጠራው፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ሲጽፍ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ የተነሣ «ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው» (1ኛ ዮሐ. 1:3) ይላል፡፡ ስለዚህ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስንሄድ፣ በመጀመሪያ ልንፈልገው የሚገባን ነገር በእርሱ መገኘት መደሰት ነው፡፡ የቅርብ ጓደኞቻችንን መጎብኘትና ከእነርሱ ጋር ጊዜ ማጥፋት እንደሚያስደሰተን ሁሉ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን መብሰል ከፈለግን፣ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር መደሰትን ልንማር ይገባል፡፡



ለ) በሕይወትህ የእግዚአብሔርን ክብር ፈልግ፡- በቀዳሚነት ጸሎት ያስፈለገው እኛ የምንፈልጋቸውን ነገሮች እግዚአብሔር እንዲሰጠን የምንለምንበት አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ ወደ እግዚአብሔር የምንጸልይበት ወቅት በእኛ፣ በምንጸልይላቸው ሰዎችና በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንድትሆን የምንጸልይበት ነው፣ ያኔ እርሱ የሚገባውን ክብር ያገኛል፡፡ ሰዎች ምድራዊ አባታችንን ሲያከብሩልን እንደምንደሰት ሁሉ፣ እግዚአብሔር አባታችንና ኢየሱስ ሲከብሩ ልንደሰት ይገባል፡፡ ለዚያ ነው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ ጸሎት ሲያስተምር፣ «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን?» (ማቴ. 6:9-10) ያለው፡፡ ኢየሱስ የጸለየው ለእግዚአብሔር ክብርና የእርሱ ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ እንጂ፣ ለራሱ ፈቃድ አይደለም (ዮሐ. 17:1፤ ማቴ. 26:39፣ 42)፡፡ ስለዚህ ለራሳችን ጉዳይ ብቻ ለጸሎት ከመቅረብ፣ የእርሱን ክብርና መንግሥቱን መስፋት ወዘተ. . . ልንፈልግ ይገባል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ባደግን ቁጥር የእግዚአብሔር መሻት የእኛም መሻት ይሆናል (ዮሐ. 4:34)፡፡

| |
|---|
| 28ኛ ጥያቄ፡- ኤፌ. 1:17-19፣ 3:14-19፤ ቆላ. 1:9-14ን አንብብ፡፡ ሀ) ጳውሎስ ለአማኞች ባደረገው ጸሎት ላይ ያነሣቸውን ጥያቄዎች ዘርዝር፡፡ ለ) እነዚህ ጥያቄዎች እኛ ለራሳችንና ለሌሎች ከምናደርገው ጸሎት በምን ይለያሉ? ሐ) በምን መልኩ ነው ለሥጋ በረከትና ፈውስ እና ለመሳሰሉት ከመጸለይ ይልቅ፣ የጳውሎስ ጸሎት ምላሽ አስፈላጊ የሚሆነው? |

4) ጸሎታችን አምልኮ፣ ምስጋና፣ ንስሐና ለሌሎችና ለራሳችና የሚሆን ምልጃ የተቀላቀለበት መሆን አለበት፡፡ በአምልኮአችን የእግዚአብሔርን ባሕሪ እናወድሳለን፡፡ በምስጋና ጊዜ እግዚአብሔርን ስላደረገልን ነገር ሁሉ እናመሰግናለን፡፡ በንስሐ የሠራነውን ኃጢአት ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ምሕረቱንና በምናሳየው ኑሮ ለእርሱ የተሰጠን እንድንሆን እንጠይቀዋለን፡፡

በጥቅሉ «ኃጢአትን እንደ ሠራሁ ጥርጥር የለኝም። ይቅር በለን» ከማለት ይልቅ፣ ንስሐ መግባት ኃጢአትን ገልጦ (ሐሜት፣ ቁጣ፣ ኩራት፣ ያልተቀደሰ አሳብ፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል) ገልጦ ተናግሮ ንስሐ መግባት ነው። መንፈስ ቅዱስ ጸሎታችንን ተጠቅሞ እነዚህን ኃጢአቶች እንድናሸንፍ የሚረዳን የሠራነውን ኃጢአት ለይተን መግለጥ ስንችል ነው። ምልጃ ደግሞ እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ማገልገል የምንችልባቸውን ነገሮች መጠየቅ ነው። በደ:ጋሚ፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ካስተማረው ጸሎት ብዙ ልንማር እንችላለን (ማቴ. 6:10-14)። ጥያቄዎቹ ከይቅርታ፣ ከሰይጣን ነፃ ስለ መውጣትና ለዕለት ፍላጎት ከሚያስፈልጉ የሚወጡ አይደሉም። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለሥጋዊ ፍላጐታችን የሚያስፈልጉንን ነገሮች በሙሉ እንድንጠይቅ አልነገረንም። ለምሳሌ፣ አንድ ሐብታምን ምን ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር ብለን የማያስፈልገውን እንደምንጠይቅ ማለት ነው። ይልቁንም፣ እርሱ ያስተማረን ለመኖር የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንድንጠይቅ ነው። እርሱ እኛ ከምንፈልገው በላይ ሊሰጥን ይችላል። ነገር ግን ያንን እንዲወስን እንተውለታለን።

| |
|---|
| 29ኛ ጥያቄ:- በሚመጣው ሳምንት፣ በየዕለቱ የጸለያችኋቸውን ነገሮች ዝርዝር ጻፍ። ሀ) እንዴት ነው እግዚአብሔርን ያመለክሽው? ለ) እግዚአብሔርን ያመሰገንከው ለምንድን ነው? ሐ) የትኞቹን ኃጢአቶች ነው ገልጠህ ንስሐ የገባኸው? መ) እግዚአብሔርን ምን ዓይነት ነገሮች ጠየቅኸው? ምኞቶችህ ናቸው ወይስ የሚያስፈልጉህ ነገሮች? ሠ) በኤፌሶንና በቆላስይስ ላይ ካሉት የጳውሎስ ጸሎቶች ጋር የአንተን ጸሎት አነጻጽር። እንደ ጳውሎስ ዓይነት ጸሎቶች እንዲሆኑ በምን ዓይነት ሁኔታ ጸሎትህን ልትቀይር ትችላለህ? |

5) ምንም እንኳን የኅብረት ጸሎት መልካም ቢሆንም፣ በባሕሪ ለማደግና በእግዚአብሔር መንገድ ለመመራት የሚያስችለው ኃይል የሚመጠው በግል ጸሎት ነው። አብዛኞቻችን በማለዳ ተነሥተን ከቤተሰቦቻችን ጋር እንጸልያለን። ወይም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችን ጋር በመሆን በጣም እስኪመሽ እንጸልያለን። ግን



ለብቻችን ሆነን ምን ያክል ሰዓት ከእግዚአብሔር ጋር እናጠፋለን? እግዚአብሔር ሲናገረን የምንሰማው፣ ሲመራን የምናየውና የምንለወጠው ለብቻችን ስንጸልይ ነው። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አንደ ጸለየ ምንም ጥርጥር የለውም። ነገር ግን የኃይሉ ምንጭ ይፈልቅ የነበረው በተራራው ላይ ለብቻው ከአባቱ ጋር በነበረት ወቅት ነው (ማቴ. 14:23)።

| |
|---|
| 30ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብዛኛውን ጊዜ የምታጠፋው በግል ጸሎት ነው ወይስ በኅብረት ጸሎት? ለ) ልትቀይረው የሚገባህ ባሕሪ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻህ ጊዜ ለመያዝ ማላደግ ያለብህ ነገር ምንድን ነው? |

6) ጸሎት መናገር ብቻ አይደለም፣ መስማትንም ያጠቃልላል። ጓደኞችህ ሲጐበኙህ ሲመጡ ጊዜውን በሙሉ እነርሱን አድማጭ ብቻ ራስህን ተናገሪ በማድረግ አትጨርሰውም። በእውነተኛ ግንኙነት፣ ሰዎች በመናገርም በመስማትም ነው ጊዜ የሚጠፉት። ጸሎትም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔርን የምናነጋግርበትና በልባችን ያለውን የምንናገርበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ተቀምጠን በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እርሱን ደግሞ የምንሰማበት ጊዜ ያስፈልጋል። ደግሞም ልክ እንደ ሳሙኤል፣ «ባሪያህ ይሰማሃልና ተናገር» (1ኛ ሳሙ. 3:10)። የምንልባቸው ጊዜያትም አሉ። እግዚአብሔር ነቢዩ ኤልያስን የተናገረው በንፋስም ሆነ በማዕበል ሳይሆን በፀጥታ ድምጽ ነበር። በጩኸት ጸሎታችንና ለእግዚአብሔር በመጸለይ ሲበዛ ከተወጠርን፣ የእርሱን ድምጽ ሳንሰማ ልንቀር እንችላለን።

7) የጸሎታችን ዓይነት ከልባችን ሁኔታ በላይ አስፈላጊ አይደለም። እጆቻችንን ወደ ላይ ብናነሣ፣ ዓይኖቻችንን ብንጨፍን፣ ጭንቅላታችንን ዝቅ ብናደርግ፣ ወይም ብንንበረከክ ምንም ለውጥ አያመጣም። ነገር ግን የሚያስፈልገው ነገር ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ለእርሱ በተሸነፈ ልብ ነው ወይ? የሚለው ነው። የምንጸልየው ለፈጠረን አባታችን ለእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፣ የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም በትሕትና ልንቀርብ ያስፈልገናል።

የእኛ ፍላጐት እርሱን ማስደሰት ሊሆን ይገባል። እርሱን የሚያስደስተው ነገር የእኛም ፍላጐት ይሆናል፣ ያም በጸሎታችን በኩል ይገለጣል።

8) ጾምን ከጸሎት ጋር በማጣመር የምናካሂድበት ጊዜ አለ። የጾም ዓላማ እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግልን ጉቦ ለመስጠት አይደለም። ይልቁንም፣ በጸሎታችንና በልባችን ባለው ነገር ላይ ትኩረት ለማድረግ ሌሎች እንቅስቃሴ እና እንደ መብል ያሉ የተለመዱ ነገሮችን ተወት ለማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር የሰጠን መሣሪያ ነው። በጸሎታችን ላይ እንድናተኩርና የምንጸልይበት ጉዳይ ለእኛ ምን ያህል አንገብጋቢ እንደ ሆነ ለእግዚአብሔር የምንገልጥበት ነው። ጾም የእግዚአብሔርን ፊት እንድንፈልግ ያዘጋጀናል። ሆኖም፣ ጾም በልባችን ውስጥ ካለ ልዩ መሻት እና እግዚአብሔር እንዲሠራ ከምንፈልገው ያልተለመደ ነገር ጋር የተገናኘ ነገር እንጂ በዘልማድ የምናደርገው ነገር እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል።

9) ጸሎትና እምነት፡- ያዕቆብ 1:1-8 ላይ ከምንችለው በላይ የሆነ ነገር ሲገጥመን እግዚአብሔር ልዩ ጥበብ እንዲሰጠን እንድንጠይቅ ይነግረናል። እግዚአብሔር ያንን ጥበብ ሲሰጠን ቃል ገብቷል። ነገር ግን ያዕቆብ «በእምነት» እንድንጸልይ አስጠንቅቋል። እግዚአብሔርን ወይም ጸሎት የመመለስ ችሎታውን ወይም ጸሎታችንን ለመመለስ ያለውን ፈቃደኝነት ከተጠራጠርን፣ ያዕቆብ ምንም እንደማናገኝ ተናግሯል። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሁሉ የማይመልሰው በቂ እምነት ስለ ሌለን ነው ብለው የሚያስተምሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች አሉ። ከዚያ የተነሣ፣ አንድ ሰው ካልተፈወሰ ሰውየው በቂ እምነት ስለሌለው ነው ይላሉ። አንድ ክርስቲያን በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሲጸልይ «ፈቃድህ ካልሆነ» ብሎ ቢጸልይ ይወቅሱታል። ምክንያቱ ይሄ አባባላቸው የሚያሳየው በቂ እምነት እንደሌላቸው ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎትና እምነት ምንድን ነው የሚያስተምረው?



ሀ) እምነት በራሱ አይሠራም፣ ይልቁን የምናምንበት ነገር ነው የሚሠራው። ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ለሐሰተኛ ጣዖት «በእምነት» ሲጸልይና ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ሳያገኝ ይችላል። ምክንያቱም እምነቱ ኃይል በሌለው ነገር ላይ ስለሆነ ነው። ስለዚህ እምነት እንዲሠራ ካስፈለገ፣ እምነታችን ራሱን በቃሉ በገለጠው እውነተኛው እግዚአብሔር ላይ ሊሆን ይገባዋል።

ለ) እምነታችን በተገለጠው የእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ ሊሆን ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጠኝነት ልንጸልይባቸው የምንችላቸውን በርካታ ነገሮችን ቃል ይገባልናል። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ለማለት ያለውን ፈቃደኝነት አውቀን በእርግጠኝነት ለበደላችን ይቅርታ ለማግኘት መጸለይ እንችላለን። ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ ልንጸልይ እንችላለን። እምነት ማለት እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠበት የሆነ ልዩ ነገር ሲገጥመን የማይቻል ቢመስል እንኳን፣ እርሱ ቃል የገባውን እንደሚፈጽም ማመን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ ሁሉም የእምነት ሰዎች የማይቻል በሚመስል ሁኔታ ውስጥ እንኳ ሆነው የሚያምኑት የእግዚአብሔር «የተስፋ ቃል» ነበራቸው (ለምሳሌ፡- የአብርሃም ካራንን መልቀቅ (ዘፍጥ. 12:1-5)፣ የይስሐቅ መወለድ (ዘፍጥ. 15:1-6)። እነርሱ በሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ «በግምት» አልነበረም የሚያውቁት።

ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ የተስፋ ቃል ያላገኘንባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ባለቤታችን ታማ ለፈውስ ልንጸልይ እንችላለን። አብዛኛውን ጊዜ፣ እግዚአብሔር ይፈውሳት አይፈውሳት አናውቅም። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው፣ «የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» (ሉቃ. 22:42) የምንለው። ኢየሱስ የጸለየው እንዲህ ነው፣ እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በግልጽ ካላወቅን እንዲህ ነው ልንጸልይ የሚገባን። እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግልን አይደለም «እምነትን» የምናሳየው። ይልቁንም፣ እንደዚያ ባለ ሁኔታ ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለእኛ ለልጆቹ

ተወዳጅ፣ ፍትሐዊ፣ ትክክል፣ የሆነ ነገር እንደሚያደርግ ልናምነው ይገባል።

ሐ) እግዚአብሔር «ቆይ» ወይም «አይሆንም ወይም ደግሞ «እሺ» ሊለን ይችላል። እርሱ እግዚአብሔር ነው። ምን መሥራት እንዳለበት ልንነግረው አንችልም። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ፈቃዱን ይነግረናል። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጸሎት በላይ የሆነ ታላቅ ዓላማ አለው። ጥያቄአችን «እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ መልካም የሆነውን እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ። መፈወስ እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን መልካም የሆነውን አድርግ። የአንተን ፈቃድ እፈልጋለሁ።» የሚል ከሆነ፣ እግዚአብሔር ካልፈወሰን፣ ከመታመማችን የሚበልጥ ትልቅ ዓላማ እንዳለው እንረዳለን (ለምሳሌ፡- ዮሐ. 9:1-5)። አንዳንድ ጊዜ በትዕግሥት እንድናድግ የእርሱን የፍቅር እጅ፣ ኃይለኝነቱንና ሁሉን የሚያውቀውን እጁን እንድናውቅ እንድንቆይ ይፈልጋል። ካደግን በኋላ ግን ጥያቄአችንን ይመልስልናል። ልክ ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር መፈለግ የእግዚአብሔርን በረከት ከመፈለግ በላይ አስፈላጊ እንደ ሆነ እንደ ተረዳው (ዘጸእ. 33:12-23) ሁሉ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ከምንፈልገው ነገር በላይ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ይፈልጋል። ምላሽ ያላገኘ ጸሎት ወይም የዘገየ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ እንድናጠፋ ያስገድደናል፣ ያም ከተመለሰ ጸሎት በላይ አስፈላጊ ነው።

10) ጸሎታችንን በጥቅሉ ሳይሆን መጠየቅ ያለብንን ነገር ነጥለን የምንጠይቅበት ነው። እግዚአብሔር ለጸሎታችን የሰጠውን ምላሽ መመስከር ያስደስታል። ነገር ግን በተለምዶ በጥቅሉ ነው የምንጸልየው። «እግዚአብሔር ሆይ፣ እከሌን ባርከው» እንላለን። ከዚያም እግዚአብሔር ጸሎታችንን መመለሱን በምንም መንገድ አናውቅም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአብዛኞዎቹ ሰዎች ጸሎት በግልጽ የተቀመጠ ነው። ሰዎች ንስሐ የሚገቡት በግልጽ የተቀመጠ ኃጢአትን ነው። ሲጠይቁም በግልጽ የሚፈልጉትን



አመልክተው ነው (ለምሳሌ፡- በንጉሡ ዘንድ ሞገስን ስጠኝ። ነህ. 1:11)። ስለዚህ ለወንጌል ስርጭት ስንጸልይም፣ እግዚአብሔር እንዲሠራ የምንፈልግበትን ብሔር መጥራት አለብን። ስወንጌላውያን ስንጸልይም የእያንዳንዱን ስም ጠርተን ነው። ለመንፈሳዊ እድገታቸውና ለሞገሳቸው፣ እንዲሁም ለመመስከር ድፍረቱን እንዲያገኙ (ለምሳሌ፣ ቆላ. 4:3-4)፣ ለእነርሱና ለቤተሰባቸው ጤንነት፣ ማናቸውም መከራ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ልጆቻቸው እንዳይቆጡ፣ ወዘተ. . . መጸለይ አለብን። በጥቅሉ ሳይሆን በነጠላ ስንጸልይ ነው በጸሎታችን ውስጥ ያለውን እምነት የምናሳየው።

11) ጸሎትና ጩኸት፡- ሰዎች በሚችሉት አቅም ሁሉ ጮክ ብለው መጸለያቸው የተለመደ ነገር እየሆነ ነው፣ በእርግጥ ያ ትጋታቸው እንደ ሆነ ያምናሉ። ነገር ግን እኛ ጸሎትን በተሳሳተ መልኩ ተረድተን እያደረገነው ያለው ስለ ጸሎትና ከእግዚአብሔር ጋር ስለ መገናኘት ካለን የተሳሳተ መረዳት ተነሥተን እያደረግነው እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። የጸሎታችን ጩኸት እግዚአብሔር እኛን እንዲሰማ ይበልጥ ያበረታታዋል ብለን የምናስብ ከሆነ፣ ልክ አምላካቸውን ከእንቅልፉ እንዲቀሰቅሱት ፈተና እንደ ገጠማቸው የበኣል ነቢያት መሆናችን ነው! (1ኛ ነገሥ. 18:25-29)። እግዚአብሔር ከመጸለያችን በፊት እንኳ ቢሆን ምን እንደምናስብ ያውቃል (መዝ. 139:4)። አፋችንን ለጸሎት መክፈት እንኳን አያስፈልገንም። የሰማዩ አባታችን ገና በአሳባችን ያለውን ያልተናገርናቸውን ቃላት ሳይቀር ይሰማል። መጮህ ያለብን እግዚአብሔር በሰማይ ርቆ ስላለ እንደ ሆነ ካሰብን፣ መንፈስ ቅዱስ በልባችን እንደሚኖር ረስተናል ማለት ነው። ሥላሴ በእኛ ውስጥ እንጂ በጣም በሰማይ ርቆ አይደለም ያለው (ዮሐ. 14:23)። የድምጻችን ጩኸት ሰይጣንን ከእኛ የሚያርቀው ከመሰለን፣ ሰይጣንን የምናሸንፈው በድምጻችን ጩኸት ሳይሆን በኢየሱስ አሸናፊነት መሆኑን ዘንግተናል ማለት ነው። ማንም ንጉሥ ወይም

አባት ጉብኚዎቹ ወይም ልጆቹ መጥተው እንዲጮኹበት አይፈልግም:: ይህ ያለማክበራችን ምልክት ነው:: በእርግጠኝነት አንድ ሰው በእግዚአብሔር መገኘት ፊት ሆኖ ሲጮህ እግዚአብሔርን አለማክበር ነው:: በጣም ጮክ ብለን የመጸለይ ልማድ ካለንና የቁጣ በሚመስል ድምጽ የምንጮህ ከሆነ፣ የምንጸልየው በትክክለኛ የልብ መሻት መሆን አለመሆኑንና በታላቁ እግዚአብሔር ፊት በአክብሮት እያደረግነው መሆን አለመሆኑን ልንመረምር ይገባል::

12) የኅብረት ጸሎት:- ሰይጣን አብዛኛውን ጊዜ የሚያሸንፈን በሕዝብ ፊት ስንጸልይ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ፊት ወይም በአማኞች ቡድን ውስጥ ስንጸልይ ግን ልንረዳቸው የሚገቡን በርካታ ነገሮች አሉ::

ሀ) የጉባኤ ጸሎት ለቤተ ክርስቲያን አመራር የሚያበቃ የግል ጥንካሬ አይሰጠንም:: መሪነት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ነው፣ ያም በግላችን የምናዳብረው ነው:: መንፈሳዊ ዕድገትና መንፈሳዊ ብስለት የሚመጡት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን የጋራ ጊዜ ነው:: እንዳንዳችን እግዚአብሔርን ስናውቀው ፈቃዱን ይገልጥልናል፣ እኛም እንታዘዛለን፣ በእርሱ ኃይልም እንመካለን::

| |
|---|
| 31ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 6:5-8ን አንብብ:: ሀ) ኢየሱስ ጉባኤ ፊት ስለ መጸለይ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ለ) አንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲጸልዩ እንዴት ይህንን ማስጠንቀቂያ እንደማይታዘዙ ግለጽ:: |

ለ) በጉባኤ ፊት መጸለይ በፍጥነት ወደ ግብዝነት ጸሎት ሊመራ ይችላል:: ጸሎታችንን የሚሰሙትን ሰዎች ለማስገረም ስንሞክር፣ በግብዝነት ኃጢአት ወድቀናል ማለት ነው:: ይህ ኃጢአት ከንጹሕ ሕሊና ከመጸለይ ይልቅ ከሌሎች ክብርን ለመቀበል የሚመነጭ ነው:: ግብዝነት ሌሎችን ለማስገረም ድምጻችንን ከፍ አድርገን መጸለይ ወይም የውሸት እንባ



መርጨትን ያጠቃልላል:: ሌሎችን ለማስገረም ስንል ድምጻችንን ይበልጥ መንፈሳዊ ለማድረግ ስንሞክር ወይም በሌሎች ፊት መንፈሳዊ መስለን ለመታየት ስንል ፊታችንን ወደ ሰማይ ማድረግ የግብዝነት ኃጢአት ነው::

ሐ) ያለምንም አሳብ ወይም ቃላትን ያለ ምክንያት መደጋገምን አስወግድ:: ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ «ከንቱ ከሆነ ድግግሞሽ» እንዲታቀቡ አሳስቧል:: የእግዚአብሔርን ስም ባልተለመደ መንገድ ስንደጋግም በከንቱ እየደጋገምነው ነው (ለምሳሌ:- አመሰግንሃለሁ፣ ኢየሱስ ሆይ፣ ስላደረግሽው ነገር አመሰግንሃለሁ፣ ኢየሱስ ሆይ፣ ለእኔ ስላደረገኸው አመስግንሃለሁ::) በዘጸአት 20:7 ላይ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እንዳንጠራ ተነግሮናል:: የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ማለት ያለ ምንም ዓላማና አሳብ የእግዚአብሔርን ስም መጠቀም ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ስም ስንጠራ፣ በዓላማና በመረዳት መሆን አለበት:: ወይም እንደ ሃሌሉያ ወይም አሜን ያሉ ቃላትን ያለምንም ምክንያት መጠቀም አላስፈላጊ ነው:: እግዚአብሔር የሚፈልገው ጸሎታችን ትርጉም ያለው ሲሆን እንጂ፣ በልምድ ሳናስበው ስንጸልየው አይደለም::

መ) ጸሎት እግዚአብሔርን የምናነጋግርበት ጊዜ እንጂ፣ የምንሰብክበት ጊዜ አይደለም:: ሰባኪዎች ብዙ ጊዜ ጸሎታቸውን የሚጠቀሙት ፕሮግራሙን ለመቀጠል ነው:: ይህ የጸሎት ዓላማ አይደለም::

13) በመንፈስ መጸለይ:- (ኤፌ. 6:18) በጣም አስገራሚ ከሆኑ እውነቶች ውስጥ አንዱ ስንጸልይ ብቻችንን አለመሆናችን ነው:: መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ይጸልያል (ሮሜ 8:26):: ይህ ማለት በምንጸልይበት ጊዜ መቃተት አለብን፣ ያም መቃተት መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት አይደለም:: ይልቁንም፣ መንፈስ ቅዱስ በልባችን በምሥጢር ይጸልያል፣ እናም እርሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለሚያውቅ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይጸልያል ማለት ነው::

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጋራ የምናደርገውን ጸሎት የሚያደናቅፉ ሦስት ነገሮች አሉ።

ሀ) በሕይወታችን ያለ ኃጢአት። ያ ኃጢአት ምናልባት በእግዚአብሔር ወይም በበደልነው ሰው ፊት ንስሐ ያልገባንበት ሊሆን ይችላል (1ኛ ጴጥ. 3:7)። ወይም አንድን ነገር ለሥጋዬ ጥቅም የመፈለግ የተሳሳተ አመለካከት ሊሆን ይችላል (ያዕ. 4:3)። ለምሳሌ:- እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲያደርገን መጸለይ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ያንን የምንጸልየው እግዚአብሔርን ለማገልገል ከመፈለግ ይልቅ ከሌሎች ክብርን ለማግኘት ነው። ወይም የምናደርገውን ነገር የምንፈጽመው ለእግዚአብሔር ክብር በማያመጣ መልኩ ነው። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ንብረት እንዲሰጥ እንጸልያለን። ነገር ግን የሰዎች ምላሽ ቀና እንዲሆን ጉቦ እንሰጣለን። ያልተመለሰ ጸሎት ካለን አብዛኛውን ጊዜ በጥያቄአችን ራስ ወዳድነት ስላለ፣ ወይም ኃጢአት በሕይወታችን ስላለ፣ በእግዚአብሔር ላይ አለማመን ስላለን፣ ወይም የምንጸልየው ከተሳሳተ ምክንያት ስለሆነ ሊሆን ይችላል።

ለ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማወቅ። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንጸልይ ተነግሮናል። እግዚአብሔር በቃሉ ስለ ፈቃዱ የገለጠውን ነገር እንድናውቅ ይጠብቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር ያለውን ካላወቅን ከፈቃዱ ጋር የሚጋጩ ነገሮችን ልንጸልይ እንችላለን። ለምሳሌ:- አንዳንድ ጊዜ ወጣት የሆነ ሰው፣ «እግዚአብሔር ሆይ፣ ያልዳነችው እጮኛዬ ሚስቴ እንደምትሆን ንገረኝ» ብሎ ሊጸለይ ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከመጸለያችን በፊት ይሄ ፈቃዱ እንዳልሆነ ተናግሯል። እግዚአብሔር ፈቃዱ መሆኑን አስቀድሞ ባሳየባቸው ለጠፉት መዳን፣ መንፈሳዊ እድገትና ብስለት፣ የአገልግሎት በር መከፈት፣ ወዘተ. . . ባሉ ነገሮች ላይ ስንጸልይ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንደምንጸልይ እናውቃለን። ነገር ግን የእግዚአብሐር ፈቃድ ይሁኑ



አይሁኑ የማናውቃቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ልክ ኢየሱስ እንዳለው፣ «የአንተ ፈቃድ ከሆነ» ብለን ልንጸልይ እንችላለን። ነገር ግን በተለዩ ሁኔታዎች ላይ የእግዚአብሔር የሆነን ነገር ለመለየት ጊዜ መውሰድ አለብን። ስለ አንድ ነገር ለመጸለይ ሸክሙ ሲኖረን (ለሥጋችን ፍላጐት ካልሆነ)፣ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት ነው።

ሐ) አእምሮአችንን መቆጣጠር አለመማርና ዝግጁነት። በመንፈስ ልንጸልይ የምንችለው ንቁ ስንሆን ነው (ቆላ. 4:2)። በሁለት መንገዶች ንቁ መሆን አለብን። አንደኛው፣ በዙሪያችን ላሉና ጸሎታችንን ለሚፈልጉ ነገሮች ንቁ መሆን ያስፈልጋል። ጸሎት ያለ አሳብ ዝም ብለን የምናደርገው መደበኛ ዝርዝር ነገሮች መሆን የለበትም። ሁለተኛ በምንጸልይበት ወቅት አእምሮአችን ንቁ መሆን አለበት። አብዛኛውን ጊዜ ሰይጣን በምንጸልይበት ወቅት እንቅልፍ እንዲጫነን ያደርጋል። ንቁ ካልሆንን በመንፈስ እየጸለይን አይደለም። ስለዚህ እንዳንደክም በቂ እንቅልፍ መተኛት ያስፈልገናል። እንዲሁም በምንጸልይበት ወቅት ንቁ እንድንሆን አእምሮአችንን መቆጣጠርን መማር አለብን።

14) ጸሎትና ለእግዚአብሔር መሥራት:- በአገልጋዮች ላይ ከሚጋረጡ አደጋዎች መካከል አንዱ እግዚአብሔርን ከማገልገል ብዛትና የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን በማስፈጸም አብዛኛውን ጊዜአቸውን ከማጥፋታቸው የተነሣ የጸሎት ጊዜአቸውን መቀነስ ነው። በሥራ በተወጠርን ቁጥር፣ ጸሎታችን እየቀነሰ የሚሄድ ይመስላል። ነገር ግን ይህ ማድረግ ያለብን ነገር ተቃራኒው ነው። በጣም ሥራ በበዛብን ቁጥር አብልጠን ልንጸልይ ይገባል። ለመጸለይ እስከማንችል ድረስ በሥራ ከተወጠርን፣ ይሄ የሚያሳየው በራሳችን ጥንካሬ እንጂ በእግዚአብሔር ኃይል እንዳላደረግነው ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔርን ሳልጠይቅ የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት እችላለሁ የሚል ኩሩ ልብንም ያሳያል። ትኩረቷ ከጸሎት ይልቅ በአገልግሎቶቿ ላይ የሆነ ማንኛ

ውም ቤተ ክርስቲያን የምትሠራው ከእግዚአብሔር ኃይል ውጪ ነው። ስለ ጸሎትና አገልግሎት ስናስብ ልናስታውሳቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች አሉ፦

ሀ) አንድ ሰው በአመራር ላይ ከፍ ባለ ቁጥር ይበልጥ ጊዜውን በጸሎት ሊያጠፋ ይገባል። በሐዋ. ሥራ 6፡1-7 ላይ ሐዋርያት በአስተዳደር ጉዳዮች ላይ (የማዕድ አገልግሎት) ውስጥ መግባትን እምቢ ሲሉ እናያለን። ምክንያቱም ያንን ማድረግ ሊያደርጓቸው ከሚገባቸው ከሁለት ነገሮች ማለትም ከጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማር ስለሚያስተጓጉላቸው ነው።

ለ) ጸሎት ሥራ ነው እንዲሁም አገልግሎት ነው። በቆላ. 4፡12-13 ላይ ጳውሎስ፣ ኤጳፍራ ለእነርሱ በትጋት በጸሎቱ ይጋደላል ብሎ ለአማኞች ይነግራቸዋል። ጳውሎስ ኤጳፍራ ለእነርሱ የሚተጋው ለእነርሱ በመጸለይ እንደ ሆነ ይናገራል። እንደ መሪ፣ በጣም ሥራ በበዛብን ቁጥር፣ የበለጠ ጭንቀት ይኖርብናል፣ በጸሎት የምናሳልፍው ጊዜ ባነሰ ቁጥር፣ የምንሠራው ሥራም እያነሰ ይሄዳል። ኢሳይያስ ድል የሚመጣው በሰው ላይሆን በእግዚአብሔር በማመን እንደ ሆነ ተነግሮታል። ለችግራችን ምላሽ የሚያመጣ የሚመስለን ነገር፣ በራሳችን ኃይል ስናደርገው ችግር የሚያመጣ ነገር ይሆናል (ኢሳ. 30፡15-17)። ምንም እንኳን ለእኛ ባይገባንም፣ አንድን ነገር ለማድረግ በትጋት በሠራን ቁጥር፣ የምናገኘው ውጤት አናሳ ይሆናል። ነገር ግን መፍትሔ ለማግኘት በጸሎት ብዙ ጊዜ ባጠፋን ቁጥር፣ ይበልጥ ስኬታማ እንሆናለን። ኢየሱስ በጣም አገልግሎት በበዛበት ጊዜ፣ በጣም ይጸልይ ነበር። እንዲሁም ፈጽሞ ጭንቀትና ችኮላ አይታይበትም ነበር።

ሐ) ማንኛውም በጥንቃቄ ያልጸለይንበት አገልግሎት በራሳችን ኃይል የምናደርገው ነው። የእኛ ሥራ እንጂ የእግዚአብሔር ሥራ አይሆንም። የእግዚአብሔርን ሥራ የምንሠራው በጸሎት እርሱ እንደሚያደርገው ስናምን ነው።



እግዚአብሔር ያለ እኛ ጸሎት መሥራት ይችላል። ነገር ግን በጸሎታችን የሥራው ተካፋዮች እንድንሆን ይጋብዘናል። ያም ልክ ትንሽ ልጁን ሞፈሩን ይዞ ከእርሱ ጋር እንዲያርስ እንደሚጠይቅ እራሽ አባት ነው። አባትየው ብቻውን ሊያርስ ይችላል፣ ነገር ግን ሥራውን አብረው መሥራታቸው፣ የትንሹ ልጅ አስተዋጽኦ ቀላል ቢሆንም፣ ለአባትየውም ሆነ ለልጅየው ደስታን ይሰጣል። በተመሳሳይ መንገድ፣ እግዚአብሔር ያለ እኛ ሥራውን ሁሉ ሊሠራ ይችላል። ነገር ግን በመጸለይ በሥራው እንድንተባበረው ይጋብዘናል።

መ) መሪነት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር አጀንዳ ማምጣት ነው። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ይፈልገዋል ብለን ያመንበትን ነገር ሰዎች እንዲያደርጉ የማድረግ «ሥልጣን» የለንም። ታዲያ እንዴት እንለውጣቸዋለን? እግዚአብሔር የሰጠን ብቸኛው መሣሪያ ጸሎት ነው። የሰዎችን ልብ፣ አእምሮአቸውን፣ ባሕሪአቸውንና ተግባራቸውን የምንለውጠው በጸሎት ነው።

ሆኖም፣ ማድረግ የምንፈልገውን በራሳችን ከወሰንን በኋላ እግዚአብሔር እንዲባርከው ከመጠየቅ ልንጠነቀቅ ይገባል። ይልቁንም፣ በምንጸልይበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅና በመፈጸም ላይ በሙላት ልንስጥ ይገባል። እግዚአብሔር ዕቅዳችንን መቀየር ከፈለገ ፈቃደኛ እንደ ሆንን ልንነግረው ይገባል። የእኛን ፈቃድ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ልናደርግ ወይም የግል ፍላጐታችንን ልንክድ ወይም በዕቅዳችን ላይ ያላንን ፍላጐት ልንተው ይገባል። ይልቁንም፣ ከልባችን «የአንተ ፈቃድ ይሁን» ልንለው ይገባል። የእግዚአብሔርን እንጂ የራሳችንን ፈቃድ ልንከተል አይገባም። የእርሱ ፈቃድና የእርሱ ሥራ ይፈጸም ዘንድ እግዚአብሔር አሳባችንንና ተግባራችንን እንዲመራ ልንጠይቀው ይገባል። እናም ሁኔታዎችን በመጠቀም ወይም በሌላ እግዚአብሔር እኛ መልካም ነው ብለን ያሰብነውን ከቀየረው እግዚአብሔር ሥራውን በመሥራቱ ደስ ሊለን ይገባል። የእኛ ዕቅድ ስላልተሳካ ልንቆጣ አይገባም። አንድ ጊዜ በታማኝነት

ሥራችንንና ዕቅዳችንን ከሠራን ውጤቱ በእግዚአብሔር እጅ ስለሆነ የሌሎችን አቋመስማማት ልንፈራ አይገባም። እናም ስለ እግዚአብሔር ክብር ማድረግ የምንፈልገው ነገር ስኬትና አለመሳካት በእጁ ላይ እናስቀምጣለን። ሥራው የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ አይደለም። ቤተ ክርስቲያኒቱ የእርሱ እንጂ የእኛ አይደለችም። ስለዚህ የምንፈልገውን ነገር እኛው ከምንወስንና እግዚአብሔር ያንን እንዲባርክልን ከምንጠይቅ በጸሎት እርሱ እንዲመራን ልንፈቅድለት ይገባል።

32ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዕቅዶቻችንን ራሳችን የምናወጣበትንና እግዚአብሔር እንዲባርከው የምንጸልይባቸውን መንገዶች ግለጥ። ለ) እግዚአብሔር ዕቅዳችንን እንዲባርክልን በመጸለይና እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲገልጥልንና ወደ ስኬት እንዲመራን በመጸለይ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

15) ጸሎት እግዚአብሔር እንድንጠቀምበት የሰጠን ነገር ከመጠቀም ኃላፊነታችን ነፃ አያደርገንም። ጥሩ ዕቅድ ላለማውጣታችን ምክንያት ሊሆን አይገባም። እግዚአብሔር ለክብሩ እንጠቀምበት ዘንድ አእምሮ ሰጥቶናል። ከጸሎታችን ጋር ዕቅድ ካላወጣን፣ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይጠቀምበትም ወይም ሥራውንም በእኛ አይሠራም። (ምሳሌ፣ ነህምያ ጸልዮ ነበር፣ ነገር ግን ዕቅድም አውጥቷል። ንጉሡ ምን እንደሚፈልግ ሲጠይቀው ነህምያ ምን ማለት እንዳለበት ዐቅዶ ነበር። የእግዚአብሔርን ሥራ ለመፈጸም እግዚአብሔር የነህምያን ዕቅድና ጸሎት ተጠቅሟል [ነህ. 1-2ን ተመልከት])። ጸሎት በርትቶ ላለመሥራት ወይም በሥራ ላለመጠመድ ምክንያት ሊሆን አይገባም። ጳውሎስ እንዴት በሙሉ ኃይሉ እንደሚሠራ ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 15:9-10)። አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር የምንጸልይበትን አንድ ነገር በልባችን ያስቀምጣል። ነገር ግን መፍትሔ ለማምጣት አብረነው እንድንሠራ ይጠብቃል። በማናቸውም ነገሮች ላይ በትጋት መጸለይና ሥራውን እንዲሠራ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ያስፈልጋል። በራሳችን ኃይል ዘላቂነት ያለው አንዳች ነገር ማድረግ እንደማንችል እናውቃለን።



ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ከፈጠርን ብቻ በእግዚአብሔር መንገድና ለእግዚአብሔር ክብር ሥራው ይከናወናል።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ተጨማሪ ፕሮግራም፣ የበለጠ ጥበብ፣ ወይም የተሻለ ዘዴ አይደለም። ይልቁንም፣ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያላቸውና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሪዎች የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። የዚህ ኅብረት መሠረት ጸሎት ነው። ከጸሎት ውጪ የመሪው ኃይልና መንፈሳዊ ሕይወት ደካማ ይሆናል። እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራው በወንዶችና ሴቶች ልጆቹ እንጂ በፕሮግራሞ አይደለም። በሥራ ብዛት ለጸሎት የሚሆን ጊዜ ስናጣ፣ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ። <u>አንደኛ</u>:- በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደርቃለን። እግዚአብሔር ኃይል ካላስታጠቀን፣ ስለምንደክም የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት አንችልም። <u>ሁለተኛ</u>፣ ኩራተኞች እንሆንና የእግዚአብሔርን ሥራ በራሳችን ጥንካሬ መሥራት የምንችል ይመስለናል። ሕይወታችን ደረቅ እንደ ሆነ ከተሰማን፣ ከደከምን፣ ሳንደክም ለመጸለይ በማያስችል ሁኔታ በሥራ ተጠምደናል ብለን ካሰብን፣ ከኃይል ምንጭ ርቀናል ማለት ነው፣ ያም ከጸሎት ምንጭ እንደ መራቅ ነው። የጸሎት ሰው ወደ መሆን ልንመለስና የእግዚአብሔርን ኃይልና መንፈስ የሚወቁ ሰዎች ልንሆን ይገባል።

**አራተኛ ቀን:-** ለሳምንታዊ ስብሰባ የሳምንቱን ትምህርት ገምግም።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

በትምህርት አንድ ላይ የተገለጠውን የስብሰባ አካሄድ ተከተል። ከአሁን በኋላ የውይይት ጥያቄዎችን ብቻ እናካትታለን።

**የውይይት ጥያቄዎች:-**

1. ሀ) በቡድን ሆናችሁ የማያምኑ ሰዎች በመደበኛው ዓይነት ሰው ላይ የሚመለከቷቸውን ባሕሪዎች ዘርዝሩ። ያ ሰው ከቤተሰቡ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖረው

ግንኙነት፣ በሥራው ቦታ ስለሚኖረው ግንኙነትና በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚኖረው ግንኙነት አስቡ። ለ) መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ አራት የሕይወት አቅጣጫዎች ላይ አንድ ሰው መሆን አለበት ብሎ የሚያስተምረው ምንድን ነው? ዓለማውያን ከሚያምኑት ጋር ያላቸው ልዩነትና አንድነት ምንድን ነው? ሐ) አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች እነዚህ ባሕርያት አሏቸው? ከሌላቸው፣ ለምን? መ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ይታወቃሉን? ካልሆነ፣ ይሄ ወንጌል እንዳይስፋፋ ምን ዓይነት መሰናክል ይፈጥራል? ሠ) አማኞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ አማኝ ሊሆን ወደሚገባው ሰው ለማደግ ሕይወታቸውን መስወጥ ያለባቸው ለምንድን ነው?

2. ሀ) መንፈሳዊ በመሆናቸው የተነሣ በከፍተኛ ደረጃ የሚከበሩ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችሁን አባላት ዘርዝር። ለ) ከባሕሪያቸው የትኞቹ ናቸው ሰዎች እንዲከበሩ ያደረጋቸው? ሐ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ባሕሪ የቤተ ክርስቲያን አመራር መሠረት ሆኖ ለምን የተሳሰ ይመስላችኋል? መ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሪነት የተመረጡት መንፈሳዊ ባሕሪ ስለሚታይባቸው ነው? ካልሆነ፣ አባላት ሽማግሌዎችን እንዴት ነው የሚመርጡት? ሠ) ከመሪዎች የተሳሳተ ባሕሪ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን ዘርዝር።

3. ሀ) እውነተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ያልሆነ ሰው ለቤተ ክርስቲያን አመራር ሲመረጥ አይተህ ታውቃለህ? በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ይህ እንዴት ሊከሰት ይችላል ብለህ ታስባለህ? ለ) ለመንፈሳዊ እድገት ጠንካራ የጸሎት ሕይወት ለምን ያስፈልጋል? ሐ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በግላቸው የጸሎት ሕይወታቸውን በማሳደግ ከእግዚአብሔር ጋር ሁልጊዜ የሚገናኙ ይመስልሃል? ካልሆነ፣ ይሄ በግል ሕይወታቸውና በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ምን ችግሮችን ያመጣል? መ) አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከሌሎች ጋር በቡድን ሆነው መጸለይን ለምደዋል። ነገር ግን መንፈሳዊ መሆን የሚቻለው በግል ከእግዚአብሔር ጋር



ባለን ጸሎት እንደ ሆነ ተምረናል። ይህ እውነት እንደ ሆነ ታምናለህ? መልስህን አብራራ። ሠ) አብዛኛውን ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመጸለይ ይልቅ በአገልግሎት መጠመድ ለምን የሚቀልላቸው ይመስልሃል? ረ) የቤተ ክርስቲያን አባላት ከእግዚአብሔር ጋር በግል ያላቸውን ጸሎት ይበልጥ ክብደት ሰጥተው እንዲያዩት ምን ዓይነት ትምህርት መማር አለባቸው? ሰ) ከእግዚአብሔር ጋር በግል ለመገናኘት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜና በጣም በተጨናነቀ ጠባብ ቤት ውስጥ ሰዎች ሲኖሩ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንደሚቻል የሚጠቅም ምን እሳብ ትሰጣለህ?

4. በሦስተኛው ቀን ትምህርት ላይ ስለ ጸሎት የተማርካቸውን 15 ነጥቦች ከልስ። ሀ) በእነዚህ ማብራሪያዎች ውስጥ ክርስቲያኖች ጠንቅቀው የሚረዱት የቱን ይመስልሃል? ከእነዚህ ማብራሪያዎች ውስጥ ክርስቲያኖች የማይገነዘቧቸውስ የትኞቹ ይመስሉሃል? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ያሉ አማኞች ጸሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን እንዳለበት ያላቸው መረዳት እንዲጨምር ስለ ጸሎት መማር አለባቸው ብለህ የምታስባቸውን ነገሮች ዘርዝር? ሐ) ሰዎች ጸሎትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲጨብጡ በቤተ ክርስቲያናችሁ እንዴት ስለ ጸሎት ማስተማር እንዳለባችሁ በኅብረት ዐቅዱ።

# ትምህርት ሦስት

## የመጀመሪያ ቀን፡- አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዴት ይበስላል (ክፍል 3)

በጣም መንፈሳዊ በመሆኑ የተነሣ በሃይማኖት መሪዎች ዘንድ እጅግ የሚከበር በጣም የተማረ ወጣት ነበረ። ረጅም ሰዓታትን በጸሎት ያሳልፍ ነበር። አንድ ሰው የእርሱን ሃይማኖት

ካልተከተለ፣ ስደት ያስነሣባቸውና አንዳንዶችም እንዲሞቱ ከመንግሥት ጋር በመተባበር ይሠራ ነበር። ለሃይማኖቱ ባለው ቀናኢነት ይታወቅ ነበር። ነገር ግን፣ በእግዚአብሔር ዓይን፣ የጠፋና ወደ ገሃነም የሚሄድ የወንጌል ጠላት ነበር። ለመሆኑ እርሱ ማን ነው? እርሱ በኋላ ጳውሎስ በሚል ስም በመላው ዓለም የታወቀው ሳውል ነበር።

እንደ ጳውሎስ ያሉ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ የሆኑ በርካታ ሰዎች አሉ። በርካታ ሰዓታትን በጸሎትና በመዝሙር ያሳ-ልፋሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አይደሉም። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን ለመከተል ከፍተኛ ቀናኢነት አላቸው፣ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ያለውን እውነት አያውቁም። ሌሎች ደግሞ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑና አብዝተው ቢጸልዩም፣ በሕይወታቸው ውስጥ መንፈሳዊ ጥልቀት የላቸውም። ሕይወታቸው ችግር መቋቋም የማይችሉ በአሸዋ ላይ የተሠሩ ቤቶች ዓይነት ናቸው (ማቴ. 7:24-26)። ልክ ሳውል ኢየሱስን ሳይቀበል በፊት እንደነበረውና ልክ እንደ አይሁዳውያን «ቅናታቸው ያለ እውቀት ነው» (ሮሜ 10:12)።

> 1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ከአማኞች የሚበልጥ ቀናኢነት እንዳላቸው የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ። ለ) ይህ ቅንአት ያድናቸዋል? ለምን ያድናቸዋል? ወይስ ለምን አያድናቸውም? ሐ) አንዳንድ አማኞች በአምልኮ ላይ ከፍተኛ ቀናኢነት ኖሯቸው፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን በመምሰል እንዳላደጉና ችግር ሲመጣ ፈጥነው እንዴት እንደሚወድቁ ግለጽ። መ) ይህ ለምን ይሆናል?

ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕሪ የመንፈሳዊ መሪነት መሠረት እንደ ሆነ ተመልክተናል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእግዚአብሔር መንገድ መምራት ካለብን በመንፈሳዊ ባሕሪዎች መብሰል አለብን። ታዲያ ይህ ከሆነ «በመንፈሳዊ ሕይወት ለመብሰል ምን ማድረግ ያስፈልገናል?» ብለን እንጠይቃለን። ለዚህ ጥያቄ የመጀመሪያው ምላሽ የጸሎት ሰዎች



መሆን አለብን የሚለው እንደ ሆነ ተመልክተናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የሚያደርገን በጸሎት ረጅም ጊዜ መፍጀታችን አይደለም። ነገር ግን የጸሎታችን ጥራት ነው። ጸሎት ከሕያው እግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት፣ እርሱን የምንሰማበትና እንዲሁም በልባችን ያለውን ለእርሱ የምናካፍልበት ነው። ጸሎት በሕይወታችን ላይ የእግዚአብሔርን ኃይል ያስለቅቃል። ጸሎት እግዘአብሔር በእኛና በሌሎች ሕይወት ፈቃዱን እንዲፈጽም የምንጠይቅበት መንገድ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ኅብረት በመፍጠር የማይገለጥ ሕይወትን ይዞ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ አንድም ሰው የለም። ይሁን እንጂ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድንበስል ጸሎት ብቻውን በቂ አይደለም።

## 2. መንፈሳዊ ብስለት የሚመጣው ወንዶችና ሴቶች የእግዚአብሔርን ቃል ሲያውቁና ሲኖሩት ነው።

አንድ እግር ብቻ ያለው ሰው ለመራመድ እንደሚቸግረው ሁሉ፣ የጸሎት ሕይወት ብቻ ያለውም አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ ይቸግረዋል። ሌላኛው እግር የሆነው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ እድገት እንዲኖረን ያስፈልገናል። ኢየሱስ እንዳለው፣ ቃሉን እውቀው የሚከተሉት ናቸው በጠንካራ ዓለት ላይ መሠረታቸውን ያደረጉት። እንደዚያ ያሉ ሰዎች፣ ከባድ ማዕበል ቢመጣባቸው እንኳን አይነቃነቁም (ማቴ. 7:24-26)። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት፣ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ላይ መቆም እንዳለበት ተረድቷል (ሮሜ 10:2)። ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነ ቅንአትና ጸሎት አብዛኛውን ጊዜ አስገራሚ ኃይልን ያሳየናል እንጂ በሕይወት ላይ ያለውን እውነታ አያሳየንም (2ኛ ጢሞ. 3:5)።

> 2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ኢያሱ 1:7-8ን አንብብ። እግዚአብሔር ኢያሱን ወደ መረዳት ሲልከው ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሰጠው? ለ) መዝ. 1:2-3 እና 119:9ን አንብብ። ዳዊት አንድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት «የተባረከ» የሚያደርገው ምንድን ነው አለ? ከኃጢአት ምን ይጠብቀዋል? ሐ) 1ኛ

> ጢሞ. 3:2ን አንብብ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በተገናኘ ሽማግሌዎች ምን ዓይነት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው? መ) 2ኛ ጢሞ. 2:15ን አንብብ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የማያሳፍር የእግዚአብሔር ሠራተኛ እንዲሆን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሰዎች ቴፕ ወይም ሬዲዮ ሲገዙ ከዕቃው ጋር አብሮ የሚሰጣቸው የአጠቃቀም መምሪያ አለ። ያ መምሪያ ቴፕ ሪከርደሩን ወይም ሬዲዮውን ለሰውየው ጥቅም እንዴት እንደሚሰጥ ከማሳየት አልፎ የዕቃውን ዕድሜ ያረዝማል። ሰዎች ሙከራ አድርገው ሬዲዮውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ሊደርሱበት ይችላሉ። ይህ ግን የሬዲዮውን ዕድሜ ያሳጥራል። ለምሳሌ፣ መምሪያው የሬድዮውን ድምፅ እስከ መጨረሻው መክፈት ድምጽ ማጉያውን ይጐዳዋል ይላል። ሰዎች ይህንን መምሪያ ካላማንበባቸውና ካለመታዘዛቸው የተነሣ ጓደኞቻቸውን ለማስደመም ሊሉ ድምጹን እስከ መጨረሻው ይከፍታሉ። ነገር ግን ወዲያውኑ ድምጽ ማጉያው ይጐዳና የሙዚቃውም ጥራት ይቀንሳል።

በተመሳሳይ ሁኔታም የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ መኖር የምንችልበትና ራሳችንም የምንጠቀምበት መምሪያችን ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል የማናነብና የማንታዘዝ ከሆነ፣ መንፈሳዊ ሕይወታችን እያድግም፣ አመራራችንም ራሳችንንና ሌሎችን በመጉዳት ይጠናቀቃል። (ለምሳሌ፣ ሰዎች እንዲመርጡን ለንል የሐሰት ቃል ብንገባ፣ ብዙም ሳይቆይ ሕዝቡ እውነት እንኳን ብንናገር የማያምንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ከዚያ የተነሣ የአመራር ችሎታችን ይቀንሳል፣ ሰዎች መልካም ምክርን ባለመከተላቸው የተነሣ ይጐዳሉ።)

> 3ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አንድ መሪ የእግዚአብሔርን ቃል ባለማወቁ ወይም ባለመከተሉ የተነሣ ራሱንና ሌሎችን ስለጐዳበት ሁኔታ ግለጽ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ



መሪዎች ቃሉን እንዲያውቁና እንዲታዘዙ ይጠይቃል። በሙሴ በኩል፣ ነገሥታት ሁሉ ሕጉን ኮፒ አድርገው ለራሳቸው እንዲይዙት አዝዟል (ዘዳግም 17:18-20)። በዚህ መንገድ ሊያጠኑትና ሊያነብቡት የሚችሉት የግል ቅጂ ይኖራቸዋል ማለት ነው። ያንን ማድረግ ያስፈለገው በዙሪያቸው ባለ ባሕልና ትምህርት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት እንዲችሉ ነበር። እግዚአብሔር ለኢያሱ ሕዝቡን መምራት ሲጀምር ሁልጊዜ ትእዛዙን በመረዳትና በመታዘዝ ላይ እንዲያተኩር ነግሮታል። ዳዊት «በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚለውና ሌትና ቀን የሚያሰላስላት» ሰው የተባረከ እንደ ሆነ ተናግሯል። ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል አውቆ በመከተል መንገዱን ንጹሕ ያደርጋል። ጳውሎስ ለሽማግሌዎች ካስቀመጠው መስፈርት ውስጥ አንዱ «ማስተማር የሚችል» የሚለው አንዱ ነው። ጳውሎስ በተጨማሪም ረዳቱን ጢሞቴዎስን በእግዚአብሔር ፊት የማያሳፍር ሠራተኛ ሆኖ ለመገኘት የእግዚአብሔርን ቃል «እንዲያጠና» አስጠንቅቆታል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመሩ ሰዎች ትኩረታቸውን የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና በመታዘዝ ላይ እንዲያደርጉ በግልጽ ያሳያል። ሆኖም በዘመናችን፣ ትኩረታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ጥናት ላይ ያደረጉት ጥቂት መሪዎችና ጥቂት ክርስቲያኖች ናቸው። ለጸሎትና ለፈውስ ኮንፈረንስ ሲሆን፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በብዙ ደስታ ይገኛሉ። ነገር ግን ትኩረቱ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ላይ የሆነ ስብሰባ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቢጠራ፣ ጥቂት ሰዎች ብቻ ይገኛሉ። አብዛኞዎቹ ሽማግሌዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው አያውቁም፤ ሌላው ቀርቶ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ላይ እንኳ በሥነ ሥርዓት አይገኙም። መምራት ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል አያውቁም። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት እንኳን አይፈልጉም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች

ለ) የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ማጥናትን ልንማር ይገባል:: ጳውሎስ አማኞች ያልበሰሉ የሚፈልጉት «ወተት» የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል እንጂ «ሥጋውን» ባለመሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ. 3:1-3):: «ወተቱ» የጀማሪ ንባብ ነው:: ያ ጥሩ ነው፣ እግዚአብሔርም ይናገረናል:: ነገር ግን ያለ «ሥጋው» (ያም የጠለቀ እውነት ነው)፣ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ጠልቀን ማደግ አንችልም:: ማጥናት ይገባናል፣ ጥናት ደግሞ አስቸጋሪ ነው:: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ሕይወቱ ሲመዘን እንዳያፍር ከፈለገ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠና ነግሮታል:: ሕያው ቃል የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ 2ኛ ጢሞ. 2:15ን «የእግዚአብሔርን ቃል ምሥጢር በማወቅና በትክክል በማስተማር የማታሳፍር ሠራተኛ መሆንህን ለማሳየት በእግዚአብሔር ፊት <u>ትጋትህ እጥፍ ድርብ ይሁን</u>» ይለዋል:: የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት አለብን:: የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት መማር መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተን የምንጨርሰው ነገር አይደለም:: ይልቁንም፣ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን ሙሉ ልናጠናውና ይበልጥ ልንረዳው የምንፈልገው መሆን አለበት:: የእግዚአብሔርን ቃል በአንድ ደረጃ እንደ መቅሀማ ባሉ የጥናት ፕሮራሞች ልናጠና እንችላለን:: በትመማ መልክ ወይም በተለያዩ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ መጻሕፍትን በመግዛት በጥልቀት ልናጠና እንችላለን:: እያንዳንዱ ጸሐፊ ወይም አስተማሪ የእግዚአብሔርን ቃል በተለየ መንገድ ነው የሚያየው፣ ስለዚህ ልዩ ልዩ ጸሐፊዎች የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀትና በግልጽ ለመረዳት ይጠቅሙናል::

6ኛ ጥያቄ:- ስላለፈው ዓመት አስብ:: ሀ) አንተ እንድትማርና ሌሎችን ታስተምር ዘንድ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ለማወቅ ያጠናህበትን መንገድ ዘርዝር:: ለ) በሚመጣው ዓመት የእግዚአብሔርን ቃል



ለማጥናት እንዴት ነው ጊዜ የምትጨምረው? የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ለማጥናት ምን ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራሞችን ትቀላቀላለህ?

ሐ) እግዚአብሔር በቃሉ ለገለጠልን ነገር ታዛዥ መሆን አለብን:: ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት የሚገለጠው መንፈሳውያን ለሆኑት ብቻ እንደ ሆነ ገልጿል (1ኛ ቆሮ. 2:6-16):: መንፈስ ቅዱስ የእግዚእብሔርን እውነት የሚገልጠው እግዚአብሔርንና ቃሉን በመታዘዝ ለሚኙት ብቻ ነው:: ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና፣ እግዚአብሔር የሚናገረንን ለመታዘዝ ልንስጥ ይገባል:: እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚገባንና እንዲናገረን ከመፍቀድና ለመታዘዝ ከመስማማት ይልቅ የራሳችንን ነገር ለመሥራት የምናቅድ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እኛን መናገር ያቆማል:: እውቀታችንንም ሰይጣን በውስጣችን ኩራትን ለመፍጠር ይጠቀምበታል (1ኛ ቆሮ. 8:1-3):: በድንጋይ ላይ እና በአሸዋ ላይ የተመሠረቱ ቤቶች ልዩነት አብዛኛውን ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃል ማወቅ አይደለም:: ይልቁንም፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝና እግዚአብሔር በቃሉ የሚናገረውን በመከተል ነው:: በመንፈሳዊ ብስለት የምናድገው ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥና መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያሳየንን በመታዘዝ ነው:: በሕይወታችን ውስጥ እያወቅን እግዚአብሔርን ያልታዘዝንባቸው ነገሮች ካሉ በመንፈስ ቅዱስ አልተሞላንም ማለት ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላን ደግሞ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግ አንችልም::

7ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሕይወትህን የለወጡና እስከ ዛሬም የምትታዘዛቸውን እግዚአብሔር በቃሉ ያሳየህን እውነቶች ዘርዝር:: ለ) እግዚአብሔር በቃሉ ያሳየህን ነገር ግን የማትታዘዘውን ወይም አብዛኛውን ጊዜ የማትታዘዛቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ሐ) ለምንድን ነው አንዳንድ እውነቶች ከሌሎች የበለጠ ለመታዘዝ የሚያስቸግሩት? መ) እንታዘዛቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያሳየንን ነገሮች ባንታዘዝ ኢየሱስ የሕይወታችን ጌታ ይሆናል? መልስህን አብራራ:: ሠ) በጥያቄ «ለ» ላይ ስለጠኸው ምላሽ ጸልይ:: ኃጢአትህን ተናዘዝና ትታዘዘው ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጠይቀው::

**መ. እግዚአብሔር የሰጠንን እውነቶች ልናስላስል ይገባል** (መዝ. 1:2)። ማስላሰል ማለት ስለ አንድ እውነት በጥልቀት ማሰብና በሕይወታችን ላይ ሊሠራ የሚችልበትን መንገድ መፈለግ ነው። ልክ ቀን ስትግጥ የዋለችውን ሣር ሌሊቱን ሁሉ መልሳ ስታመነዥግ እንደምትውል ላም እንደ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንዴት በሕይወቱ ላይ መሥራት እንደሚችል በጥልቀት ሳያስብና ሳያስላስል በእግዚአብሔር ቃል እውቀት በጥልቀት ያደገ ማንም የለም። መጽሐፍ ቅዱስን በፍጥነት ካነበብን፣ ወይም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ እውነታዎችን ብቻ መረዳት ከፈለግን፣ በጣም በትንሹ ነው የምናድገው። በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት መማር አለብን። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር አድልዎን ይጠላል (ያዕቆብ 2:1--9)። በዚህ እውነት ላይ ስናስላስል፣ በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ላይ አድልዎ የሚታይባቸውን የተለያዩ ነገሮች እናስታውሳለን። በብሔር የሚደረግ አድልዎ፣ በኢኮኖሚ የሚደረግ አድልዎ፣ በቆዳ ቀለም የሚረግ አድልዎ፣ በትምህርት ደረጃ የሚደረግ አድልዎ፣ ለቤተሰብ አባለት የሚደረግ አድልዎ፣ ወዘተ. . . ይታየናል። እያንዳንዱን አድልዎ ስንፈትሽ፣ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች በሕይወታችን አድልዎ ያደረግንባቸውን ክፍሎች ለይተን ለማወቅ ራሳችንን ጥያቄ መጠየቅ እንጀምራለን። ከዚያም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በመወሰን እንዲህ ያሉ መድልዎዎች በሕይወታችን እንዳይቀጥሉ እናደርጋለን። ስለ እግዚአብሔር እውነቶች በጥልቀት ካላሰብን አንለወጥም። አስተሳሰባችንና አኗኗራችንን ካልለወጥን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሳል አንሆንም።

8ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ ጠዋት ካነበብከው የእግዚአብሔር ቃል እውነት አንዱን ውሰድና «አስላስለው»። ሀ) እውነቱ በሕይወትህ ሊሠራ የሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች ምንድን ናቸው? ለ) እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንድትኖር እውነቱ ተጽዕኖ የሚያመጣባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶች ግለጥ? ሐ) በእግዚአብሔር ቃል ስመራመድ በሕይወትህ ልትቀይራቸው የሚገባህን መንገዶች ግለጽ?



**ሠ. ከእግዚአብሔር ቃል ቁልፍ የሆኑ እውነቶችን በቃል ማስታወስ አለብን** (መዝ. 119:11)። ዳዊት የሚነግረን የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ከሸሸግን በሕይወታችን የሚመጣውን የኃጢአት ፈተና ማለፍ እንደምንችል ነው። ሰይጣን ሲፈታተነው፣ ኢየሱስ የሚያስታውሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመጥቀስ ነው የሰይጣንን ፈተና ድል ያደረገው (ማቴ. 4:4፣7)። ሰይጣንን «ከምንቋቋምበት» ዋና ዋና መንገዶች አንዱ ሰይጣን ፈተናውን ሲያመጣ ለዚያ የሚሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስታውሶ መጥቀስ ነው (ያዕቆብ 4:7፤ 1ኛ ጴጥ. 5:9)። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ. 10:3-5 አሳብን ሁሉ «እየማረክን» ይላል። ስለ መንፈሳዊ ነገሮች በማሰብ፣ በተለይም ከእግዚአብሔር ቃል ስለ ወጡ ነገሮች በማሰብ ነው አስተሳሰባችንና ተግባራችንን የምንለውጠው። አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሥራ ቦታና ወደ ትምህርት ቤት መጽሐፍ ቅዱሳችንን ይዘን ለመሄድ አንችልም። መጽሐፍ ቅዱሳችንን በልባችን «መያዝ» አለብን። መንፈስ ቅዱስም በቃል ያጠናውን ቃል ወስዶ በተለያየ ሁኔታ ይሠራበታል። በቃል ያጠናነውን ቃል ወስዶ የሚያሳዝን ነገር ሲገጥመን ያጽናናናል። ወይም በኃጢአት ስንፈተን መንፈስ ቅዱስ በቃል ያጠናነውን ቃል ወደ አእምሮአችን አምጥቶ ከኃጢአት ፈተና «እምቢ» የማለትና በድል የመውጣት ችሎታ ይሰጠናል። በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ቁልፍ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል በመደበኛነት በቃል ማጥናት ነው። (ፊልጵ. 4:8 ላይ ያለውን ጳውሎስ እውነትና ንጹሕ የሆነውን ብቻ እንድናስብ የሰጠውን መመሪያ ተመልከት።)

9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በየጊዜው በቃልህ ታጠናለህ? ለ) በቃልህ የምታውቃቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዘርዝር። ባለፉት ጊዜአት መንፈስ ቅዱስ እነዚያን ጥቅሶች ወስዶ አንተን ለማጽናናት ወይም ከኃጢአት ለመጠበቅ እንዴት እንደ ተጠቀመባቸው ግለጥ? ሐ) ልታስታውሳቸው የሚገቡህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዘርዝር። በመጪው ዓመት እነዚያን ጥቅሶች በምን ዓይነት ሁኔታ በቃልህ ለማጥናትና በልብህ ለመሸሸግ ያወጣኸውን ዕቅድ ዘርዝር።

***ማጠቃለያ፡-*** መንፈሳዊ ብስለት ሂደት ነው። ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ ሊበስል አይችልም። ይልቁኑም፣ በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓቶች መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ይሠራል፣ ልምድን መለወጥ ባሕሪን ይለውጣል፣ ያም መንፈሳዊ ብስለትን ያመጣል። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለመለወጥ የሚጠቀምባቸው ሁለት ዋነኛ መሣሪያዎች ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል ጥናት ናቸው። ሁለቱም በጣም አስፈላጊና ሊመጣጠኑ የሚገባቸው ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ሁልጊዜ ለመገናኘት እርሱን ለመስማትና ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል ጥናትን «ልማዳችን» ልናደርገው ይገባል።

ነገር ግን በመንፈሳዊ ብስለት እንድናድግ እግዚአብሔር የሰጠን ሌሎች መሣሪያዎችም አሉ።

**3. «ጾምን» ለመንፈሳዊ ዕድገት መሣሪያ እድርገን ከተጠቀምን መንፈሳዊ ብስለታችን ይጨምራል።** በታሪክ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በሙሉ ለመንፈሳዊ እድገት ጾም አስፈላጊ መሆኑን ተረድተዋል። ነገር ግን ጾም በተሳሳተ መንገድ ለመረዳት እጅግ የቀረበና ጥሩ መሣሪያ መሆኑ ቀርቶ ሰዎችን ኩራት ውስጥ ለመጨመር ሰይጣን ሊጠቀምበት ይችላል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጾም ምን እንደሚመስልና ለመንፈሳዊ ዕድገት እንዴት እንደሚረዳ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጾም የሚከተሉትን ያስተምራል፡-**

ሀ. ጾም ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዲከተሉት የምታስገድደው ሥርዓት አይደለም። ይልቁንም፣ ለአንድ ዓላማ አንድ ሰው ወይም የተወሰኑ የአማኞች ቡድን በምርጫቸው የሚያደርጉት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለጾም የወሰናቸው ቀናት፣ ሳምንታት ወይም የበዓል ቀናት የሉም። እንደዚህ ያሉ ጾሞችን ማድረግ ይፈቀዳል፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች በተወሰኑ ቀናት፣ ሳምንታት ወይም በዓመቱ የተወሰኑ ክፍሎች በሚደረጉ ጾሞች የሚያገኙት ጥቅም አለ። ነገር



ግን ክርስቲያኖች ራሳቸውን እንዲህ ካሉ የጾምን ዋንኛ ምክንያት ባለማስታወስ ከሚደረጉ ልማዶች መጠበቅ አለባቸው። ሽማግሌዎች ቅዳሜ ሌሊትን ቢጾሙ ጥሩ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የሚጾሙበትን ምክንያት ሳያስታውሱ በልማድ ከመጾም ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ጾም የተወሰኑ የምግብ ዓይነቶችን መተው እንደ ሆነ አያስተምረንም። ይልቁንም፣ ጾም ለተወሰነ ጊዜ ምንም ዓይነት ምግብ አለመብላት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰኑ ቀናት ዓሣ መብላታችንን እና የሌሎች እንስሳት ተዋጽኦዎችን አለመጠቀማችንን ጾም ልንል የምንችልበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለውም። እንደዚያ ዓይነት አመለካከት ጾሙ ለመንፈሳዊ እድገት ያለውን ዓላማ እንድንረዳ ከማገዝ ይልቅ የኩራትን ስሜት ሊያሳድግ ስለሚችል አደገኛ ሊሆን ይችላል።

ሐ. ጾም፣ ምንም ዓይት ምግብ አለመብላትም ይሁን ወይም ከባለቤታችን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለማድረግንም ቢያካትት፣ የጾም ዓላማ አይደለም። ይልቁንም፣ የጾም ተቀዳሚ ዓላማ የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ነው። የተለመደውን ሕይወታችንን ከቀጠልን ከጾም የምናገኘው ጥቅም በጣም አነስተኛ ነው። ጾም ይዘን ሥራ የምንገባ ከሆነ፣ ቴሌቪዥን የምናይ ከሆነ፣ ከጓደኞቻችን ጋር ጊዜ የምናጠፋ ከሆነ፣ ጾማችን የሚኖረው ዋጋ ጥቂት ይሆናል።

መ. ጾም ለእግዚአብሔር የምናቀርበው «ጉቦ» አይደለም። ጾም እግዚአብሔር ማድረግ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ የምናስገድድበት መሣሪያ አይደለም። ጾምን እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲመልስልን የምናስገድድበት መሣሪያ አድርጎ ሰይጣን ከሚዋሽው ነገር ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል።

ሠ. አማኞች ሊጾሙ የሚችሉባቸው ቢያንስ ሦስት ዋነኛ ምክንያቶች አሉ፡-

1) ራሳችንን መቆጣጠርና ለሥርዓት መገዛትን እንድንማር የሚረዳን መሣሪያ ነው። በጾም የመብላት ፍላጎታችንንና የፍትወት ፍላጎታችንን መቆጣጠር እንማራለን። በፈቃደኝነት እነዚህን ጥሩ ነገሮች በማቆም፣ የራሳችንን ፍላጐት መቆጣጠሩን በመማር ለጸሎት፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትና ለማሰላሰል ለጊዜው ተወት እናደርጋቸዋለን (1ኛ ቆሮ. 7:2-5)። ጳውሎስ ራሱን ለእግዚአብሔር ስመሰጠት ትኩረቱ በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን ሥጋውን መጐሸም እንደ ተማረ ይገልጣል (1ኛ ቆሮ. 9:27)። የተፈጥሮ ፍላጐቶቻችን በእኛ ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ መቆጣጠር እስካልቻልን ድረስ በመንፈሳዊ ብስለት አናድግም። ጾም እነዚህን የተፈጥሮ ፍላጐቶቻችንን መቆጣጠርና እነርሱ እንዲታዘዙን ማድረግ የምንችልበት መሣሪያ ነው።

2) ጾም በተለመደው የኑሮ ሂደታችን ከመቀጠል ይልቅ ጊዜአችንን በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ እንድናተኩር ይረዳናል። በታሪክ ውስጥ በርካታ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከተፈጥሮ ፍላጐቶች ካስወገዱ (ለምሳሌ፣ ምግብ) እና የእግዚአብሔርን ፊት ፍለጋ ጊዜ ከወሰዱ፣ እግዚአብሔር ባልተለመደ መንገድ እንደሚገናኛቸው ያምናሉ። በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ሰዓታትን ካሳለፉ፣ የስሜት ሕዋሳቶቻቸው በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚያተኩሩ ያምናሉ። እግዚአብሔር ከልባችን ከፈለግነው እንደምናገኘው ተናግሯል (ኤር. 29:13)። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ትኩረታችንን በእግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ አድርገን ሰዓታትና ቀናትን ካሳለፍን፣ እግዚአብሔር ባልተለመደ መንገድ ይመራናል፤ በእምነታችንም በጥልቀት እናድጋለን። አንዳንድ ክርስቲያኖች ትኩረታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ለማድረግ በዓመት ለአንድ ሳምንት ያለ ምንም ምግብ ከጓደኞቻቸው ተለይተው ይቆያሉ። ታዲያ እነርሱ ሲመሰክሩ ይህ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ ትኩረት የሚያደርጉበት እንደ ሆነና ዓመቱን በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው



እንደሚረዳቸው ይናገራሉ።

3) በጣም የተለመደው የጸሎት ዓይነት ኃጢአት ስንሠራ ወይም ችግር ሲገጥመን ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደን የምንቀርብበት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ጾም አብዛኛውን ጊዜ ከንስሐ ጋር የተያያዘ ነበር። በግል ወይም በተለይ በጋራ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንደ ሠሩ የሚያሳዩበት ነው። ስለዚህ ትኩረታቸው የሠሩትን ሥራ እየተናዘዙ የእግዚአብሔርን ምሕረት መለመን ነበር። እግዚአብሔር እነርሱንና ምድራቸውን ከኃጢአታቸው እንዲፈውሳቸውና የቅጣት እጁን እንዲያነሣና በረከቱን እንዲያድስ ይማጸኑ ነበር (ለምሳሌ፣ 1ኛ ሳሙ. 7)። በእግዚአብሔር ላይ ትኩረት ለማድረግና በይቅርታው ላይ ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሳየት አይሁዳውያን ማቅ ለብሰው፣ ሳይታጠቡና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳያደርጉ ነው የሚጾሙት። ዛሬ ለእኛ ጾም የራሳችንንና የቤተ ክርስቲያናችንን ኃጢአተኝነት ለመፈተሽ የሚረዳን መሣሪያ ነው። እግዚአብሔርን ለኃጢአታችን ይቅርታን በመጠየቅና ከቅጣቱ ነፃ እንድንሆን በመለመን ላይ በማተኮር የምናሳልፈው ጊዜ ነው። እርሱን ማክበር እንድንችል እግዚአብሔር አኗኗራችንን እንዲለውጠው ራሳችንን የምንሰጥበት ጊዜ ነው።

ጾም በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲያደርግልን በምንፈልገው ነገር ላይ የምናተኩርበትም ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ቢታመም፣ እግዚአብሔር እንዲፈውሰው እንጾማለን። ወይም አዲስ ለምናሠራው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ልንጾም እንችላለን። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን አዋርደን በትጋት በፊቱ እንድንሆን ለማድረግ ሲል መልሱን ያዘገያል። የምንፈልገውን ምላሽ ወዲያውኑ ሊሰጥን ይችላል፤ ነገር ግን ያ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት አያሳድገውም። ትንሽ ቆይተን ታላቁ እግዚአብሔር እንደ «ገና አባት» (የሚፈልገውን ነገር በሙሉ ለሥጋችን ፍላጐትም ቢሆን እንኳን

ሊሰጠን እንደሚችል) ልንወስደው እንችላለን። ፈጣን ምላሾችን ዘግየት በማድረግ፣ መልካም ስጦታ በሙሉ ከእርሱ እንደሚመጣ እንድንረዳ ያበረታታናል። እንደዚሁም መልሶቹ የመጡት በጸጋ እንጂ በእኛ መልካምነት ወይም እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግልን ስለተጫንነው እንዳልሆነ ያስታውሰናል። ስንጾምና ስንጸልይ፣ በሕይወታችን ያሉ ሥጋዊ ፍላጐቶችን ስለምንረዳ ስለ እነዚያ ነገሮች መጸለይ እናቆማለን። ለመንፈሳዊ ሕይወታችንና ለእግዚአብሔር መንግሥት በጣም አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ብቻ መጸለይ እንጀምራለን።

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች የሚጾሙባቸውን ምክንያቶች ዘርዝር። ለ) ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት የጾም ምክንያቶች ውስጥ አብዛኛው ክርስቲያኖች የሚከተሉት የቱን ነው? ሐ) ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት የጾም ምክንያቶች ውስጥ ክርስቲያኖች የማይከተሉት የትኛውን ነው? መ) ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ጾምን እንደ መሣሪያ መጠቀም የምትችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? |

**4. መንፈሳዊ ብስለት የሚመጣው ቅዱስና ጻድቅ ለመሆን ራሳችንን ስንሰጥ ነው።** በዕብ. 12:14 ላይ ያለ ቅድስና ማንም እግዚአብሔርን ማየት እንደማይችል ተነግሮናል። «ቅድስና» የሚለው ቃል «መለየት» ማለት ሲሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት።

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ሁሉም አማኞች ቅዱስ ወይም «ጻድቅ» ይባላሉ፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ከማያምኑት ስለ ተለየን ነው። አማኞች ከዚያ በኋላ ከተቀሩት የዓለም ሕዝቦች የተለዩ እንደ ሆኑ ማስታወስ አለባቸው። እግዚአብሔር መርጦናል፣ ስለዚህ ከሌሎች የተለየን ልዩ ሕዝብ ነን። አማኞች በአኗኗራቸውና በተግባራቸው ዓለምን ለመምሰል ሲሞክሩ፣ እግዚአብሔር ከዓለም የተለየን እንድንሆን እንደ ጠራን እንረሳለን።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ከኃጢአት መለየት አለብን። ኃጢአት



ከእግዚአብሔር ፍላጐት ውጪ የሆነ ማንኛውም ነገር ነው። በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላና በመንፈሳዊ ብስለት ማደግ ከፈለግን፣ ራሳችንን ሁልጊዜ ከኃጢአት መለየት አለብን። የግል ኃጢአትን በተመለከተ ልክ ኢሳይያስ «ወዮልኝ እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ» (ኢሳ. 6:5) እንዳለው ዓይነት አመለካከት ሊኖረን ይገባል። ምንም ያህል ትንሽ ቢመስለንም እንኳን፣ ኃጢአትን ልንጠላ ይገባል። ፍጹም ቅዱሳን ለመሆን ልንወስን ይገባል። እናም ይህ ማለት በአመራራችን ላይ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ውስጥ የሚከሰት ኃጢአትን እንጠላለን ማለት ነው። ልክ ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ልክ እንደ አንድ ንጽሕት ድንግል አድርጐ ለማቅረብ እንደ ተዘጋጀ እንደ ተናገረው ዓይነት አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል (2ኛ ቆሮ. 11:2)።

ስለ ቅድስና ስናስብ፣ አብዛኛውን ጊዜ ትኩረታችን በጣም መጥፎ መስለው በሚታዩ ውጪአዊ ተግባራት ላይ ነው። ለምሳሌ፣ ትኩረታችን በመጠጥ፣ በዝሙት፣ ከአንድ በላይ በማግባት፣ ጫት በመቃምና በመሳሰሉት ላይ ነው። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ችግሮች እንዴት እንደምናስተናግዳቸው መመሪያ ቢሰጥም፣ ሌሎች ስውር የሆኑና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ብዙ ኃጢአቶች አሉ። ዳዊት «እነሆ፣ እውነትን ከሰው ልብ ትሻለህ፤ ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ አስተምረኝ» (መዝ. 51:6- አ.መ.ት) ይላል። ያንን ያደረገው እግዚአብሔር ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር በስውር እንኳን ባለው ግንኙነት ታማኝ እንዲሆን እንደሚፈልግ ለማሳየት ነው። ኢየሱስ በሰው ልብ ውስጥ ያለው አሳብ ከውጫዊ ነገር በላይ ሰውየውን ሊያጠፋው እንደሚችል ተናግሯል (ማቴ. 7:14-23)። በእርግጥ፣ ኢየሱስ ኃጢአታዊ አመለካከትና ከሌሎች ጋር ያለ መጥፎ ግንኙነት ከኃጢአት ሥራ ጋር እኩል እንደ ሆነ አስቀምጧል (ማቴ. 5:27-30)። በ2ኛ ቆሮ. 12:20-21 ላይ ጳውሎስ እንደ ጥል፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፣

አብሪትና ሁከት ያሉ ነገሮችንና ክፉ የምንላቸውን እንደ አለመቀደስና ዝሙት የመሳሰሉትን የተለመዱ ኃጢአቶች ብሎ ዘርዝሯል:: በመንፈሳዊ ብስለት ማደግ ከፈለግን፣ እግዚአብሔር፣ ምንም ያህል ለእኛ ትንሽ ቢመስለንም፣ ኃጢአትን እንደሚጠላ ልንረዳ ይገባል:: እርሱ ትንሽ ውሸትንም ሆነ ዝሙትን እኩል ይጠላል:: ሐሜትንም ከስካራምነት እኩል ይጠላል:: በሕይወቱ እያወቀ ትንንሽ ኃጢአቶችን እየሠራ ንስሐ ሳይገባና እነዚያን ትንንሽ ኃጢአቶች ሳያሸንፍ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ የሚችል ሰው የለም:: ያዕቆብ እንዳለው፣ ከሕጎች ትንሿን የሚተላለፍ፣ «ሕግን ተላልፏል::» ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት በትልልቅ ኃጢአቶች እንደሚጐዳው ሁሉ በትንንሽ ኃጢአቶችም ይጐዳል (ያዕቆብ 2:8-11)::

11ኛ ጥያቄ:- ሀ) እቅልሰን የምናያቸውን ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ጋሬጣ የሆኑብንን «ትንንሽ» ኃጢአቶች ዘርዝር:: ለ) ከእነዚህ «ትንንሽ» ኃጢአቶች ውስጥ አንዳንዴ የምትደጋግማቸው ነገር ግን መጥፎ እንደ ሆኑ የምታስባቸው ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው? አሁኑኑ በእነዚህ ኃጢአቶች ላይ ንስሐ በመግባት በእነርሱ ላይ እግዚአብሔር ድል እንዲሰጥህ ጠይቅ:: ሐ) በየትኛው መንገድ ነው «ትንንሽ ኃጢአቶች» በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚያስቀጡት ትልልቅ ኃጢአቶች በላይ በግል ሕይወትህና በቤተ ክርስቲያንህ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉት?

ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ እንዲሆኑ ሲመረጡ መስፈርቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መሆን እንዳለበት ተመልክተናል:: መንፈስ ቅዱስ ሥጋዊ የሆኑና በሕይወታቸው ያልተናዘዙትና ያልተመለሱበት ኃጢአት ያለባቸውን ሰዎች አይሞላም:: በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሁልጊዜ በሕይወታችን ቅዱስ እንድንሆን ይጠይቃል::

<u>ሦስተኛ፣</u> ቅዱስ መሆን ማለት ለእግዚአብሔር ሥራ መለየት ማለት ነው:: ከኃጢት ነፃ መሆን ብቻውን በቂ አይደለም:: ቅዱስ



መሆን ማለት ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት ነው:: እርሱ ስለ ዋጀን ለእርሱ እንገባለን (1ኛ ቆሮ. 6:20):: ስለዚህ፣ በልባችን የምናደርገው በሙሉ ለእርሱ ክብር መሆን አለበት ብለን እንወስናለን:: ከዚያ በኋላ የምንኖረው ራሳችንን ለማስደሰት ሳይሆን፣ የዋጀንን ለማስደሰት ይሆናል (2ኛ ቆሮ. 5:14-15):: እግዚአብሔር እንድናደርግ የጠየቀንን ነገር ማድረግ አለብን::

እነዚህ ሦስት ዓይነት ቅድስናዎች በሕይወታችን እውን ሲሆኑ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንበስላለን፣ እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አመራር ሊጠቀምብን ይችላል::

መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ እግዚአብሔርን ማስደሰት ከፈለግን ጻድቅ እንድንሆን ይናገረናል:: ጻድቅ መሆን ማለት እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ማለት ነው:: ነቢዩ ሚክያስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሲናገር እግዚአብሔርን ማስደሰት ካለባቸው «ፍትሕን እንዲያደርጉና ምሕረትንም እንዲወድዱ» (ሚክያስ 6:8) ይነግራቸዋል:: ያዕቆብ ደግሞ፣ እውነተኛ ሃይማኖተኝነት እንደበትን መጠበቅ፣ ድሆችን ማለትም ባሎቻቸው የሞቱባቸውንና ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን መንከባከብን እንደሚጨምር ይናገራል (ያዕ. 1:26-27):: ስለዚህ ከኃጢአት መሸሽ ብቻውን በቂ አይደለም፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ መሥራትና እርሱ ከእኛ የሚፈልገውን ነገር መሥራት ይኖርብናል::

12ኛ ጥያቄ:- በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግና ለቤተ ክርስቲያን አመራር ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉ ነገሮችን መለስ ብለህ ቃኝ:: ሀ) የጸሎት ሰውና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነብ ሰው ለመሆን በምን ዓይት ሁኔታ ጊዜህን ማመጣጠን እንደምትችል ጥልቅ የሆነ ዕቅድህን ግለጥ:: ለ) ለሚቀጥለው ወር፣ ምን ያህል ጊዜህን በእግዚአብሔር ቃል ንባብና በጸሎት ላይ እንዳሳለፍክ መዝግብ:: ይህ መዝገብህ ሕይወትህ እንዴት የተመጣጠነ ስለ መሆኑ ምን ያስተምረሃል? ሐ) የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረው እውነተኛ ቅዱስና ጻድቅ ሰው በመሆን ላይ ትኩረት ማድረግ የሚቻልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ቅዱስና ጻድቅ የመሆን ፍላጎትህ ልማድና በኋላም የሕይወትህ ባሕሪ ሊሆን ይችላል?

## 5. መንፈሳዊ ብስለት የሚመጣው እንደ መደበኛ የሕይወት ዘይቤ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ነው (ኤፌ. 5:18)::

> 13ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 5:1-21ን አንብብ:: ሀ) 1) ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስለሚያጠቃልላቸው ነገሮች በተለምዶ ምን ምን ያስባሉ? 2) አንድ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን እንዴት ነው የሚያገኘው? 3) የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአንድ ሰው ውስጥ ስለ መኖሩ የሚሰጠው ማረጋገጫ ምንድን ነው? ለ) ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላትና ራሱን እንዴት እንደሚገልጥ ምን ማሳያ ሰጥቷል? ሐ) መንፈሳዊ ብስለት ለማምጣት መንፈስ ቅዱስ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? መ) በአንድ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? ሠ) ገላ. 5:16-26ን አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላትና ስለ መሪ ባሕሪ ምን ያስተምራሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት ብቻ ለመሪነት እንደሚመረጡ ያስተምራል (የሐዋ. ሥራ 6:3):: ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ባልተሞላና በእርሱ ቁጥጥር ሥር ባልሆነ መሪ የምትመራ ከሆነ፣ ያ ሰው የእግዚአብሔርን ሕዝብ በራሱ ጥናካሬና ጥበብ ነው የሚመራው:: መንፈስ ቅዱስ ከዚያ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በተሞሉ መሪዎች አይመራትም:: ራስ ወዳድና በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ያልሆኑ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን በመሯት ቁጥር፣ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈልገውን ማሟላት አይችልም:: እንደዚያ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቷ መሞት ትጀምራለች:: መንፈስ ቅዱስ ዓለማዊ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲያጋጥሙት፣ የእርሱን ፈቃድ እንዲፈጽሙ አያስገድዳቸውም:: ይልቁንም፣ በጸጥታ በመሄድ በራሳቸው ጥንካሬ እንዲመሩ ይተዋቸዋል:: ነገር ግን መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሲሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ለመሪዎች ይሰጣል:: ጥበቡን በመስጠት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ይነግራቸዋል:: መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ሰዎች አልፎ ቤተ ክርስቲያንን ይመራል::



በተለምዶ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ሲያስቡ፣ ትኩረታቸው በሐዋርያት ሥራ 2 ወይም በሐዋርያት ሥራ 10 ላይ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ በታላቅ ኃይል ወርዶ በልሳን እንዲጸልዩ ስላደረጋቸው ነገር ነው:: እነዚህ ታሪኮች በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ በሆኑ ክርስቲያኖች ላይ ምን እንደሚሠራ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው ይላሉ:: ሆኖም፣ የሐዋርያት ሥራን በግልጽ ያነበበ ሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሲመጣ ሁልጊዜም በአማኞች ሕይወት እንደዚህ እንደማይሆን ይረዳል:: ይልቁንም፣ ሐዋርያት ሥራ የሚያስረዳው እንዴት መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አይሁዳውያን አማኞች ላይ እኩል እንደ መጣ ነው (የሐዋ. ሥራ 2)፣ የሰማርያ ሰዎች (የሐዋ. ሥራ 8)፣ አሕዛብ (የሐዋ. ሥራ 10):: እነዚህ ታሪኮች በቀዳሚነት የሚያስተምሩት ያኔ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተለመደ የነበረው የዘር መከፋፈል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመኖሩን ነው:: በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ ከተጻፈው ክስተት ከ30 ዓመታት በኋላ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉ በልሳን እንደማይናገሩ ይገልጣል:: ይልቁንም፣ ይህ መንፈሳዊ ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ለተወሰኑ አማኞች ነው (1ኛ ቆሮ. 12:7-11፣ 28-30):: መንፈስ ቅዱስ ሌሎች መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ለሌሎች አማኞች ይሰጣል::

ኤፌ. 5:21 ስለ መሪና በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት ምን ይነግረናል?

ሀ. <u>መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ያዝዛል</u>:: ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ወይን ጠጅ ጠጥቶ ከመስከር ጋር ያነጻጽረዋል:: አንድ ሰው ወይን ጠጅ ጠጥቶ ከሰከረ፣ በወይኑ ቁጥጥር ሥር ስለሚሆን ራሱን ለመቆጣጠር አይችልም:: ቀጥ ብሎ መሄድ አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ ይወድቃል:: ከወይኑ የተነሣ ንግግሩ ይዛባል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ያለ ሰው በራሱ ኃይል ሊያደርገው በማይችላቸው ተጽዕኖዎች እንዲኖር ያደርጋል:: በተፈጥሮአችን

ራስ ወዳድ፣ ኩሩ፣ ትዕግሥት የሌለን ከእኛ ዝቅ ያሉትን የማንወድ፣ ወዘተ. . . ነን። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ስንሆን፣ ራሳችንን የማንወድ፣ ትሑት፣ ታጋሽና ጠላቶቻችንን ሳይቀር የምንወድ እንሆናለን።

ለ. <u>በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አማኞች ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች</u>። በኤፌሶን 5:18 ላይ ያለው ዐውደ ንባብ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን የሚያፋጥኑ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች እንዳሉ ይናገራል። <u>አንደኛ</u>፣ በሕይወታችን ያሉ ኃጢአቶችን ልናስወግድ ይገባል። በኤፌሶን 5:3-17 ላይ ጳውሎስ እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችንና እንደ ብርሐን ልጅነታችን ልናቆማቸው የሚገቡ ኃጢአቶችን በሙሉ ይዘረዝራል። በቧንቧ ውስጥ ያለ ቆሻሻ ንጹሕ ውኃ እንዳያልፍ እንደሚያግደው ሁሉ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በሕይወታችን ያለ ኃጢአት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳይሞላንና በሕይወታችን እንዳይፈስ ይገድባል። መንፈስ ቅዱስ መንፈሱን የሚሞላው ያልተናዘዙት ኃጢአት የሌለባቸውንና ራሳቸውን የማይወዱ ሰዎችን ነው። አንድ ጊዜ ልባችን መንፈስ ቅዱስ የሚጠላቸውን ነገሮች ካስወገደ፣ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ይሞላናል። <u>ሁለተኛ</u>፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን ኃይል ተጠቅመን ራሳችንን በቅድስናና በጽድቅ ስንመራ ነው (ኤፌ. 5:9)። በሕይወታችን ቅዱስ መሆንና ኃጢአትን ማስወገድ በቂ አይደለም። በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናውቅና ልንታዘዘው ይገባል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሌሎች ፍቅርን ማሳየት፣ በኅብረት መኖር፣ እርስ በርስ ማገልገልና፣ ድሃን መርዳትና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

(ማስታወሻ፡- አብዛኛውን ጊዜ አማኞች መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል ወደ ሕይወታችን የሚመጣው ሕይወታችንን ከኃጢአት ለናጸዳ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ታላቅ ነገር እንዲያደርግ በመፈለግ ጊዜ ስናጠፋ ነው። ልክ እግዚአብሔር



በሙሉ ልባችን ከፈለግነው እንደምናገኘው እንደተናገረው ነው (ኤር. 29:13)፣ እግዚአብሔር አንዳንዴ የመንፈስ ቅዱስን ኃይለኛ መገኘት ለመግለጥ የሚዘገየው እጅግ በጣም እስክምንፈልገው ድረስ ነው። ለአንዳንዶች ይህ ኃይል በልሳን በመናገር ይገለጣል። ለሌሎች፣ ይህ ኃይል ራሱን የሚገልጠው በጥልቀት ራስን በመስጠትና በሰላም ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህንን ያልተለመደ አንድ ጊዜ በኃይል የሚሠራውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመንፈስ ቅዱስ «ጥምቀት» ይሉታል። አንዳንዶች «የመንፈስ ቅዱስ ሙላት» ይሉታል። በጣም አስፈላጊው ነገር ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የምንጠቀመው ቃል ወይም መንፈስ ቅዱስ በምን ዓይነት መንገድ በሕይወታችን እንደ ተገለጠ አይደለም። ይልቁንም፣ ራሳችንን በሙላት ለእርሱ መስጠታችንና የእርሱ ንጹሕ መሣሪያ መሆናችን ነው። የሥጋ ፍላጐታችንንና ዐመፃችንን ሰብረን ፍጹም ወደ ሆነ መታዘዝ መምጣታችን ነው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ነፃ እንዲሆን የሚያደርገው። ያ ኃይል በራሱ ጊዜ በታላቅ ኃይል ራሱን ይገልጣል። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ያ ኃይል ራሱን በእኛ ውስጥ የሚገልጠው ኢየሱስን እንድንመስል ባሕሪያችንን በመቀየር ነው። እጅግ አስፈላጊ የሆነው ነገር በመጀመሪያ ጊዜ «መንፈስ ቅዱስ ስንሞላ» ራሱን የገለጠበት መንገድ አይደለም። ይልቁንም፣ መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ መሞላታችንና አለመሞላታችን ወይም ሁልጊዜ ሕይወታችንን መቆጣጠርና አለመቆጣጠሩ ነው። ሕይወታችን ኢየሱስን እንዲመስልና በመንፈሳዊ ነገር እንድንበስል የሚደርገን በየዕለቱ መንፈስ ቅዱስ መሞላታችን ነው።)

መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ መንፈስ ቅዱስ መሞላት ከፈለግን፣ በሕይወታችን ያሉ የምናቃቸውን ኃጢአቶች ማስወገድ አለብን። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ወደ መታዘዝ ልንወስድ ይገባል። በሌላ አነጋገር፣ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ልናስገባ ይገባል። ይህን ስናደርግ፣ መንፈስ ቅዱስ

በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ ያመጣል፡፡ እርሱ ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር እንድናደርግ መንፈስ ቅዱስ ማንነታችንንና አስተሳሰባችንን ይቆጣጠራል፡፡ እውቀታችን፣ ስሜታችን፣ ፈቃዳችንና ሰውነታችን እርሱ ዓላማውን እንዲፈጽምበት ክፍት ይሆንለታል፡፡ እርሱ ማንነታችንንና የተፈጥሮ ችሎታችንን ወስዶ በማስታጠቅ በእነርሱ ይሠራል፡፡

ሐ. <u>የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወታችን ውስጥ የሚገለጥባቸው መንገዶች፡፡</u> እግዚአብሔር በሕይወታችን ካለው መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገው ማንነታችንንና አኗኗራችንን እንዲለውጥ ነው፡፡ እርሱ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጣችንን በመቀየር ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናከብር ተግባራችንን ይለውጠዋል፡፡ ኤፌ. 5:18-33 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወታችን ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ ያሳያል፡፡ <u>አንደኛ</u>፣ መንፈስ ቅዱስ አምልኮአችንን ይለውጣል፡፡ በምስጋናና በአምልኮ ሆነን እግዚአብሔርን ስማመስገን እርስ በርሳችን እንገናኛለን፡፡ <u>ሁለተኛ</u>፣ በሕይወት ውስጥ ያለን አስተሳሰብ ከራስ ወዳድነትና ከመነጫነጭ ወጥቶ በሕይወታችን ውስጥ ምንም ዓይነት ነገር ቢመጣ የምናመሰግንበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን፡፡ <u>ሦስተኛ</u>፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ያለን ግንኙነት ይቀየራል፡፡ የራሳችንን መንገድና ፍላጐት እንተዋለን፡፡ ይልቁንም፣ በፈቃዳችን ራሳችንን ዝቅ አድርገን ለሌሎች እንሰጣለን፡፡ ወጣት ቢሆኑ ሽማግሌ፣ ወንድ ቢሆኑ ሴት ግድ አይኖረንም፡፡ በፍቅር ሌሎች ሰዎችን ማክበርና ፍላጐታቸውን ማሟላት እንጀምራለን፡፡ <u>አራተኛ</u>፣ በቤተሰብ ውስጥ ያለን ግንኙነት እግዚአብሔርን የሚያከብር ይሆናል፡፡ በባልና ሚስት መካከል የእኔ ፈቃድ መፈጸም አለበት ከሚል ትግል ወጥተው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እንደ ሰጠው ባል ራሱን ሚስቱን ለማገልገል ቢሰጥ መልካም ነው፡፡

መ. <u>መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊ ብስለት እንድናድግ እንዴት እንደሚረዳን፡፡</u> <u>አንደኛ</u>፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መቀየር በሚገባቸው የሕይወታችን ክፍሎች ላይ ትኩረት እንድንሰጥ ያደርገናል፡፡ <u>ሁለተኛ</u>፣ የመለወጥን ፍላጐት የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ <u>ሦስተኛ</u>፣ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ ያልሆኑ ልማዶችና ባሕሪዎቻችን እግዚአብሔር ወደሚፈልጋቸው ዓይነት ልማዶችና ባሕሪዎች መቀየር የምንችልበትን ኃይል ይሰጠናል፡፡ ጳውሎስ እንዳለው፣ ለመለወጥ ፈቃደኛ እንድንሆን የሚያደርገንና የሚለውጠን እራሱ እግዚአብሔር ነው (ፊልጵ. 2:12-13)፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>፡- መንፈስ ቅዱስን በመታዘዝም ሆነ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ለመሆን በእያንዳንዷ ቀን ምርጫ እናደርጋለን፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ወይ በመንፈስ ቅዱስ አልያም በሥጋችን ቁጥጥር ሥር እንሆናለን፡፡ በሥጋችን ቁጥጥር ሥር ከሆንን፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለማይረዳን ማደግ አንችልም፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ስንሆን፣ ከፈቃዱ ጋር መሄድ የሚችሉ ውሳኔዎችን እንድናደርግ ይረዳናል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ጋር የሚሄዱ ውሳኔዎችን እየወሰድን ስንሄድ፣ መንፈሳዊ ልማዳችን እያደገ ይሄዳል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ ይህ መንፈሳዊ ልምዳችን መንፈሳዊ ባሕሪያችን በመሆን መንፈሳዊ ብስለታችንን ይገልጣል፡፡

ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለመብሰል፣ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ልንኖር ይገባል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ያላከበርንባቸውን የሕይወታችንን ክፍሎች ያሳየናል፡፡ ደረጃ በደረጃ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ ያልሆኑ ልማዶችና ባሕሪዎቻችንን እግዚአብሔርን በሚያከብሩ ልማዶችና ባሕሪዎች ይተካቸዋል፡፡ ቀስ በቀስ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንበስላለን፡፡ እስክንሞትና ወደ መንግሥተ ሰማያት እስክንሄድ ድረስ፣ መንፈስ ቅዱስ ደረጃ በደረጃ እየተቆጣጠረው የሚሄደው የሕይወታችን ክፍል ሁልጊዜም ይኖራል፡፡ መንፈሳዊ ብስለት ማለት ፍጹም መሆን አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ ለሌሎች

እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እንዲኖሩ ምሳሌ የምንሆንበትና በመንፈሳዊነት የተሻለ ደረጃ ላይ የምንኖርበት ነው።

በገላ. 5:16-26 ላይ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ሁለት ተፈጥሮ እንዳለ ይናገራል። አንደኛው በእግዚአብሔር ላይ ማመፅና የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ የሚፈልግ ነው። ሌላኛው ተፈጥሮአችን እግዚአብሔርን መታዘዝና እርሱ የሚፈልገውን ማድረግ ይፈልጋል። እነዚህ ሁለት ተፈጥሮዎች ሕይወታችንን ለመቆጣጠር እርስ በርስ ይፎካከራሉ። በራሳችን ኃይልና በግላዊ ፍላጐታችን ሕይወታችንን መምራት ከፈለግን፣ ኃጢአተኛ ማንነታችን ይቆጣጠረናል። ከዚያም ሕይወታችን በዝሙት ኃጢአት፣ በሐሰተኛ አምልኮ፣ ወይም በእኛና በሌሎች ሰዎች መካከል መከፋፈልን በሚፈጥር በራስ ወዳድነት ይገለጣል። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከተሞላንና እርሱ ከተቆጣጠረን፣ አዲስ ባሕሪን ይሰጠናል። ከዚያም ሕይወታችን በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላም፣ በትዕግሥት፣ በደግነት፣ በጥሩነት፣ በታማኝነት፣ በጨዋነትና ራስን በመቆጣጠር ይሞላል። በመደበኛ ሁኔታ ሕይወትህን የሚቆጣጠረው ማን ነው?

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ፡- መንፈስ ቅዱስ ሕይወትህን እንድትመረምር እንዲረዳህ ጊዜ ወስደህ ጸልይ። ሀ) በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል? በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላትህ ምን ማረጋገጫ አለህ? ለ) በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላህ፣ ልታስወግዳቸው የሚገቡ ኃጢአቶች ወይም መንፈስ ቅዱስ እንድትሞላ ልታደርጓቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ፈቃድ ውጪ የሆኑ ልምዶችህንና ፀባዮችህን እንዲገልጥልህ ጸልይ። እነዚያን ነገሮች በወረቀት ላይ ዘርዝራቸው። መ) በሚቀጥለው ሳምንት በእያንዳንዱ ቀን በእነዚያ መንፈሳዊ በሆኑ ልምዶችና ባሕሪዎች ላይ ጸልይ። የመለወጥ ፍላጐት እንዲኖርህና የመለወጥ ኃይል እንዲኖርህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ። ሠ) እነዚህ ትክክል ያልሆኑ ልማዶችና ባሕሪዎች እግዚአብሔርን ወደሚያከብሩ ልምዶችና ባሕሪዎች እንዲለወጡ በምን ዓይነት ውሳኔና ተግባር ላይ ማተኮር አለብህ? |

## 6. መንፈሳዊ ብስለት ባሉን ጓደኞች ዓይነት ይወሰናል።



በመንፈሳዊ ብስለት ማደግ ካለብን፣ ትክክለኛ ዓይነት ጓደኞችን መምረጥ አለብን። አብዛኛውን ጊዜአችንን ከእነርሱ ጋር የምናጠፋባቸው ጓደኞቻችን በመንፈሳዊ ብስለት ለማደጋችን ወይም የዓለም ነገር አእምሮአችንንና ሕይወታችንን እንዲመራን የሚያደርጉት ተጽዕኖ አለ። ሰለሞን «ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፤ የተላሎች ባልንጀራ ግን ጉዳት ያገኘዋል» ብሏል (ምሳሌ 13:20፣ በተጨማሪም ምሳ. 22:24-25፤ 24:1፤ ምሳ. 1:13 ተመልከት)። ጊዜአችንን በመንፈሳዊ ብስለታቸው ለማደግ ከማይፈልጉ ሰዎች ጋር የምናጠፋ ከሆነ፣ በመንፈሳዊ ብስለት እናድግም። ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚወዱና በሙሉ ልባቸው ሊከተሉት የሚፈልጉ ሰዎችን ከመረጥን፣ እኛም በሕይወታችን እርሱን የምንወድና እርሱን ልናከብረው የምንፈልግ ሰዎች እንሆናለን።

በመንፈሳዊ ብስለት እንድናድግ የሚረዳን መንፈሳዊ ጓደኞች ማበጀታችን ብቻ አይደለም። ጓደኞቻችን በመንፈሳዊ ብስለት እንድናድግ እንዲረዱን በሕይወታችን ያሉ መንፈሳዊ ያልሆኑና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አብረው የማይሄዱ ነገሮችን እንዲያሳዩን ልናበረታታቸው ይገባል። ሰሎሞን እንደ ተናገረው፣ «ብረት ብረትን እንደሚስል፣ ሰውም ሌላውን ሰው እንደዚሁ ይስለዋል» (ምሳሌ 27:17፣ 27:9ን ተመልከት)። አብዛኛውን ጊዜ የራሳችንን ድካም ማየት አንችልም። ነገር ግን ሌሎች ሊያዩዋቸው ይችላሉ። ማደግ ካለብን፣ ድካማችንን የሚያሳዩንና እንድናድግ የሚረዱን ጓደኞች ያስፈልጉናል።

(ማስታወሻ፡- ሁላችንም በተለያየ ደረጃ ያሉ ጓደኞች ያስፈልጉናል። ለምሳሌ፣ የምንመሰክርላቸው ያልዳኑ ጓደኞች ሊኖሩን ይገባል። በዚህ ወዳጅነታችን ግን፣ በእነርሱ አስተሳሰብና የአኗኗር ተጽዕኖ ውስጥ ላለመውደቅ መጠንቀቅ ይኖርብናል። በተጨማሪም ከአማኞች ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያምኑ ጓደኞችም ሊኖሩን ይገባል። ከእነርሱ ጋር መሆን መንፈሳዊ

ሕይወት እንድንመራ ይረዳናል። በመጨረሻም፣ ሁላችንም በጣም የሚውቁንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የሚገፉፉን ጥቂት ጓደኞች ያስፈልጉናል።)

> 15ኛ ጥያቄ፡- የጓደኞችህን ስም ዘርዝር። ሀ) ከእነርሱ ጋር መሆኑ ደስ የሚልህ፣ ነገር ግን በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ የማይረዱህን ጓደኞች ዘርዝር። ከእነዚህ መንፈሳዊ ዕድገትህን ከሚያሰናክሉ ጓደኞችህ ጋር ያለህን ጊዜ መገደብ ያስፈልግህ እንደ ሆነ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቅ። ለ) ለመንፈሳዊ ዕድገትህ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸውን ጓደኞችህን ዘርዝር። ሐ) መንፈሳዊና ጥበበኛ የሆኑ በቤተ ክርስቲያናችሁ ስለሚገኙ ሰዎች አስብ። በመንፈሳዊ ብስለት ለማደግ እንዲረዳህ እንዴት ነው ጊዜህን ከእነርሱ ጋር የምታሳልፈው? መ) አንድ ወይም ሁለት የቅርብ ጓደኞችን ምረጥ። በሕይወትህ የሚገኝና እነርሱ የእግዚአብሔር ፍላጉት አይደለም የሚሉትን ነገር ጠይቃቸው። በመንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ ከአንተ ጋር እንዲጸልዩ ጠይቃቸው።

## ሁለተኛ ቀን፡- ለመንፈሳዊ አመራር የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 1)

ምን ማድረግ እንደምንፈልግ ግልጽ የሆነ አሳብ ከሌለን፣ የሚረባ ነገር ማድረግ አንችልም። በመንፈሳዊ ብስለት ማደግ የእንጨት ቁራጭን ወንዝ ውስጥ ከትቶ ምንም ሳያደርግ እንዲንሳፈፍ እንደ ማድረግ አይደለም። ይልቁንም፣ እንደ ማረስና መዝራት ነው። ገበሬ መቼና የት ምን ዓይነት ሰብል መዝራት እንዳለበት ዕቅድ ያወጣል። ከዚያም በትክክለኛው ጊዜ እንዲደርስለት መሬቱን በርትቶ ያርሳል። በመጨረሻም ዘሩን መሬቱ ላይ መዝራት አለበት። እንድ ጊዜ ያንን ካደረገ፣ በኋላ እግዚአብሔር ነው ዘሩ እንዲያድግና እንዲያፈራ ዝናብ እያዘነበ የሚንከባከበው። በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ዓይነት መሪ ለመሆን ምን ዓይነት ባሕሪን ማሳደግ እንዳለብን ማወቅ ይገባናል። ሕይወታችንም በጸሎት መታረስ አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ዘሩን መዝራት አለብን።



መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያደናቅፉ አረሞችንም መንቀል ይገባናል። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በልባችን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ባሕሪ እንዲፈጠር ይሠራል፣ ያንንም በመሪዎቹ በኩል በዓለምና በቤተ ክርስቲያን ላይ ልዩነት ለማምጣት ይጠቀምበታል።

> 16ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጢሞ. 3፡1-12፣ ቲቶ 1፡6-9፣ 1ኛ ጴጥ. 5፡1-4ን አንብብ። ሀ) ለሽማግሌዎችና ለዲያቆናት የሚያስፈልጉ መንፈሳዊ መስፈርቶችን ዘርዝር። ለ) እያንዳንዱን ባሕሪ ተርጉም። ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርሱ እንደሚፈልገው ለመምራት እያንዳንዱ መልካም ባሕሪ ለምንድን ነው የሚያስፈልጋቸው? መ) በሽማግሌዎች ሕይወት ውስጥ እነዚህ መልካም ባሕሪዎች ካልታዩ በሽማግሌዎቹ አመራር ላይ ምን ይከሰታል? ሠ) ለሽማግሌዎች በተሰጠውና ለዲያቆናት በተሰጠው መስፈርት መካከል ምን ዓይነት ልዩነት አለ?

ጳውሎስ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ፣ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚመሯት መሪዎች ጥራት አሳስቦት ነበር። በእግዚአብሔር መንገድ የማይመሩ በርካታ መሪዎች እንዳሉ ያውቅ ነበር። እነዚህ መሪዎች እማኞች በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ከመርዳት ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን ይጎዱ ነበር። ስለዚህ ጢሞቴዎስና ቲቶ በኤፌሶንና በቀርጤስ ያሉ ቤተ ክርስቲያናትን ሄደው እንዲጎበኙና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ የሚመሩ መሪዎችን እንዲመርጡ ላካቸው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ምን ዓይነት መሪ መመረጥ እንዳለበት በጥንቃቄ ገልጧል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲመሩ ከሚፈልጋቸው መሪዎች የሚጠበቁትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሪዎችን ለመምረጥ በጣም መጠንቀቅ ነበረባቸው። ጴጥሮስም በተጨማሪ ለሽማግሌነት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለነበራቸው ቤተ ክርስቲያናት ጽፏል።

ጴጥሮስና ጳውሎስ ለሽማግሌዎችና ለዲያቆናት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ሲዘረዝሩ መሪዎች ሊኖሯቸው በሚገቡ መንፈሳዊ መስፈርቶች ወይም ባሕሪዎች ላይ ነው ትኩረት ያደረጉት። እነዚህን መስፈርቶች ስንመለከት የሚከተሉትን ልናይ እንችላለን፡-

1. ስመሪነት የሚያስፈልጉት አብዛኛዎቹ መስፈርቶች የተመሠረቱት ውጪአዊ ከሆነ የትምህርት ደረጃ፣ ከታዋቂነት፣ ከሐብታምነትና ከመሳሰሉት ነገሮች ይልቅ በመንፈሳዊ ባሕሪና በመንፈሳዊ ብስለት ላይ ነው። ትኩረታቸው አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን ባሉበት ነገር ላይ እንጂ፣ ምን እንደሚሠራ አይደለም። ሽማግሌ የሚሠራውን በተመለከተ የተቀመጠው ብቸኛ ው መስፈርት «ማስተማር የሚችል» የሚለው ነው።

2. እነዚህ ባሕሪዎች የሚያስፈልጉት ለመሪዎች ብቻ አይደለም። ሁሉም ክርስቲያኖች እነዚህ መስፈርቶች ያስፈልጉአቸዋል። ሆኖም፣ መሪዎች እግዚአብሔር ሁሉም ልጆቹ እንዲሆኑለት የሚፈልገውን የሚያሳዩ ሞዴሎች በመሆናቸው (1ኛ ቆሮ. 11:1)፣ ሁሉም መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት እነዚህ መስፈርቶች ያስፈልጓቸዋል።

3. በ1ኛ ጢሞቴዎስ፣ በቲቶና በ1ኛ ጴጥሮስ ላይ ከተጻፉት ዝርዝሮች ውጪ ስለ መሪዎች ብቃት የተጻፉ መስፈርቶች አሉ። እነርሱን በሚቀጥለው ሳምንት እንመለከታቸዋለን።

4. ዛሬ ትኩረት ያደረግንባቸው አብዛኛዎቹ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን አመራር መስፈርቶች በዚህ አልተጠቀሱም። ለምሳሌ፣ ማንበብና መጻፍ ስለሚችል መሪ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስለ ተማረ መሪ፣ ወይም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለ ተማረ መሪ ምንም የተጻፈ ነገር የለም። እነዚህ መሪዎች የመንግሥት ሥልጣን ያላቸው ወይም ህብታሞች መሆን እንዳለባቸው የተጠቀሰ



ነገርም የለም። በዘመናችን ለመሪነት የሚያስፈልገው ትምህርትና ህብት ከሆነበት አሠራር ጋር ሲነጻጸር ይሄ እንዴት የተለየ ነው። ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ በሆነው ልብ ላይ ማተኮር ትተን በውጪአዊ ነገር ላይ ስናተኩር ልክ እንደ ሳሙኤል ሆነናል (1ኛ ሳሙ. 16:6-7)።

5. ይህ ለመሪዎች የተዘጋጀ መስፈርት የሚናገረው ልዩ በሆኑ ሦስት የመሪው የሕይወት ክፍሎች ላይ ነው፡- ሀ) በግል ሕይወቱ፣ ለ) ከቤተሰቡ ጋር ባለው ግንኙነት፣ እና ሐ) ክርስቲያን ካልሆኑት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ናቸው። መንፈሳዊ ሰው መሆን በራሱ ብቁ አይደለም፣ ነገር ግን መሪ ከቤተሰቦቹና ከማያምኑት ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። መንፈሳዊ ባሕሪው ከቤተሰቡ ጋር ባለው ግንኙነትና እርሱን ከሚመለከተው ማኅበረሰብ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ማምጣት አለበት።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ በሰውየው ልብና ባሕሪ ላይ ማተኮር ትተን በውጫዊ መስፈርቶች ላይ የምናተኩረው ለምንድን ነው? ለ) አንድ መሪ በ1ኛ ጢሞ. 3 ላይ ጳውሎስ የጻፈው ባሕሪ ቢጐድለው ነገር ግን ውጫዊ መስፈርቶችን ቢያሟላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ችግር ይከሰታል? ሐ) ከውጪአዊ መስፈርት ይልቅ በባሕሪ ላይ ይበልጥ እንድናተኩር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ የሚመረጥበትን መንገድ ለመለወጥ ምን ማድረግ አለብን? |

ጳውሎስና ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንን ለሚመሩ ሰዎች የዘረዘሩት መስፈርት በንጽጽር የሚያቀርበውን ሠንጠረዥ እጥና።

| 1ኛ ጢሞቴዎስ 3 -ሽማግሌዎች | 1ኛ ጢሞ.3 - ዲያቆኖች | ቲቶ 1 - ሽማግሌዎች | 1ኛ ጴጥሮስ 5- ሽማግሌዎች |
|---|---|---|---|
| ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ/ የአገልጋይ ልብ ያለው | | | እንደ ባሪያ ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነና የሚጓጓ |
| የማይነቀፍ | | በደል የሌለበት/ ትክክለኛ | |
| የአንዲት ሚስት ባል | | የአንዲት ሚስት ባል | |
| ልከኛ | | | |
| ራሱን የሚገዛ | | ራሱን የሚገዛ/ ጨዋ | |
| ሊከበር የሚችል | አክብሮት የሚገባው | | |
| እንግዳ ተቀባይ | | እንግዳ ተቀባይ | |
| ማስተማር የሚችል | | በቃሉ ሌሎችን የሚያጽናና፣ ሐሰተኛ አስተማሪ ዎችን የሚቃወም | |
| የማይሰክር | ብዙ ወይን የማይጠጣ | የማይሰክር | |
| ጨዋ | | በመፀኛ ያልሆነ በቀላሉ የማይናደድ፣ | |
| የማይጣላ | | ንዴቱን መቆጣጠር የሚችል | |
| ገንዘብን የማይወድ | ለረብ የማይላሳ | ነውረኛ ረብ የማይወድ | ለገንዘብ የማይስስት |
| ቤተሰቡን በሚገባ የሚያስተዳደር | | የሚያምኑና የሚታዘዙ ልጆች ያሉት | |
| አዲስ አማኝ ያልሆነ | | | |



| | | | |
|---|---|---|---|
| በውጭ ባሉት ዘንድ ጥሩ ዝና ያለው | | | |
| | እውነተኛ | | |
| | የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚያምን | የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን የሚያምን | |
| | | መልካም የሆነውን የሚወድ ቅዱስ | |
| | | | ኃይልን ከመጠቀም ይልቅ በምሳሌ የሚመራ |

ከዚህ ሠንጠረዥ እንደምንረዳው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን አመራር ያለው መስፈርት አንድ ብቻ አይደለም። እያንዳንዳቸው ተ መሳሳይነት አላቸው፣ ነገር ግን ከሌሎች ይለያሉ። ጴጥሮስና ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሳል መሆን እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል። ጳውሎስ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰለ ሰው «የማይነቀፍ» ወይም «ነቀፋ የሌለበት» ነው ይላል። በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ መሪዎች ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት አላቸው። ቅዱስ ናቸው፣ ለሌሎች ደግ ናቸው፣ ያውቃሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራሉ፣ ልጆቻቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ ያስተምራሉ። እንዲሁም በገንዘብ ጉዳይ ላይ ጠንቃቆች ናቸው።

በጣም የሚያስገርመው በሽማግሌዎችና በዲያቆናት መካከል ያለው የመስፈርት ልዩነት፣ ሽማግሌዎች እውነቱን የሚያውቁ፣

ማስተማር የሚችሉና የሐሰት አስተማሪዎችን የሚቃወሙ መሆን ሲገባቸው፣ ዲያቆናት ግን እውነቱን ብቻ እንዲያምኑ ነው የሚጠበቅባቸው። በተረፈ ግን ከእነርሱ የሚፈለገው ባሕሪ ከሽማግሌ ከሚፈለገው ጋር አንድ ዓይነት ነው። በአዲስ ኪዳን ላይ በግልጽ እንደሚታየው፣ ዲያቆናት ወንበር ለማመላለስ ፈቃደኛ የሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጸዱ ወይም መባ የሚሰበስቡ ብቻ አይደሉም። መንፈሳዊ ባሕሪ ማሳየት የሚያስፈልገው ጠቃሚ አገልግሎት አላቸው። አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳዮች እነርሱን የሚመለከቱ ሲሆን፣ ሽማግሌዎች ደግሞ አማኞችን መንፈሳዊ በሆነ መንገድ የማስተማራት ኃላፊነት አለባቸው።

እስኪ ጴጥሮስና ጳውሎስ ለሽማግሌዎች (ኤጲስ ቆጰስ) ለሚባሉትና ለዲያቆናት ስለ ጠቀሷቸው ልዩ ባሕርያት እናጥና። የመንፈሳዊ ባሕሪን መሠረት ለማጥናት 1ኛ ጢሞ. 3ን እንጠቀማለን።

## በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለመሪነት ሁኔታዎች የሚያስፈልጉ መሠረቶች (ዳራዎች)

ከሙሴ ዘመን ጀምሮ፣ አይሁዳውያን ይመሩ የነበሩት «ሽማግሌዎች» በሚባሉ ቡድኖች ነው (ዘኍል. 11:16-17ን ተመልከት)። ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ አይሁዳውያን በምርኮ ሲበታተኑ፣ ምኩራቦቻቸውን በመሠረቱባቸው በእያንዳንዳቸው ከተሞች ሁሉ፣ የሚመሯቸውን ሽማግሌዎች ይመርጡ ነበር። እነዚህ ሽማግሌዎች በምኩራቦች ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርትና አምልኮ ይቆጣጠሩ ነበር፣ የብሉይ ኪዳን ትምህርቶችን የማያከብሩ አይሁውያንን ይቆጡና ይገሥጹ ነበር፣ አስፈላጊ ሲሆንም በአይሁዳውያን መካከል የሚነሡ አለመግባባቶችን በመፍታት ጉዳዮቹ ወደ ፍርድ ቤት እንዳይሄዱ ያደርጋሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች ይመረጡ የነበረው በጥበባቸውና አይሁዳውያንን እንደ አባት ሆነው ለመቆጣጠር ፈቃደኛ በመሆናቸው ነበር።



የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ስታድግ፣ የአይሁዳውያንን ልማድ ወስደው ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት የሚቆጣጠሩ ሽማግሌዎችን መረጡ። ልክ እንደ አይሁዳውያን ሁሉ፣ እነዚህ ሽማግሌዎች የሚታወቁት በባሕሪዎቻቸውና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲከተል መምራት በመቻላቸው ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ትምህርትና አምልኮ ይቆጣጠራሉ። ያፈነገጡ ክርስቲያኖችን ይቀጣሉ። በአማኞች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ይፈታሉ።

ምንም እንኳን በተለምዶ በየአጥቢያው ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «ሽማግሌዎች» ቢባሉም፣ «ኤጲስ ቆጰስ»ም ይባሉ ነበር። ጳውሎስ «ኤጲስ ቆጰስ» የሚለውን ቃል በመጠቀም ሁለት ዋና ዋና ትርጉሞችን ማስተላለፍ ፈልጓል። አንደኛ፣ ኤጲስ ቆጰስ ሌሎችን የሚቆጣጠር ነው። ስለዚህ ኤጲስ ቆጰስ እግዚአብሔር የሕዝቡን መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጐት እንዲቆጣጠር ኃላፊነት የሰጠው ሽማግሌ ነው። ሁለተኛ፣ «ኤጲስ ቆጰስ» በራሱ ምንም ሥልጣን የሌለው ለራሱ ጥቅም የማይሠራ ነው። ይልቁንም፣ ኃላፊነቱ የሚሰጠው በሌላ ሰው ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለዚያ ሰው ነው። የሚሠራው ለዛ ሰው ጥቅም ነው። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጰስ በራሱ ምንም ሥልጣን የለውም። ይልቁንም፣ የእርሱ ሥልጣን የሚመጣው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የሚያገለግለውም ለራሱ ጥቅም ሳይሆን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነው (ማስታወሻ፦ «ኤጲስ ቆጰስ» የሚለው ቃል ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ እንደ ነበረው የተወሰነ የመልክአ ምድር ክልልን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚሰጥ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣን ሹመት አይደለም። ስለዚህ ቃሉን ኦርቶዶክሶች ወይም ካቶሊኮች እንደሚጠቀሙበት ልንረዳው አይገባም።)

አዲስ ኪዳን ሽማግሌና ኤጲስ ቆጰስ የሚሉትን ቃላት እያቀያየረ ነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በበላይነት የሚቆጣጠሩ ሰዎችን

የሚጠራው (ቲቶ 1:5፣ 7ን ተመልከት)። «ሽማግሌ» የሚለው ቃል የሚያተኩረው በተከበሩ፣ አብዛኛውን ጊዜ ሽማግሌ በሆኑ የማኅበረሰቡ ሰዎች ላይ ነው። «ኤጲስ ቆጶስ» የሚለው ቃል ደግሞ በሽማግሌዎቹ ሥራ ላይ ያተኩራል። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መንፈሳዊ ቁጥጥር እንዲያደርጉ በእግዚአብሔር አማካኝነት የተሰጣቸው ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ በአዲስ ኪዳን፣ «መጋቢ» የሚለው ቃል የተጠቀሰው ስለዚህ የመሪነት ክፍልም ነው። በተለይም በሙሉ ጊዜአቸው የቤተ ክርስቲያንን አባላት በማስተማር የሚያገለግሉትን ነው (ማስታወሻ፡- ይህንን በዚህ የት.መ.ማ. መጽሐፍ ክፍል ሦስት ላይ እናጠናዋለን)።

ጳውሎስ 1ኛ ጢሞቴዎስን በጻፈበት ወቅት፣ በኤፌሶን የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በአመራራቸው የደከሙ ይመስላል። ከብዙ ዓመታት በኋላ ጳውሎስ ሁሉንም አንድ ላይ ጠርቶ ቤተ ክርስቲያንንና የእግዚአብሔርን መንጋ ከሐሰት ትምህርት ስለ መጠበቅ አስፈላጊነት አስጠነቀቃቸው። (የሐዋ. ሥራ 20:28)። ምናልባት ያንን አላደረጉ ይሆናል። ስለዚህ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አዳዲስ ሽማግሌዎችን እንዲመርጥ ወደ ኤፌሶን ላከው። ጢሞቴዎስ ለሽምግልና ትክክለኛ ሰው እንዲመርጥ ለመምራት፣ ጳውሎስ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን መንጋ ከሚቆጣጠሩ ኤጲስ ቆጳሳት የሚፈለገውን መንፈሳዊ መስፈርት ገልጦለታል።

## ለቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚያስፈልጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶች

**1. አገልጋይነት፡- አንድ ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በፈቃደኝነት ለማገልገል የሚፈልግና ዋጋ የሚከፍል መሆን አለበት፡-** ላይመሳሰል ቢችልም፣ በ1ኛ ጢሞ. 3:1 ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመሪ ባሕሪ ተገልጧል። ይህም ለሌሎች ብሎ የራስን ሕይወትና ምቾት የመሠዋት ባሕሪ ነው። ኢየሱስ ታላቁ



ፍቅር የሚገለጠው አንድ ሰው ለሌሎች ሲል ራሱን ሲሠዋ እንደ ሆነ ገልጧል (ዮሐ. 15:12-13)። የቤተ ክርስቲያን መሪነት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል የራሳችንን ሕይወት፣ ምቾታችንና ፍላጎቶቻችንን መተው ነው። በጣም ከፍተኛ የሆነ መሥዋዕትነትን ስለሚፈልግ፣ በዚህ መንገድ ማገልገል የሚፈልጉ ብቻ መሪዎች መሆን ይገባቸዋል።

ቤተ ክርስቲያን እንደ መሪዎች ማገልገል በማይፈልጉ ሰዎች ክፉኛ ተጎድታለች። ያለ ፈቃዳቸው ወይም በቸልታ በመሪነት የሚያገለግሉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሽማግሌነትን አገልግሎት አይፈጽሙም። ወደ ስብሰባ የሚመጡት ሲመቻቸው ብቻ ነው፣ ወይም ሲሠሩም በተቻላቸው መጠን ትንሽ ብቻ ለመሥራት ይሞክራሉ። ቦታውን ይዘው ሌሎች እግዚአብሔርን ማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች እንዳያገለግሉ በር ይዘጋሉ። አብዛኛውን ጊዜ የሚመሩት ልክ እንደ ዓለም በኃይልና በሥልጣን እንጂ በትሕትናና በታጋሽነት አይደለም። ብዙ የተሻለ ውጫዊ ብቃት ያላቸውና ባላቸው ኃይል ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥራት የማይፈልጉ ብዙ መሪዎች ከሚኖሩን ይልቅ በጣም ጥቂት ባላቸው ኃይል ሁሉ እግዚአብሔርን ማገልገል የሚፈልጉ መሪዎች ቢኖሩን ይሻላል። ለዚያ ነው ጳውሎስና ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን አመራር ሕዝቡን በሽምግልና/ በእረኝነት/ ለማገልገል ለሚፈልጉ ሰዎች እንጂ መሪ እንዲሆኑ ለተገደዱ ሰዎች እንዳልሆነ ያመለከቱት። መምጣት ያለበት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ማገልገል ከሚፈልግ ልብ ነው።

> *18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ለአገልግሎት የሚሆን ጊዜ ሳይኖረው ወይም አገልግሎት ሳይፈልግ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ እንዲሆን ስታስገድደው ስላየህበት ጊዜ ግለጥ። ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ዓይነት ጉዳት አምጥቷል? ሐ) አንድ ሰው ተገድዶ ከሚያደርገው ይልቅ በፈቃዱ ሽማግሌ እንዲሆንና የእግዚአብሔር ጥሪ ያለው መሆኑ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?*

ጳውሎስ እንድ ሰው ኤጲስ ቆጳስ ቢሆን መልካምን ተመኝቷል ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ለመረዳት፣ ጳውሎስ ስለ አመራር ያለውን መረዳት ማወቅ ያስፈልጋል:: በተለምዶ መሪ መሆንን መፈለግ ጥሩ አይደለም፣ ምክንያቱም መሪ መሆን የምንፈልገው በራስ ወዳድነት ተነሣሥተን ነው፤ እንደ ደረጃ፣ ክፍያ፣ ወይም ክብር፣ ወይም እነዚህን ለመሳሰሉት ለሌሎች ጥቅሞች ነው:: ግን እግዚአብሔር፣ «የቤተ ክርስቲያን መሪ እንድትሆንልኝ እፈልጋለሁ:: ሕዝቤ እንዲያድግና እንዲቀደስ በመርዳት እንድታገለግለኝ እፈልጋለሁ» እለህ እንበል:: በእርግጥ እግዚአብሔር ስለ ጠየቀህ ክብር ይሰማሃል:: ነገር ግን፣ «አስተውል፣ መሪ ለመሆን ከፈለግህ፣ በዚህ ዓለም ላይ በቂ ክፍያ አይኖርህም:: ወደ መንግሥተ ሰማያት እስክትሄድ መጠበቅ አለብህ:: በጣም ረጃጅም ሰዓቶችን የሚፈጁ ስብሰባዎች ይጠብቁሃል:: እንተን ከማክበር ይልቅ፣ ብዙ ሰዎች በአንተ አመራር ያጉረመርማሉ:: ቤተሰብህ ከአንተ ጋር የሚሆንበት ጊዜ ይናፍቀዋል:: የግል ሥራህ ይጐዳል:: ለሰዎች እንዴት አድርገህ እንደምታገለግላቸው ሳትናገር ሽንት ቤት ማጽዳት ቢሆን፣ ወንበሮችን መደርደር ቢሆን፣ ወለሉን መወልወል ቢሆን፣ ማንኛ ውንም ዓይነት ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን አለብህ:: በአጭሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት ሰዎች ባሪያ መሆን አለብህ፣ እነርሱም አብዛኛውን ጊዜ እንደ ባሪያ ይቆጥሩሃል:: ጠላት ቤተ ክርስቲያንን ሲያሳድድ ሲመጣ፣ በእምነትህ የተነሣ በመጀመሪያ እሥር ቤት የምትገባውና የምትሞተው አንተ ትሆናለህ:: የእኔ አገልጋይ ለመሆንና ሽማግሌ ለመሆን ፈቃደኛ ነህ?»

ወይም በዚህ መንገድ እናስቀምጠው፣ ስንቶቻችን ነን ሽማግሌ ለመሆን የምንፈልገው? ጳውሎስና ጴጥሮስ ሽማግሌ የመሆን መሻት ከትክክለኛ የልብ ፍላጐት መመንጨት አለበት፣ ይኸውም በግል ሕይወት ላይ አደጋ ወይም እለመመቸትን ቢያጋጥም እንኳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው::



ኢየሱስ እንዳለው፣ ታላቅ አገልጋይ የሌሎች ሰዎች ባሪያ ለመሆን ፈቃደኛ የሆነው ነው (ማቴ. 20:25-28):: እንደዚያ ያለ ውሳኔ ማለት ራሳችንን ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሥዋዕት ማድረግ ነው::

መሥዋዕትነት የቤተ ክርስቲያን አመራር ልብ ነው:: ከዓለማውያን በተለየ መልኩ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ በመሆን የሚገኘው ጥቅም ትንሽ ነው:: ለማነቃቂያ የሚሆን ጥቅም ብንፈልግ፣ እንደ ክብር፣ ዝና፣ ኃይል፣ ክፍያና የመሳሰሉትን ብንፈልግ፣ እስካሁን ድረስ እንደ ዓለም ነው የምንመራው ማለት ነው፣ እናም መጨረሻችን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መጉዳት ነው:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለእርሱና ለሌሎች ሰዎች ሕይወታችንን እንድንሰጥ ሲጠይቀን፣ በሕይወታችን ምንም ዓይነት ሽልማት ካልጠበቅን፣ የአገልጋይ ልብ አለን ማለት ነው:: እናም የእግዚአብሔር አገልጋይ ምንም እንኳን በዚህ ሕይወቱ ጥቅም ላያገኝ ቢችልም፣ በሚመጣው ሕይወት ግን ታላቅ ሽልማት አለው (1ኛ ጴጥ. 5:4):: የቤተ ክርስቲያን መሪነት መፍሰስ ያለበት ከአገልግሎት መሻት፣ ሌሎች ሲያድጉ ከማየትና ችግራቸውን ከመፍታት ፍላጎት ነው:: እግዚአብሔርን ማገልገል የሚችሉት የአገልጋይነት ባሕሪ ያላቸው ብቻ ናቸው:: ይህ መሻት አለህ? ያ ከሆነ በአመራር ቦታ ላይ መቀመጥን መፈለግህ ጥሩ ነው:: በዚያም ሌሎችን ራስን ባለመውደድ ልታገለግል ትችላለህ::

| |
|---|
| 19ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብዛኞዎቹ መሪዎች የመሪነት ቦታቸውን ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ይረዳሉ? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) መሪነት ሌሎችን «ከመምራት» ይልቅ የሌሎች «ባሪያ» መሆኑን የምንረዳ ሽማግሌዎች ከሆንን በአስተሳሰባችንና በአመራራችን ላይ የሚመጣው ልዩነት ምንድን ነው? ሐ) መሪዎች ከመሪነታቸው ጥቅም ከማግኘት ይልቅ ሚናቸውን እንደ ሌሎች አገልጋይ አድርገው ቢመለከቱ በሕይወታቸውና በአመራራቸው የሚመጣውን ልዩነት ግለጥ:: |

**2. ነቀፋ የሌለበት (በደል የሌለበት፣ ቀና):-** በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ከሁሉ በላይ የመሪው መልካም ዝና ወሳኝ ነው:: ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ዝና የሚለኩት በቤተ ክርስቲያን መሪው ዝና ነው:: በእርግጥ፣ የክርስትናን እውነትነት የሚለኩት በመሪው ባሕሪ ነው:: የማያምኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሲኖር ሲያዩ፣ ብዙ ጊዜ «ክርስትና እንዲዚህ ከሆነ፣ አልፈልገውም» ይላሉ:: ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሕዝቡ የተከበሩ መሆን እንዳለባቸው ይናገራል፣ ያም ለቤተ ክርስቲያንና ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን ያመጣል::

«ነቀፋ የሌለበት» ማለት ሰዎች ሲክሱት የሚችሉበት ምንም የተሳሳተ ነገር የሌለው ማለት ነው:: የግሪኩ ቃል «ስሕተት ሲሠራ የማይገኝ» ነው የሚለው:: መሪ ነቀፋ የሌለበት ባሕሪ እንዲኖረውና በባሕሪው ውስጥ ሌላ ሰው ሊጠቁም የሚችለው ምንም ዓይነት ችግር የሌለው ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር የሚያጎድፍ ምንም ነገር የለውም:: ሕይወቱ በጣም ንጹሕ ከመሆኑ የተነሣ መስታወት ላይ ጭቃ እንደ መወርወር ይመስላል:: ጭቃው ይንሸራተታል እንጂ መስታወቱ ላይ ተጣብቆ አይቀርም:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መሪውም ንጹሕና ማንኛውም ክስ በላዩ ላይ ተጣብቆ የሚቀር ሳይሆን በፍጥነት ተንሸራትቶ የሚወድቅና ነቀፋ የሌለበት መሆን አለበት::

ሽማግሌዎች ልክ እንደ ዳንኤል መሆን ይኖርባቸዋል:: ሰዎች ሕይወቱን፣ አመራሩን የገንዘብ አያያዙን፣ እና የመሳሰሉትን ሲመረምሩ፣ እግዚአብሔርን ከመመስሉ በቀር ምንም ዓይነት ነቀፋ አላገኙበትም (ዳን. 6:1-5):: በተመሳሳይ መንገድ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምንም የተደበቀና የታወቀ ዕለት የእርሱንና የቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚያሳጣ ነገር ሊኖረው አይገባም:: ምንም ዓይነት አድልዎና ገንዘብን ያለአግባብ መጠቀም፣ ምንም ዓይነት ውሸት፣ ምንም ዓይነት የግል መሻትና ምንም ዓይነት ሰዎች እርሱን የሚከስሱበትና ጥፋተኛ ሆኖ የሚያገኙበት ነገር መኖር



የለበትም::

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብዛኛዎቹ መሪዎች ዝናውን የሚያጕድፍ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማጣራት ሕይወታቸው በጥንቃቄ እንዲመረመር የሚፈልጉ ይመስልሃል? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) የመሪዎች ዝና መጉደፍ ለቤተ ክርስቲያንና ለክርስቶስ ውርደትን እንዴት እንደሚያመጣ ግለጥ:: |

ብዙ ምሁራን ጳውሎስ «ነቀፋ የሌለበት» የሚለውን ባሕሪ እንደ ርእስ ወይም መሪዎች ሊሆኑ የሚገባቸው ዋነኛው መስፈርት አድርጐ እንደ ተጠቀመበት ያምናሉ:: ሌሎች ባሕሪዎች በሙሉ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ያለ ነቀፋ መሆን የምንችልባቸው ምሳሌዎች ናቸው::

## እግዚአብሔርን የሚያስከብር ትዳር መመሥረት

ሀ. የአንዲት ሚስት ባል የሆነ:- በዚህ መስፈርት ውስጥ ሦስት ዓይነት አሳቦች አሉ:-

አንደኛ:- መሪ አንድ ሚስት ብቻ ሊኖረው ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔር የሰጠውን አንድ ወንድ አንድ ሚስት የሚለውን ትዳር በምሳሌነት ማሳየት አለበት:: ብዙ የሚያገባ ሰው መሆን የለበትም:: ብዙ ባሕሎች የተለያዩ ልምምዶች ቢኖራቸውም፣ እግዚአብሔር ያቀደው ትዳር አንድ ለአንድ ነው:: ይህም ማለት ከአንድ በላይ ሚስት ያለው ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን አይችልም ማለት ነው::

ሁለተኛ:- የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በተመለከተ ባል ለሚስቱ ታማኝ መሆን አለበት:: ከሌሎች ሴቶች ጋር ዝሙት የሚፈጽም መሆን የለበትም::

ሦስተኛ:- ባልና ሚስት እግዚአብሔር ያቀደውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ጋብቻ ምሳሌ ናቸው:: አንድ ሰው ሚስቱን የሚያየው እንደ አጋዥ ነው:: ያም እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሲፈጥር ካቀደው ጋር የሚስማማ ነው:: ሚስቱን እንደ

ባሪያና ወይም የበታች እንደ ሆነች አድርጎ አይመለከትም:: ይልቁንም፣ አንድ ሰው ሚስቱን ማየት ያለበት ልክ እንደ አቻ ተጣማሪ ነው፣ ያም ልክ ሁለት በሬዎች ለአንድ ዓሳማ ቀንበር እንደሚጫንባቸው ነው:: እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ሲፈጥር የተለያዩ ዓይነት ቢያደርጋቸውም፣ ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል የተሠሩና የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወርሱ ናቸው (ዘፍጥ. 1:27፤ 1ኛ ጴጥ. 3:7ንም አንብብ):: ጴጥሮስ ባሎች ሚስቶቻቸውን ካላከበሩ፣ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደማይሰማ ያስጠነቅቃቸዋል:: ጳውሎስ ደግሞ በባልና ሚስት መካከል ያለው መፋቀርና የእርስ በርስ መስጠት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት ምሳሌ እንደ ሆነ ይናገራል (ኤፌ. 5:22-23)::

ይህ ባሕሪ በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ተጻፈ በጳውሎስ ዓይን ምሳሌ የሚሆን ትዳር በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: ትዳር የማንኛውም ማኅበረሰብ መሠረት ነው:: ትዳር ሲፈርስ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሰላም አይኖርም:: ወላጆች ሌሎችን ማክበር ምን ማለት እንደ ሆነ በቤታቸው ውስጥ በምሳሌነት ካሳሳዩ፣ ልጆች ከማኅበረሰቡ ጋር ሲቀላቀሉ ሰዎችን አያከብሩም:: እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ትዳሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥም በጣም አስፈላጊ ናቸው:: በመላው ዓለም፣ ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉት ከ16 ዓመታቸው በፊት ነው:: ስለዚህ መንፈሳዊ ነገርን በከፍተኛ ደረጃ የሚቀበሉ ወጣቶች ናቸው:: ከሁሉም በላይ መንፈሳዊ ነገርን የሚቀበሉ ደግሞ የአማኞች ልጆች ናቸው:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ እግዚአብሔር ከአማኞች የሚወለዱ ልጆች ልዩ እንደ ሆኑ ተናግሯል:: ሚልክያስ 2:15 ላይ እግዚአብሔር ትዳርን የሚያከብርበት አንድ ምክንያት መንፈሳዊ ከሆኑ ቤተሰቦች መንፈሳዊ የሆኑ ልጆች እንዲወለዱ ነው:: ጳውሎስም ወላጅ መልካም የሆነ መንፈሳዊ ተጽዕኖ በልጅ ላይ ስለሚያመጣ ልጁ



አማኝ የመሆን ዕድሉ የሰፋ እንደ ሆነ ተናግሯል:: ስለዚህ ያላመነች ሚስት ያለው ወይም ያላመነ ባል ያላት ሴት፣ በትዳራቸው በመቆየት ለትዳር ተጣማሪዎቻቸውና ለልጆቻቸው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት መመስከር አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 7:14)::

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ምሳሌ የሚሆን ትዳር ያላቸው ይመስልሃል? ለምን? ለ) አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምሳሌ የሚሆን ትዳር አላቸው? ከሌላቸው፣ እንዴት ነው አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገው ዓይነት ትዳር ሳይኖራቸው የቀረው? |

ጳውሎስ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን የግድ ማግባት አለበት አላለም:: ያ ከሆነ፣ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ያላገቡ በመሆናቸው፣ ለአመራር አይበቁም ነበር (1ኛ ቆሮ. 7:7- 8፣ 9:5):: ጳውሎስ እንዲያውም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በተለይም ወንጌላውያንና የቤተ ክርስቲያን ተካዮችን ወንጌልን ያለምንም መሰናክል ለመስበክ እንዳያገቡ ያበረታታቸዋል (1ኛ ቆሮ. 7:1፣ 32-35):: ያለማግባት የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆንን የሚከለክል ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ ይህንን መመሪያ አይሰጥም ነበር:: ሆኖም፣ ጳውሎስ አብዛኛዎቹ ሰዎች እንደሚያገቡ ያውቃል:: እናም የሚያገቡ ከሆነ፣ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አባላት ምሳሌ የሚሆን ትዳር ሲመሠርቱ ይገባል::

## በእግዚአብሔር መንገድ እንድንመራ የሚያደርጉ አዎንታዊ ባሕሪዎች

**ለ. የማይቆጣ:-** ይህ ቃል ማለት «ረጋ ማለት፣ እና ጠንቃቃ፣ እና ጥበባዊ ጥንቃቄ የሚያደርግ ማለት ነው::» ግሪኮች ይህን ቃል የሚጠቀሙት በችግር ውስጥ ለሚረጋጋ ሰው ነው:: በግብታዊነት ነገሮችን አይሠራም:: በጣም ንጹሕ የሆነ አዕምሮና የተመጣጠነ አስተሳሰብ አለው:: የሚያይበት አቅጣጫ መጽሐፍ ቅዱስን

መሠረት ያደረገና ወደ ጽንፈኝነት ያልሄደ ነው። ከቁጣ ወደ መረጋጋት፣ ከድብርት በአንድ ጊዜ ወደ ሐሴት፣ ወዘተ. . . ቶሎ የመምጣት ስሜታዊነት የለበትም። መሪው ሕዝቡ ለእርሱ ያላቸውን ክብር የሚቀንስ ምንም ዓይነት ልማድ አይኖረውም።

**ሐ. ራስን መቆጣጠር፡-** ይህ የሚያሳየው አንድ ሰው እንደ እግዚአብሔር መመሪያ ለመኖር ሲል ራሱን መቆጣጣር መቻሉን ነው። በስሜቱ ቁጥጥር ሥር አይወድቅም ወይም በሌሎች ሰዎች አመለካከት አይነዳም። ራሱን የሚቆጣጠር መሪ ተፈጥሮው ሁሉ በእግዚአብሔርና በቃሉ ቁጥጥር ሥር በመሆኑ ልማዶችና የሰዎች አስተሳሰብ አይቆጣጠረውም። ይህንን አሳብ በ1ኛ ቆሮ. 3:27 ላይ ጳውሎስ በኃጢአት እንዳይወድቅ አካሉን እንደሚጎሽም ከተናገረው ንግግር ላይ እናያለን።

ለመንፈሳዊ ዕድገት ራስን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርን ለማግኘት ለመጸለይና ቃሉን ለማግኘት ስንል የመተኛት ፍላጎታችንን በመቆጣጠር በጠዋት እንነሣለን ማለት ነው። ይህ ማለት የፍተወት ፍላጎታችንን እንቆጣጠራለን ማለት ነው። ይህ ማለት እንዳንቆጣና በሁኔታዎች እንዳንወሰድ በስሜታችን ላይ የበላይነት አለን ማለት ነው።። ጊዜአችንን ከጓደኞቻችን ጋር ተቀምጠን ስናወራ ከመዋል ይልቅ በሚጠቅመን ነገር ላይ ለማዋል የጊዜ አጠቃቀማችንን እንቆጣጠራለን። ራሱን የሚቆጣጠር ሰው ለሚፈጠሩ ችግሮች ሌሎችን ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ ለነገሮች ኃላፊነትን ይወስዳል። ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግ ማለት እኛ ከቁጥጥር ውጭ እንደ ሆንን ማሳወቅ ነው። አንድ ሰው ሲናገር ብዙ መሪዎች በአመራር ላይ የሚወድቁት ከአመራር ችሎታ ችግር ይልቅ ራስን መቆጣጠርን ስላልተማሩ ነው ብሏል።

> 22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ራስን መቆጣጠር እንዴት የመንፈሳዊ ዕድገትና የመንፈሳዊ አመራር መሠረት እንደ ሆነ አብራራ። ለ) በሕይወትህ ውስጥ ራስህን መቆጣጠር የማትችለው ክፍል የትኛው ነው? ሐ) በሕይወትህ ውስጥ ራስህን መቆጣጠር የተማርክባቸው የትኞቹ ክፍሎች ናቸው? መ) ስሜታዊነትህን ወይም ሌሎች ከሚቆጣጠሩህ ይልቅ ራስህን መቆጣጠርን ለመልመድ ምን ማድረግ አለብህ?

**መ. የተከበረ፡-** በግሪኩ፣ ይህ ቃል የሚያመለክተው ከሌሎች ጋር ባለው ነገር ሁሉ መልካም ሥነ ምግባር ያለውና የተከበረ ሰውን ነው። በራስ ወዳድነት ዝም ብሎ የራሱን ደስታ የሚፈልግ ሳይሆን ለሌሎች የሚያስብ ነው። በአለባበሱና በተግባሩ ሰዎች የክብር ሰው አድርገው ይሥሉታል። መሪ ራስን መቆጣጠር በማዳበሩ፣ በደመ ነፍሱና በፍላጎቱ ሁሉ ራሱን የሚገዛ ነው። ይህ ደግሞ ወደ የሚከበር ሰውነት ይወስደናል፣ በውስጡ ያለው ራስን መቆጣጠር ውጪአዊ ሕይወቱን ውብ ያደርገዋል። «መሪ በልቡ የክርስቶስ ኃይል የነገሠበትና በሕይወቱም የክርስቶስ ውበት የሚያንጸባርቅበት ሰው መሆን አለበት።»

**ሠ. እንግዳ ተቀባይ፡-** እንግዳ ተቀባይነት በጣም አስፈላጊ የሆነ የሽማግሌ አገልግሎት ነው። ይህ ደግ የመሆን ቀጣይ ክፍል ነው። በዚህ ውስጥ የተጠቃለሉ ሁለት ዓይነት የእንግዳ ተቀባይነት ደረጃዎች እሉ፡-

<u>አንደኛው</u>፣ ሽማግሌ ለእንግዶች በሩን በመክፈት ደግነቱን ማሳየት አለበት። ለሌሎች ሲል ምቾት ማጣትን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለበት። ይህ በተለይ እንደ ዛሬ በብዙ ገጠራማ ቦታዎች ሆቴል ባልተስፋፋበት የአዲስ ኪዳን ዘመን በጣም አስፈላጊ ነበር። በከተሞች የሚገኙ ሆቴሎች ደግሞ ርኩሰትና የሥነ ምግባር ጉድለት የሚታይባቸው ነበሩ። ስለዚህ ክርስቲያኖች ከቦታ ቦታ እየተጓዙ የሚስተምሩ መምህራንና ድሆችም፣ እንዲሁም እማኞች ቤት አድራሰሁ ብለው ይተማመኑ ነበር። ይህ እማራጭ የተሰጠው ሌሎች እማኞች ጋር ማደር ካልተቻለ ነበር። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነታቸው፣ ሽማግሌዎች ለሚጓዙ አማኞች ቤታቸውን በመክፈት የደግነት ምሳሌ መሆን አለባቸው። (ማስታወሻ፡- ሰዎችን በእንግድነት መቀበል ለሆቴል የሚሆን ገንዘብ የተሰጣቸው ሀብታም

አማኞች ለሆቴልና ለምግብ የሚሰጣቸውን ኪሳቸው ከትተው በድሃው ሕዝብ ላይ ገንዘብ እንዲያተርፉ ለማድረግ አይደለም የታቀደው። ያ ፍቅር አይደለም። ፍቅር የሌሎች ሰዎችን ምቾት በመቀነስ የግል ጥቅም ማግኘት አይደለም። የሆቴል እየተከፈለን ሌሎች ክርስቲያኖች ቤት በእንግድነት ለማረፍ ከፈለግን፣ ገንዘቡን ለራሳችን ከማስቀረት ይልቅ እነርሱን የምንረዳበት መንገድ መፈለግ አለብን።)

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሽማግሌ የቤተ ክርስቲያን አባላትን የሚጠብቅ እረኛ በመሆኑ፣ ቤቱ ሁልጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲመጡና እንዲጫወቱ ክፍት መሆን አለበት። ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ወደ ሽማግሌው ቤት ሲመጡ ቤተኝነት ሊሰማቸው ይገባል። ቤተኝነት ካልተሰማቸው፣ ችግራቸውን ለመፍታት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሽማግሌ ዘንድ ችግራቸውን ይዘው አይመጡም። ስለዚህ እንግዳ ተቀባይነት ማለት የቤተ ክርስቲያን አባላትና የማያምኑ ሰዎች እንዲጐበኙንና ችግራቸውን እንዲያወያዩን መፍቀድና፣ መንፈሳዊ ምክርና ትምህርት ፍቅርና፣ የመሳሰሉትን መስጠት ነው።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰዎች የሽማግሌዎችን ቤት በደስታ ይጐብኙ ዘንድ የሽማግሌዎች ቤት ደስ ብሏቸው እንዲሄዱ ማድረግ ለምን ይጠቅማል? ለ) ቤትህ ምን ይመስላል? ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊጐበኙህ ይመጣሉ? ካልሆነ፣ ለምን? |

## በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት የሚያስፈልገው ዋና ክህሎት

**ረ. ማስተማር የሚችል** - ይህ በቀጥታ በባሕሪ ላይ መሠረት ካላደረጉ ጥቂት መስፈርት መካከል አንዱ ነው። ይልቁንም፣ ችሎታ ነው። ሆኖም፣ ከማስተማር አገልግሎት ጀርባ በመሪ ውስጥ መታየት ያለበት አመለካከትና ባሕሪ አለ። ለማስተማር፣ ሽማግሌው አምስት በጣም አስፈላጊ ነገሮችን መማር አለበት፡-



<u>አንደኛ</u>፣ ሽማግሌው ለመማር የተዘጋጀ መንፈስ ያስፈልገዋል። አዳዲስ ነገሮችን ለመማር ራሳችንን ካልከፈትን፣ መማር አንችልም። ስለዚህ ሽማግሌዎች ሁልጊዜ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር የሚፈልጉ መሆን አለባቸው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ የእግዚአብሔርን እውነት ለመማር ጊዜ ወስደው የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት አለባቸው። ጳውሎስ ወደ ቲቶ በጻፈው መልእክት ላይ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅሰው ሕዝቡን የሚያጽናኑና እውነትን በመጥቀስ ሐሰተኛ ትምህርትን የሚቃወሙ መሆን አለባቸው ይላል። ሽማግሌዎች ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ማወቅ አለባቸው። ያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ሽማግሌዎች ጊዜ ወስደው የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው ሲያጠኑ ነው።

<u>ሦስተኛ</u>፣ ሽማግሌው የእግዚአብሔርን ቃል በራሱ ላይ ተግባራዊ ካደረገ በኋላ ነው። ወደ ሌሎች አማኞች ማስተላለፍ ያለበት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚጀምረው እውነቱን ስናውቅና በሕይወታችን ተግባራዊ ስናደርገው ነው። የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን ላይ እንዴት እንደሚሠራ ከተረዳን በኋላ በእውነተኛ ሕይወት ውስጥ እንዴት የእግዚአብሔር ቃል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱሳዊ «ጥበብ» እናስተላልፋለን። እግዚአብሔር በሕይወታችን ያደረገውንና ስለ መንፈሳዊ ዕድገት የተማርነውን እናስተምራለን። ዛሬ ሰዎች የትምህርት መሠረቱ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር እንደ ሆነ በማሰብ በዚያ ላይ ያተኩራሉ። ትምህርት እውነትን በማወቅ ላይ የተመሠረተ ነው ብለን እናስባለን። እውነቱን ተስማመድን አልተስማመድን ግድ የለንም። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ያላገቡ ሰዎች በትዳር ላይ የተወሰነ የክፍል ውስጥ ትምህርት ስለ ወሰዱ ብቻ ስለ ትዳር ማስተማር የሚችሉ ይመስላቸዋል። ነገር ግን እንደዚያ ያሉ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚያመጡት ተጽዕኖ በጣም አነስተኛ ነው። ይልቁንም፣ እውነቱን

የኖሩ ሰዎች ሌሎችን ሊያስተምሩ ተቀባይነትን ያገኛሉ።

አራተኛ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል ወስደው እንዴት በእውነተኛ ሕይወታቸው ላይ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ማወቅ መቻል አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚሠራው የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ወስደን ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ላይ ተግባራዊ ስናደርገው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተማርናቸውን በጥቅሉ የተቀመጡ መረጃዎች ወይም እውነቶች ማስተላለፍ ብቻ አይደለም። ሽማግሌዎች እውነትን ማስተማር ማለት በሰዎች ደረጃ፣ የትምህርት ደረጃቸውንና የመንፈሳዊ ዕድገታቸውን ደረጃ ጠብቀን የምንሰጠው መሆኑን መማር አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን አባላት ያሉባቸውን ችግሮች በመፍታቱ ላያ ያተኮረ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ወስደው የሚያጽናኑና በቤተ ክርስቲያን የሚነሡ የሐሰት ትምህርቶችን መቃወም የሚችሉ ናቸው።

አምስተኛ፣ ሽማግሌዎች አባሎቻቸውን ለማስተማር የተለያዩ መንገዶችን መቀየስ አለባቸው። ከቤተ ክርስቲያን ምስባክ፣ ወይም በሰንበት ትምህርት ቤት፣ በደቀ መዝሙርነት ክፍለ ጊዜ፣ በየቤቱ እየሄዱ መንፈሳዊ ምክር መስጠት፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል።

በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰወረ አስፈላጊ እውነት አለ። አብዛኛ ውን ጊዜ መሪዎች በቀዳሚነት የሚያከናውኗቸው ነገሮች ውሳኔ የሚወሰንበት የሽማግሌዎች ስብሰባ፣ ትእዛዛትን ማሳለፍ፣ ገንዘብ በምን ዓይነት መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው መወሰን፣ መቼ ቤተ ክርስቲያን መገንባት እንዳለባቸው መወሰን፣ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መፍታት፣ ወዘተ. . . ይመስሉናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የመሪነት ዋነኛ ክፍሎች እነዚህ እንዳልሆኑ ያስተምራል። ይልቁንም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር መሠረት ያደረገው በሁለት የመሪነት መሣሪያዎች ላይ ነው።

አንደኛ፣ ይህ መሠረት ያደረገው ለሌሎች አማኞች እንዴት



እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መኖር እንዳለባቸው ምሳሌ በመሆን ነው። ጳውሎስ መንፈሳዊ መሪ ስለ መሆን የጻፋቸው ዝርዝሮች በሙሉ ለሌሎች ምሳሌ ስለ መሆንና ጳውሎስ እንዳለው «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» ነው (1ኛ ቆሮ. 11:1፤ 1ኛ ጢሞ. 4:12ን ተመልከት)።

ሁለተኛ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት በትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው። ሰዎች በመንፈሳዊ እርምጃና እውቀት እንዲያድጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ማስተላለፍን ያካትታል። ዓለም ሰዎች እንዲታዘዙ የሚጠቀመው ትእዛዛትን፣ ሽልማቶችን ወይም የቅጣት ማስፈራሪያን ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደዚህ ዓይነት ሥልጣን አልሰጠም። ይልቁንም፣ የእኛ ሥልጣን የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከማወጅ ነው። ለዚያ ነው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር ሰዎች የእርሱን ትምህርት ችላ ሲሉና መስማት የሚፈልጉትን ብቻ ቢሰሙም፣ በጊዜውም ያለጊዜውም ቃሉን በመስበክ ላይ እንዲያተኩር የነገረው (2ኛ ጢሞ. 4:1-5)። ሽማግሌዎች ሕዝቡ ሕይወቱን እንዴት በእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ማሳየት አለባቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት የሚፈልግን የስሕተት ትምህርት ለመቋቋም የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር አለባቸው (የሐዋ. ሥራ 20:26-31)። ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእውነት «ጠባቂዎች» መሆን አለባቸው። እውነቱን ለመጠበቅ ደግሞ፣ እውነቱን ማወቅ አለባቸው።

ጳውሎስ ሽማግሌዎች ሁሉ ጥሩ ተናጋሪዎች መሆን አለባቸው አላለም። ነገር ግን ሁሉም ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሊኖራቸውና በሆነ መንገድ ማስተማር የሚችሉ መሆን አለባቸው። አንዳንድ ሽማግሌዎች በሕዝቡ ፊት በመናገር ጐበዞች ሊሆኑና በየእሁዱ አማኞችን ማስተማር ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን አንዳንድ ሽማግሌዎች ትንንሽ ኅብረቶችን ማስተማር የሚችሉ ይሆናሉ ወይም በግል ሊያማክሩ አንድን ሰው እንዲታረም

የማድረግ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ መሪዎች ሰዎች በእምነት እንዲያድጉ ኃላፊነት ስላለባቸው፣ እና መንፈሳዊ እድገት ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር የሚያስፈልገው በመሆኑ፣ ሽማግሌዎች ሕዝቡ በእምነቱ ያድግ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር መቻል አለባቸው፡፡

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ያሉ ሽማግሌዎች የተመረጡት የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ይችላሉ በሚል መረዳት ነውን? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል ባለማወቃቸውና አማኞችን በትክክል ማስተማር ባለመቻላቸው የተነሣ ያየኸውን ችግር አስረዳ፡፡ ሐ) ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሄደው መማር የማይችሉ ሽማግሌዎች ማስተማር ይችሉ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ማደግ የሚችሉባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? መ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን የማስተማርና ለሌሎች ምሳሌ የመሆን መሣሪያ ምን ያህል ይጠቀማሉ? እንዴት ነው እነዚህን መሣሪያዎች በተሻለ ሁኔታ የሚጠቀሙት? ሠ) መጽሐፍ ቅዱስ የሚያተኩርበት ምን ዓይነት የመሪነት መሣሪያ ይጠቀማሉ?

## ሦስተኛ ቀን፡- ለመንፈሳዊ መሪነት የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 2)

ትላንትና ጳውሎስና ጴጥሮስ በፈቃደኝነት ሕዝቡንና ቤተ ክርስቲያንን በመሪነት ለሚመሩ ሰዎች ያስፈልጋሉ ብለው የዘረዘሯቸውን ባሕርያት ማየት ጀምረናል፡፡ እነዚህ ባሕርያት ለሽማግሌዎች **«አስፈላጊዎች»** ናቸው፡፡ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን አባላት በሙሉ የእድገት «ግቦች» መሆን አለባቸው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰልን መሆን አለመሆናችንን ለማየት እነዚህን ባሕርያት ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡፡

25ኛ ጥያቄ፡ 1ኛ ጢሞ. 3፡1-12፣ ቲቶ 1፡6-9፣ እና 1ኛ ጴጥ. 5፡1-44 በድጋሚ አንብብ፡፡ ሀ) አብዛኛዎቹ መሪዎች ከሚያሟሏቸው ባሕርያት በመጀመር ጥቂቶቹ የሚያሟሏቸውን ባሕርያት ዘርዝር፡፡ ለ) እነዚህ



ባሕርያት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት አካል ቢሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን ያለው ሁኔታ እንዴት እንደሚለወጥ ግለጽ፡፡

በጳውሎስና በጴጥሮስ የተዘረዘሩትን የመንፈሳዊ መሪ ባሕርያትን በአጭሩ ማጥናታችንን እንቀጥል፡፡ በ1ኛ ጢሞ. 3 ላይ፣ ጳውሎስ የዘረዘራቸው ቀጣይ ባሕርያት ያለነቀፋ የሆነ የክርስቶስ ተከታይ ሊያደርጋቸው የማይገቡ ነገሮችን ነው፡፡

## መሪዎች ሊጠነቀቁባቸው የሚገባቸው አሉታዊ ባሕርያት

ሰ. የማይሰክር፡- ከዚህ ቀደም ብለን መሪ ራሱን መቆጣጠር እንዳለበት ተምረናል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ ሕይወቱን እንዲቆጣጠር ለማንም መፍቀድ የለበትም (ኤፌ. 5፡18)፡፡ እናም ጳውሎስ ማንኛውም ሽማግሌ መጠጥ እንዲቆጣጠረው መፍቀድ እንደሌለበት ተናግሯል፡፡ ስካራም ራሱን መቆጣጠር ስለማይችል፣ መሪ ፈጽሞ መስከር የለበትም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌም ሆነ ተራ የቤተ ክርስቲያን አባል የስውን የራስ መቆጣጠር ሊነጥቁ የሚችሉ እንደ ጫት፣ አደንዛዥ ዕጾች፣ ሲጋራና የመሳሰሉ ነገሮችን መጠቀም የለበትም፡፡

ሸ. ቁጡ ያልሆነ ወይም ጨዋ፡- ልንቆጣጠረው የሚገባ ሌላው የሕይወታችን ክፍል ቁጣ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በቤተሰቡ ውስጥም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰዎች ላይ የቃላትም ሆነ አካላዊ ጥቃት ለማድረስ ሥልጣኑን የሚጠቀም መሆን የለበትም፡፡ ልክ እንደ ኢየሱስ፣ ሌሎች ሲሰድቡት፣ አይበቀልም (1ኛ ጴጥ. 2፡20-23)፡፡

ግሪኮች የጨዋነትን ባሕሪ በጣም ከፍ አድርገው ይመለከታሉ፡፡ በግሪክ ቋንቋ «ጨዋ» የሚለው ቃል ዝምተኛና ሌሎችን የሚያልፍ ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ እውነተኛ ፍትሕ የመስጠት ባሕሪ ነው፡፡ ከተጻፈው ሕግ አልፎ፣ ሕጉ ምን ለማለት

እንደ ፈለገና የሰዎችንም ምክንያት የሚያገናዝብ ነው:: ሰዎች ደካሞችና የሚወድቁ እንደ ሆነ ይረዳል:: ስለዚህ ሰዎችን በጨዋነት ያስተናግዳል:: ሰውየው የሠራውን ስሕተት ብቻ ሳይሆን ሰውየው ስሕተቱን የሠራበትን ምክንያት ጭምር ሳይቀር ይረዳል:: ሰውየው አሁን ከሠራው ስሕተት ይልቅ የረጅም ጊዜ ሥራዎቹንና ያለፈው ሕይወቱ ምን እንደሚመስል ይመለከታል:: ጨዋ ሰው የሚያተኩረው ሰዎች ባሏቸው መልካም ነገሮች እንጂ በስሕተታቸውና በችግራቸው ላይ አይደለም::

ሽማግሌዎች ለሰዎችና ላሉባቸው ችግሮች ሲራሩ ይገባል:: መንፈሳዊ መሪ ሰዎች በኃጢአት ሲወድቁና ድካማቸውን ይረዳል:: ሕፃናት እኛ የማንፈልገውን ነገር ሲሠሩ እንኳን በፍቅር እንደምናያቸው፣ ከሌሎች ጋርም ልክ እንደዚያ ጨዋ መሆንን መማር አለብን:: ኢየሱስ ራሱን ሲገልጥና አቅማቸው የደከመ ሁሉ አረፍትን ያገኙ ዘንድ ከነችግራቸው ወደ እርሱ እንዲመጡ ሲያዝ «ጨዋና ሩኅሩኅ» መሆኑን በመንገር ነው (ማቴ. 11:29):: በኢሳ. 42:2-3 ላይ መንፈሳቸው ስለ ተሰበረ ሰዎች ሲጽፍ፣ ኢየሱስ የተቀጠቀጠ ሸምበቆን እንደማይሰብርና የሚጤሰን ክር እንደማያጠፋ ተነግሮናል:: በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያሉት ሽማግሌዎችም እንደዚያ መሆን አለባቸው:: ሰዎችን መቅጣትን ከመፈለግ ይልቅ፣ ሽማግሌዎች ወደ ሰዎች ቀርበው ሲረዷቸውና ድካማቸውን በማወቅ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ በጨዋነት ሲረዷቸው ይገባል::

> 26ኛ ጥያቄ:- ሀ) በምን ዓይነት መንገዶች ነው ሽማግሌዎች ከሌሎች አማኞች ጋር ትዕግሥት በማጣት በክፉ የሚያስተናግዷቸው? ለ) ሽማግሌዎች ከአማኞች ጋር ባላቸው ግንኙነት አማኞች ትልቅ ችግር ሲፈጥሩም እንኳን በጨዋነት ማስተናገዳቸው አስፈላጊ የሆነው ስምንድን ነው? ሐ) «በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጐች» ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ስውየው ስሕተቱን የሠራበትን ምክንያት መረዳት አስፈላጊ የሆነው ስምንድን ነው?



ቀ. የማይጣላ:- ይህ ማለት በተደጋጋሚ ከሰዎች ጋር ባለ የአሳብ ልዩነት የማይጣላ፣ ሁልጊዜ የሰዎችን ስሕተት የማይፈልግ፣ ሁልጊዜ የተለየ አሳብ የማያነሣ፣ ሁልጊዜ እሱ ታዊና የእኔ አሳብ ብቻ ይሁን የማይል ሰው ማለት ነው:: ሽማግሌ የእኔ አሳብ መሆን አለበት ብሎ ሁልጊዜ ከመጣላት ይልቅ፣ ሌሎችን የሚሰማ፣ ለሌሎች ካለው ክብር የተነሣ የሰዎቹ አሳብ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ካለው አሳብ ጋር የማይጋጭ ከሆነ የራሱን አሳብ የሚተው መሆን አለበት::

በ. ገንዘብን የማይወድ:- ጳውሎስና ጴጥሮስ በገንዘብ አጠቃቀምና ስለ ገንዘብ ሲኖረን በማገባው አስተሳሰብ ላይ ማተኮራቸው አስገራሚ ነው:: በእርግጥ፣ ስለ መሪ አስፈላጊ ባሕርያት በተጻፉት ዝርዝሮች ሁሉ ላይ ይህ ጉዳይ ተጠቅሷል:: (በትላንቱ ትምህርት ያየነውን ሠንጠረዥ ተመልከት):: ምናልባት ጳውሎም ሆነ ጴጥሮስ በዚህ ነጥብ ላይ ያተኮሩት መሪዎች አብዛኛ ውን ጊዜ ከሚወድቁባቸው ዋነኛ ክፍሎች አንዱ ስለሆነ ነው:: በ2ኛ ቆሮ. 7:17 ላይ ጳውሎስ «ብዙዎች እንደሚያደርጉት» የወንጌልን ቃል አልሸቅጥም ብሏል:: በእርሱ ጊዜም እንኳን እግዚአብሔርን ለገንዘብ ጥቅም ሲሉ የሚያገለግሉ በርካታ የቤተ ክርስቲ:ያን መሪዎችና አገልጋዮች ነበሩ:: በ1ኛ ጢሞ. 6:5-10 ላይ ጳውሎስ ከዘረዘራቸው ሐሰተኛ የአስተማሪዎች ባሕርያት አንዱ ጤናማ ያልሆነ የገንዘብ ፍላጐት ነው::

በሙሉ ጊዜአችን በክፍያ የምናገለግል ሰዎች ልናስብበት ይገባል:: ሌላ ሥራ ማግኘት ስለማንችል መጋቢነትን ወይም ወንጌላዊነትን ከመረጥን፣ ከቤተ ክርስቲያን የመክፈል አቅም ይልቅ በዓለማውያን የደመወዝ ስኬል መሠረት እንዲከፈለን የምንጠይቅ ከሆነ፣ የወንጌል ነጋዴዎች ነን ማለት ነው:: ወይም ብዙ ጊዜ ደመወዛችንና ጥቅማችን ምን ያህል ሲሆን ይችላል ብለን የምናስብ ከሆነ፣ ያም የት እንደምንሠራ የሚያስወስነን ከሆነ፣ በወንጌል እየነገድን ነው ማለት ነው:: ነጋዴዎች ለያዙት ጤፍ ምርጥ ዋጋ

የሚያቀርብላቸውን ደንበኛ እንደሚፈልጉ፣ እኛም ለቤተ ክርስቲያን መሪነት አገልግሎታችን የተሻለ ምርጥ ክፍያ እንፈልጋለን ማለት ነው።

ሆኖም፣ እንደ ሽማግሌዎች ያሉ ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ገንዘብን በተመለከተ ባላቸው አመለካከት ሊጠነቀቁ ይገባል። በሥራቸው (በእርሻቸው፣ በቢሮ ሥራቸው፣ ወዘተ. . . ) ገንዘብና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ለእነርሱ እጅግ አስፈላጊ ነገር ያለመሆኑን ማሳየት አለባቸው። ስለ ዓለምና ጥቅማ ጥቅሞቹ ከማሰብ ይልቅ፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንግሥቱ መቆርቆርን ማሳየት አለባቸው (ማቴ. 6:19-24፣33)። ትኩረታቸው ትልልቅ ቤቶችን በማግኘትና በማኅበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ፣ ወዘተ. . . መሆን የለበትም።

ለሽማግሌዎች ይህ አስፈላጊ የሆነባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ፡-

<u>አንደኛ</u>፣ ሽማግሌዎች በደግነትና ለእግዚአብሔርና ለመንግሥቱ በመጨነቅ የሕይወት ዘይቤ ረገድ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ምሳሌ መሆን አለባቸው። በምንሰጠው የአሥራት መጠን ለእግዚአብሔር የመስጠትን ደስታ ለሕዝቡ ማሳየት እንችላለን። ድሃን በመርዳት፣ እግዚአብሔር እንዴት ልጆቹ ድሃን እንዲረዱ እንደሚፈልግ ልናሳይ እንችላለን። ገንዘባችንን ወንጌልን ለማስፋፋት በመጠቀምና የራሳችንን ጥቅም ባለመፈለግ፣ ለአማኞች ሌላ ዓለም እንደሚመጣና ሁላችንም አሁን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ማተኮር እንዳለብን እናሳያለን።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በአግባቡ የመጠቀም ኃላፊነት አለባቸው። በገንዘብ አጠቃቀማችን ላይ ታማኞች ካልሆንን፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስለ መባውና ስለ አሥራቱ ብር አጠቃቀማችን አያምኑንም። የራሳችንን ገንዘብ



ሕይወትን ሊያቀሉልን በሚችሉ ነገሮች ላይ ካዋልን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑ (ለምሳሌ፡- እምነትን የሚያሳድጉ መጻሕፍትና ወንጌላውያንን መላክን የመሳሰሉ ነገሮች እያሉ) ያን ያክል የማያስፈልጉ ነገሮችን (ለምሳሌ፡- ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ፣ የሙዚቃ መሣሪያ፣ የመዘምራን ልብስ) መግዛታችን አይቀርም። ገንዘብን በጣም የምንወድ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ ለግል ፍላጐታችን ማሟያ ለመጠቀም ልንፈተን እንችላለን፣ ይኸውም በሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ ጥሩ ምግብ እንዲቀርብበት፣ ወይም ለራሳችን ጥቅም ገንዘቡን ልንጠቀምበት እንችላለን። ሽማግሌዎች በዚህ የሕይወታችን ክፍል ዝናችንን የሚያጐድፍ ነገር እንዳይኖር መጠንቀቅ አለብን። ያ ማለት በእኛ ላይ ክስ የሚያመጣ ምንም ነገር እንዳይኖር መጠንቀቅ አለብን ማለት ነው። (ማስታወሻ፡- ከኋላ በሚመጣ አንድ ትምህርት ላይ ይህንን በስፋት እናጠናዋለን)።

> 27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በምን ዓይነት መንገዶች ነው መከራከርና መጣላት የሚፈልግ ሰው በመሪዎች መካከል ወይም በቤተ ክርስቲያን ያለውን ኅብረት ሲያጠፋ ያየኸው? ለ) «የገንዘብ ፍቅር ያለው» የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጥር እንዴት እንዳየህ አስረዳ።

## መሪ ሊጠብቃቸው የሚገቡ ቁልፍ ግንኙነቶች

ተ. ቤተሰቡን በሚገባ የሚመራ፡- መሪነት የሚጀምረው ከቤት ነው። በቤቱ ውስጥ መንፈሳዊ አመራር መስጠት የማይችል ሰው በትልቁ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ አመራር መስጠት አይችልም። መሪዎች ልጆቻቸው እግዚአብሔርን እንዲከተሉ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ተጽዕኖ ማሳደር ካልቻሉ፣ እንደ ዔሊና እንደ ሳሙኤል ልጆች መጨረሻቸው በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ክፋትና መጥፎ ምስክርነትን ነው የሚያስፋፉት (1ኛ ሳሙ. 2:12-17፣ 8:3)።

«ማስተዳደር» የሚለው ቃል ባልየው በልጆና በሚስቱ ላይ ክፉ አለቃ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ይልቁንም፣ አባት ከቤተሰቡ አባላት ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ ሁለት አላቦች ተካትተውበታል። **አንደኛ፣** ቤተሰቡን «መንከባከብ» አለበት። ይህ ማለት ስለ አካላዊና መንፈሳዊ ደኅንነታቸው ኃላፊነት አለበት ማለት ነው። የሚመራቸው ለራሱ ጥቅም ሳይሆን፣ ለእነርሱ ጥቅም ነው። አገልጋይ - መሪነት የሚጀምረው በቤተሰባችን ውስጥ ባል እንደ መሆናችን መጠን ለሚስታችንና ለልጆቻችን እንክብካቤ ስናደርግ ነው። **ሁለተኛ፣** ባል ቤተሰቡን ሊያስተዳድር፣ ሊመራ፣ ሊቆጣጠርና መንገድ ሊያሳያቸው ያገባል። በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድጉ ሊመራቸው ይገባል። በቤቱ ከሌለ፣ ወይም በጥንቃቄ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር በመሆን እንዲያድጉ ካልረዳቸው፣ እግዚአብሔር በቤቱ የሰጠውን የመሪነት ሚና አልፈጸመም ማለት ነው። በቤቱ ውስጥ ያንን ካልፈጸመ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊፈጽመው አይችልም።

(ማስታወሻ፡- ይህ ትምህርት የሚያመለክተው ባልና ሚስት አብረው እንደሚኖሩ ነው። አንድ ባል ከሚስቱ ጋር ተራርቆ እየኖረ ለቤተሰቡ የመሪነት ድርሻውን እንዴት ይወጣል? ዛሬ ዛሬ በአንዳንድ ወንጌላውያንና የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሠሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ያለው ባልና ሚስት በተለያየ ቦታ እየኖሩ በተወሰነ ጊዜ የሚገናኙበት ሁኔታ (አዝማሚያ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም። አብርሃም ሚስቱን ሣራን በካራን ትቶ ወደ ከነዓን ሲሄድ ሊታይህ ይችላል? የገንዘብ ፍላጐት ባልና ሚስትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ግንኙነት ውስጥ እንዳይከታቸው መጠንቀቅ አለባቸው። የገንዘብ ፍቅር ሽማግሌና ቤተሰቡን የሚለይ መንገድ አይደለምን? መሪው ቤተሰቡ አብሮት ከሌለ እንዴት ነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለሆነ ትዳር ምሳሌ የሚሆነው?

ለአንዳንድ ወንጌላውያን፣ ተለይቶ መኖር የገንዘብ ጥያቄ



አይደለም፣ ነገር ግን ሚስትየው ቤተሰቧን እየናፈቀች አዲሱን ባሕል ለመልመድ በመታገል ላይ መሆኗ ነው። እግዚአብሔር ወንጌላውያን እንድንሆን ከጠራን፣ ሚስት የምትሆነን ስንመርጥ በጣም መጠንቀቅ አለብን። እነርሱም ለወንጌላዊነት ካልተጠሩ በስተቀር፣ ከመኖሪያ አካባቢአቸው ርቀው በመኖራቸው አይረኩም። ለጊዜው ከባላቸው ጋር ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ወደ ቤቷ ተመልሳ የምትሄድበትን ምክንያቶች በመፍጠር ከባለቤቷ ጋር ተለያይታ ትኖራለች። ምንም እንኳን ወንጌላዊው አብራው እንድትቆይ ቢያስገድዳትም፣ ብዙ ጊዜ አይሳካለትም። እርሷ በዚያ መቆየትን ካልወደደች የእርሱን ሕይወትና አገልግሎት አስቃቂ ታደርገዋለች። በዚህ ትውልድ፣ ሚስትየው ወደ ቤት ለመሄድ የራሷን ውሳኔ ታደርጋለች። አንድ ወንጌላዊ ራሱን በዚህ ሁኔታ ካገኘና ሚስቱ በዚያ ስፍራ አብራው መቀመጥ ካልፈለገች፣ ወደ ቤት ቢመለስ ይሻለዋል። ታላቁ አደጋ አንዳንድ ወንጌላውያን ሚስታቸው አጠገባቸው ባለመኖሯ በዝሙት ኃጢአት መውደቃቸው ነው። ሊያገለግሏቸው ለተጠሩት ሕዝብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ መስጠት ያቅታቸዋል። በቤቱ እያለ፣ አንድ ሰው ወንጌላዊ እንዲሆን እግዚአብሔር እንደ ጠራው የሚያምን ከሆነ፣ ሚስቱ አብራው እንድትሄድ እግዚአብሔር ልቧን እንዲቀይረው መጸለይ አለበት። እናም እግዚአብሔር በሚስቱ ልብ እንዲሠራ በትዕግሥት መጠበቅ አለበት።)

ሌላኛው ቤተሰብን «ማስተዳደር» ማለት ሚስት ባል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አገልግሎት መደገፍ አለባት ማለት ነው። ሽማግሌ፣ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ የመሆን ውሳኔ ለባል ብቻ የሚተው መሆን የለበትም። ይልቁንም፣ ቤተሰቡ በሙሉ እግዚአብሔርን በመሥዋዕትነት ለማገልገል መወሰኑ አስፈላጊ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚነካው ባልን ብቻ ሳይሆን፣ ሚስትና ልጆችንም ጭምር ነው። ባል በቤት ውስጥ የሚያሳልፈው ጊዜ እያነሰ ስለሚሄድ፣ ሚስት ልጆቹን የማሳደግና

ቤቱን የመምራት ኃላፊነቷ ይጨምራል። እንዲሁም ሰዎች የባሏን እርዳታ ፈልገው በተደጋጋሚ ወደ ቤቷ ይመጣሉ። ከዚያ የተነሣ ከሌላ ጊዜው የሚበልጥ ምግብ ማብሰል ይጠበቅበታል። እርሷ እግዚአብሔርን እያገለገለች እንደ ሆነ በመረዳት የተጨመረባትን ኃላፊነት በደስታ ካልተቀበለች፣ የባሏ አገልግሎት ይጐዳል። እርሷም ሆኑ ልጆቿ በአባትየው ላይ ያምጻሉ። ቤታቸውም እንደ ባልና ሚስት በሰላም አብሮ የመኖር ምሳሌ መሆኑ ይቀራል።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሉቃ. 18፡29-30ን በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጐም ወንጌላዊ ከቤተሰቡ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አያስፈልገውም ይላሉ። እርሱ ተባረኩ ብሎ ሊተዋቸው ይገባል ይላሉ። ነገር ግን ይህ የሉቃስ ወንጌል ምንባብ የሚያስተምረው እንደዚያ አይደለም። እዚያ ጋ የሚናገረው መጀመሪያ ኢየሱስን ለማመን በሚደረግ ውሳኔ ነው። አንድ ሰው ቤተሰቡ (ሚስቱ ወይም ልጆቹ) የኢየሱስ ደቀ መዝሙር እንዳይሆን ሊያሰናክሉት አይገባም። ይልቁንም፣ እምነቱን በኢየሱስ ላይ አድርጐ ሊከተለውና እነርሱን «ሊተዋቸው» ይገባል። ጳውሎስ በግልጽ ባል ሚስቱንና ልጆቹን በእግዚአብሔር መንገድ የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት ብሏል። በእርግጥ ጳውሎስ ቤተሰባቸው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዳያድግ ችላ የሚሉ ወንጌላውያንና ሽማግሌዎች ወንጌላዊና ሽማግሌ ለመሆን እንደማይበቁ ይናገራል።

እንዳለመታደል ሆኖ፣ በቤታቸው መንፈሳዊ የሆነ አመራር የሌላቸው ብዙ መጋቢዎችና ወንጌላውያን አሉ። አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር ሥራ ከመጠመዳቸው የተነሣ ለቤተሰባቸው ምንም ጊዜ የላቸውም። ሌሎቹ ደግሞ ጊዜ ወስደው ስለ እግዚአብሔር፣ እንዴት እንደሚከተሉትና በሕይወታቸው እንደሚያከብሩት፣ እንዴት መጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት እንደሚችሉ፣ ወዘተ. . . አያስተምሯቸውም። ሚስታቸው ይህንን እንደምታደርግ ይገምታሉ። ከዚህ የተነሣ፣ የመጋቢዎችና የወንጌላውያን ልጆች በሥርዓት አልበኝነት የሚታወቁትና ትምህርት ቤት ሲገቡም



እምነታቸውን መጀመሪያ የሚተዉት ለዚያ ነው። ብዙ ጊዜ የሽማግሌዎችም ልጆች ልክ እንደዚሁ ናቸው።

እግዚአብሔር ለመሪነት ያለው መመሪያ በከፍተኛ ደረጃ አመራርን ከመስጠታችን በፊት በትንንሽ የአመራር ደረጃዎች ላይ ታማኝ መሆን ነው። ቤተሰብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሙሉ እግዚአብሔርን የሚያስደስት አመራርን የሚለምዱበት የመሪነት መሠረት ነው። በዚያ መምራት የማይችል መሪ፣ ብዙ ሰዎች ባሉበት ሊመራ እንደማይችል ግልጽ ነው። አንድ ሰው ሚስቱንና ልጆቹን እግዚአብሔርን ስለ መውደድ ካላስተማረና እግዚአብሔርን መውደዳቸው ወላጆቻቸውን በማክበር ካልተገለጠ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲወድና እንዲታዘዝ ተጽዕኖ ማምጣት አይችልም። ሽማግሌ የቤተ ክርስቲያን አባላት «መንፈሳዊ አባት» ነው። ቤት ውስጥ ቤተሰቡን ለማሳደግ የሚደረገው ዓይነት እንክብካቤ በሙሉ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲያድጉ ለመርዳት መወሰድ አለበት።

የሽማግሌ የመሪነት ዘዴም በቤት ውስጥ ይታያል። ሽማግሌ ሚስቱና ልጆቹ እንዲታዘዙት ለማድረግ ኃይልን፣ ትእዛዝን፣ የቃላትና አካላዊ ጉዳትን በቤተሰቡ ላይ የሚያመጣ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም የሚመራው በተመሳሳይ መንገድ ነው። ነገር ግን ሽማግሌ በማገልገል፣ በመርዳት፣ በመንከባከብ፣ በጨዋነት፣ በማበረታታት፣ በማስተማር፣ በቤት ውስጥ ምሳሌ በመሆን የሚመራ ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ልክ እንደዚያው አገልጋይ ይሆናል።

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የብዙ ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና ወንጌላውያን ቤተሰቦች በሥነ ምግባርና በመንፈሳዊነት መልካም ዝና አላቸው? ከሌላቸው፣ ለምን? ለ) ለምንድን ነው ጳውሎስ ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን የሚወድና የሚታዘዝ ቤተሰብ ሊኖራቸው ይገባል ያለው? ሐ) አባት የቤቱ መንፈሳዊ መሪ እንደ መሆኑ መጠን ልጆቹ በእግዚአብሔር እንዲያምኑ፣ እንዲወዱትና እንዲታዘዙት ለመርዳት በምን ዓይነት

መልኩ ማብረታታት እንዳለበት ዘርዝር:: መ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የሚገኙ አብዛኛዎቹ አባቶች ይህንን ያደርጋሉ? ሠ) ኢየሱስ ማንኛውንም ሰው ባልና ሚስትን ማለያየት እንደሌለበት ተናግሯል (ማቴ. 19:4-6፣ 1ኛ ቆሮ. 1-6):: እነዚህ ጥቅሶች በማንኛውም ምክንያት ከባለቤታቸው ተለያይተው በሚኖሩ ወንጌላውያንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የሚሠሩ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ረ) ሚስቶች የባሎቻቸውን፣ ልጆችም የአባቶቻቸውን አገልግሎት መደገፋቸው በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ይህ ማለት የአንድ ሽማግሌ ልጅ ቢያምፅ ሽማግሌው ወዲያውኑ ያለውን መሪነት ያጣል ማለት ነው? አይደለም:: ልጆቻችንን ምንም ያህል ጥሩ አድርገን ብናስተምራቸው፣ በእግዚአብሔር ላይ የማመፅና በራሳቸው መንገድ የመሄድ ችሎታ አላቸው:: ሆኖም፣ አብዛኛዎቹ ልጆች በጥባጮች፣ ሥርዓተ-ቢሶችና ከእምነት ያፈነገጡ ከሆነ፣ ብዙ ጊዜ ባል በቤት ውስጥ ልጆቹ ስው አክባሪዎችና ኢየሱስን መከተል የሚፈልጉ አድርጐ እንዳላሳደጋቸው የሚያሳይ ምልክት ነው:: ስለዚህ አንድ ልጅ ዐመፀኛ ስለሆነ አንድን ሽማግሌ ከአገልግሎት ከማስወገዳችን በፊት፣ ሌሎቹ ሽማግሌዎች ሁኔታው የተከሰተው ሽማግሌው በቤቱ በአግባቡ ባለመምራቱ ይሁን ወይም ልጁ ከተማረው ትምህርት በማፈንገጡ የተነሣ ሁኔታውን መመርመር አለባቸው::

ቸ. አዲስ አማኝ ያልሆነ:- ጳውሎስ ሽማግሌ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ መሆን እንዳለበት በጥብቅ ያስገነዝባል:: አዲስ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወት ለመብሰል ጊዜ ስለሌለው፣ በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ መሪ ለመሆን ዝግጁ አይደለም:: በመንግሥት ሥራ ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ መሪ ሲሆን ይችላል:: ነገር ግን መንፈሳዊ ድርጅትን ለመምራት ዝግጁ አይደለም:: እግዚአብሔርን መምሰል የተማሩና እርሱን የሚመስሉት እንዲሁም እርሱ እንደሚፈልገው የሚመሩት ብቻ ለቤተ ክርስቲያን መሪነት ብቃት አላቸው:: አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚበስለው እንዴት ነው?



<u>አንደኛ</u>:- በዋነኛነት ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ጊዜ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የአንድ ሰውን ባሕሪ ለመሥራትና ክርስቶስን እንዲመስል ለማድረግ ጊዜ ያስፈልገዋል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ እያንዳንዱ ሰው ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት አለበት:: አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ክርስቶስን ወደ መምሰል ለማደግ መፈለግ አለበት:: ይህ ማለት የመጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት፣ እግዚአብሔርን የመታዘዝ፣ እርሱን የማገልገል፣ ወዘተ. . . ፍላጐት ሲኖረው ይገባል::

<u>ሦስተኛ</u>፣ አንድ ሰው በቋሚነት በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ አለበት:: አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያድገው የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰማና በሕይወቱ ላይ ተግባራዊ ሲያደርገው ነው:: ከዓለም የተማርናቸውን የተሳሳቱ አመለካከቶችና በጊዜ ሂደት ያዳበርናቸውን የተሳሳቱ ልማዶች ብናስወግድ ይገባል:: እያንዳንዳችን አዳዲስ ፍጥረቶች እንደ መሆናችን አዳዲስ የአስተሳሰብ መንገዶችን ልንማርና እግዚአብሔርን የመከተል አዲስ ልማድ ልናዳብር ይገባል::

<u>አራተኛ</u>:- እያንዳንዱ ሰው አማኙን በመቃወም የሚሠሩትን ሦስት ጠላቶቹን ማለትም፣ እርጌ ተፈጥሮውንና የዓለምን ትምህርት እንዴት እንደሚያሸንፍ መማር አለበት::

ምንም እንኳን መንፈሳዊ ብስለት ለማግኘት ጊዜ ቢወስድም፣ ለረጅም ጊዜ አማኝ ሆኖ መቆየት ብቻውን መንፈሳዊ ብስለትን አያመጣም:: አንዳንድ አማኞች፣ ኢየሱስን በሙሉ ልባቸው ለመከተል ካላቸው ፍላጐት የተነሣ፣ ፈጥነው በመንፈሳዊ ብስለት ያድጋሉ:: ሌሎች፣ ለረጅም ጊዜ ክርስቲያን ቢሆኑም እንኳን፣ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ባለመስጠታቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አያድጉም:: ስለዚህ አንድ ሰው መሪ ለመሆን የሚያበቃው አንድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ የለም::

መሪዎች ሲመረጡ ጳውሎስ እንድንጠይቅ የሚፈልገው «በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በስለዋል ወይ?» የሚለውን ነው። ካልሆነ፣ አንድ ሰው የቅርብ ጊዜ ክርስቲያንም ይሁን ወይም የረጅም ዓመት ክርስቲያን ሁለቱም ለመሪነት ብቁ አይደሉም። ብዙ ጊዜ ታዋቂ የሆኑ አዳዲስ አማኞች በፍጥነት ሥልጣን ይሰጣቸዋል። ነገር ግን መሪ ለመሆን የሚያበቃ የሥነ ምግባር ባሕርያት ገና ስላልተላበሱ፣ አመራራቸው የሰይጣን መሣሪያ ሊሆንና ወደ ኩራትና ውድቀት ሊመራቸው ይችላል። ሰይጣን ለውድቀት ያበቃውን የትዕቢት ኃጢአት ይፈጽማል። በአመራር ውስጥ የሚከሰተው ትዕቢት አብዛኛውን መንፈሳዊ ብስለት የሌላቸውን እንዲወድቁና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ያደርጋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አማኞች በትዕቢት እንዳይወድቁና የተሰጣቸውን ሥልጣን እንደ ዓለም ሥልጣን እንዳያዩ ክሥር ክሥር ኃላፊነት እየጨመሩ መሄድ አለባቸው።

29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አዲስ አማኝ ወይም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያልበሰለ ሰው መሪ እንዲሆን በመመረጡ በትዕቢት ኃጢአት ሲወድቅ እንዴት እንዳየህ አብራራ። ለ) አሁን ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልበሰሉ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉና ለመሪነት ብቁ እንዲሆኑ ምን ሊያደርጉላቸው ይገባል?

**ኀ. በውጪ ሰዎች ዘንድ መልካም ዝና ያለው፡-** ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን የሚገመግሙት በመሪዎች ሕይወት በሚያዩት ነገር ነው። በዓለማውያን ዕይታ መሪዎች ጥሩ ዝና ካላቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ትከበራለች። መሪዎች በራስ ወዳድነትና በጸብ የሚታወቁ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን አትከብርም። የመሪዎች ዝና የእነርሱን ወይም የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት የሚጐዳ ከሆነ፣ በዲያብሎስ ወጥመድ ውስጥ ወድቀዋል ማለት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ዕድገት የሚገድቡ የማሰናክያ ድንጋዮች ናቸው ማለት ነው።

በአንድ ወቅት የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ደርግ ከወደቀ በኋላ



አንድን የመንግሥት ባለ ሥልጣን ያነጋግራል። ያ ባለ ሥልጣን «በአንድነት ስለ መኖርና እንደ አገር ስለ ማደግ ታላቁን ዘንድ ወደ እናንተ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች እየተመለከትን ነው» ብሎ ተናገረ። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣ ብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርስና በውስጣቸው መጣላት ጀመሩ። በሚቀጥለው ጊዜ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ያንን ባለ ሥልጣን ሲያገኘው ባለ ሥልጣኑ፣ «ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከእኛ የባሳችሁ ናችሁ። እርስ በርሳችሁ በሰላም መኖር የማትችሉ ከሆነ ለምንድን ነው እናንተን የምንሰማው?» ነበር ያለው። በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በአማኞች መንፈሳዊነት ማጣት የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በምድሪቱ ላይ ልታመጣ የሚገባትን ተጽዕኖ ገድቧል።

መሪዎች መሆን የሚገባቸው መንፈሳዊ የሆነ መሪ ምሳሌ ብቻ ሳይሆን፣ የመልካም ዜጋ ምሳሌም ጭምር ነው። የማያምኑ ሰዎች የመሪውን እምነት ወይም አኗኗር ላይቀበሉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ስለ ባሕሪውና ተግባሩ ሊያከብሩት ይገባል። ይህ ማለት ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ሥራ ወይም ከሌሎች አማኞች ጋር በተያያዘ ሥራ ብቻ ሳይሆን በማኅበረሰቡ ውስጥም ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው። ነገር ግን ከማኅበረሰቡ ጋር ሲገናኙ፣ ሽማግሌዎች ከሰዎቹ ጋር ሲወዳጁ እንደማያምኑት እንዳይሆኑ ሊጠነቀቁ ይገባል። ልክ እንደ ኢየሱስ፣ የኃጢአተኞች ወዳጅ ልንሆን ይገባል፣ ነገር ግን በኃጢአታቸው አንተባበርም (ማቴ. 11፡19፤ ዮሐ. 8፡46)። ስለዚህ ሽማግሌዎች ልክ እንደ ዓለማውያን በሥልጣናቸው ክብር ማግኘት የለባቸውም፣ ነገር ግን ለመርሕ በመቆምና መንፈሳዊ ባሕሪ በማሳየት ክብርን ሊያገኙ ይገባል። ዓለማውያን ሳይቀሩ መንፈሳዊ መርሖዎችን የሚከተልና ሰዎችና ማኅበረሰቡን የሚያከብሩ ሰዎችን ያከብራሉ። ለምንድን ነው በየቀበሌውና በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ብዙ አማኞች መሪ እንዲሆኑ የሚመረጡት?

## ከዲያቆናት የሚጠበቅ ተጨማሪ ባሕሪ

ነ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ታማኝና በውሳኔአቸው የሚጸኑ መሆን አለባቸው፡- ምንም እንኳን ይህ ባሕሪ የተጻፈው ለዲያቆናት ቢሆንም፣ ሽማግሌዎችም ይህ ባሕሪ እንዲኖራቸው ይጠበቃል። ለዚህ ባሕሪ የተቀመጠው የግሪክ ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች የማይናገር የሚል ነው። ይህ ሁለት ነገሮችን ማለት ሊሆን ይችላል። አንደኛ፣ አንድ ሰው ለአንድ ሰው ሌላ ለሌላው ደግሞ ሌላ ነገር አይናገርም። የሚወስነውና የሚናገረው ሁልጊዜ አንድ የሆነ ነው። ከተለያዩ ሰዎች ጋር በሆነ ቁጥር አሳቡንና የሚለውን የማይለዋውጥ ነው። ችግሮችን ላለማንሣት ወይም ለመሸፋፈን ሲል በሚያባብሉ ቃላት አይጠቀምም። ማንም ይስማው ማንም፣ የሚናገረው ሁሉ ግልጽና እውነት ነው። ሁለተኛ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወሬ የማያሰራጭ ማለት ሊሆን ይችላል። ሰዎች ወደ ሽማግሌ (ወይም ዲያቆን) ሲመጡና ምሥጢራቸውን ሲያካፍሉ፣ ይህ ሰው ያየውንና የሰማውን ወስዶ ለሌላ ሰው አይናገርም።

> 30ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዝና የማያምኑ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ክብር ሲጨምር እንዴት እንዳየህ አብራራ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጥፎ ዝና የማያምኑ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ክብር ሊያደናቅፍ እንዴት እንዳየህ አብራራ። ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነርሱና ወንጌላቸው ይበልጥ ይከበሩ ዘንድ በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚሳተፉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። መ) መሪዎች ጓደኞቻቸውና ማኅበረሰባቸው የወንጌልን ስርጭት እንዳይገድቡ ሊጠነቀቁባቸው የሚገባቸው ጥቂት አደገኛ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ጳውሎስ ለሽማግሌዎች ያስቀመጣቸው አብዛኛዎቹ መስፈርቶች ለዲያቆናት በተሰጡ መስፈርቶችም ላይ ተጠቅሰዋል። በቲቶ መልእክት በጠቀሳቸው ዝርዝሮች ውስጥ፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለሽምግልና ለመብቃት የሚያስፈልጋቸውን በርካታ ተጨማሪ የግል ባሕርያትን ጨምሯል።



## በቲቶ መልእክት ላይ ስለ መሪዎች መንፈሳዊ ባሕሪ የተጠቀሱ ትምህርቶች

ኘ. በጐ የሆነውን የሚወድድ፡- በመንፈሳዊ ብስለት ስናድግ፣ ባሕሪያችን እግዚአብሔርን እየመሰለ ይሄዳል። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ይወድዳል፣ ግን ክፋን ይጠላል። ጳውሎስ ለቲቶ ሲናገር እነርሱም እንደዚያ መሆን እንዳለባቸው ተናግሯል። ክፋውን በምንም ዓይነት መንገድ መጥላት አለብን። ያ ክፋ በአማኞች መካከል ያለ ግብዝነት፣ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ኢ-ፍትሐዊነት፣ ወይም ማዳላት፣ ወይም ስለ ሴቶች የተሳሳተ አመለካከት፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል። (ማስታወሻ፡- ኃጢአትን መጥላት፣ ኃጢአተኛን ግን መውደድን ልንማር ይገባል።) በሌላ በኩል፣ መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው መሪዎች ምስጋናን የሚፈልጉና መልካም የሆነውን የሚሸልሙ ናቸው። ሕፃናት ልጆች ኢየሱስን መውደድ ሲማሩ ወይም አንድ ሰው በፍቅር የማያምኑትን ሲረዳ ልንደሰት ይገባል። ከመንግሥት የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ሲል አንድ ሰው ጉቦ አልከፍልም ሲል ወይም ሰዎች ዛፎችን ሁሉ ባለመቁረጥ የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሲንከባከቡ ስናይ ደስታ ሊሰማን ይገባል። በሰዎች ላይ ከመማረር ይልቅ፣ የምናመሰግንበትን ጥሩ ነገር ልንፈልግ ይገባል።

አ. ቅዱስ፡- ቅዱስ መሆን ማለት ከዓለምና ከኃጢአት ለእግዚአብሔር ክብር መለየት ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ሰው ከዓለማውያን የተለየ እንደ ሆነ ይረዳል። አኗኗሩ፣ አስተሳሰቡም ሆነ ተግባሩ የተለየ ነው። ሌሎች ቢያደርጉትም እንኳ፣ እግዚአብሔርን በማያስደስት ነገር አይሳተፍም። ባሕሉን መከተል አቁሞ፣ ሕይወቱን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ዓይነት ይለውጣል።

> 31ኛ ጥያቄ፡- ያለፉትን ሁለት ቀናት ትምህርቶች ከልስ። ሀ) ከእነዚህ ባሕሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

የሚለማመዷቸው ባሕሪዎች የትኞቹ ይመስሉሃል? ለ) የትኞቹ ባሕሪዎች ይመስሉሃል አብዛኞዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚፈታተኗቸው? ከዚያ ባሕሪ ጋር የሚታገሉት ለምን ይመስልሃል? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሽማግሌዎች ምርጫን በበላይነት ተቆጣጠር ብትባል፣ አባላት እንደ ትምህርት ደረጃና በሕዝብ ፊት የመናገር ችሎታ ባሉ ነገሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ በእነዚህ ባሕሪዎች ላይ እንዲያተኩሩ ምን ታደርጋለህ?

*ማጠቃለያ፡-* መንፈሳዊ አመራር ባሕሪን መሠረት ያደረገ ነው። ስለዚህም ጳውሎስ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመምራት መንፈሳዊ መስፈርቶችን ማሟላት እንደ አለባቸው። አጽንኦት ሰጥቷል። በሚቀጥለው ሳምንት ለመንፈሳዊ አመራር መሠረት የሆኑ ሌሎች ባሕሪዎችን እናጠናለን። ከዚህ በታች መንፈሳዊ መስፈርቶችን ለማቀናጀት ሌላ መንገድ ታገኛለህ። በጥንቃቄ አንብባቸው። እነዚህን መስፈርቶች ታሟላለህ? ካላሟላህ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን የመንከባከቡን ኃላፊነት ሲሰጥህ እንዲችል በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ሰው ለመሆን ምን ማድረግ ያስፈልግሃል?

**ሀ. በመንፈሳዊ ሕይወት ብቁ የሆኑ ሰዎች ልምድ ያላቸው ናቸው።** እነዚህ ሰዎች ያላቸው ከትምህርት ቤት የተመረቁበት ወረቀት ብቻ አይደለም። ይልቁንም፣ በሚከተሉት የሕይወት ክፍሎች ልምዶችን አዳብረዋል፡-

**1. በዘመናት ሁሉ በእግዚአብሔር ይታመናሉ።** በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ራሳቸውን ለክርስቶስ ሲሰጡ ታይተዋል።

**2. ከሰዎች ጋር ምርጥ ግንኙነት አላቸው።** መንፈሳዊ ሰው የራሱን ድካምና ብርታት ያውቃል። የሚያገለግሉትን ሕዝብ ያውቃሉ። እንደ መሪ ሰዎችን የማገልገል ፍላጐት ያሳያሉ፣ ሰዎችም ወደ እነርሱ በመምጣት ምላሽ ይሰጣሉ። ሌሎች ደግሞ



ኢየሱስን መከተልን በተመለከተ እንደ ጥሩ ምሳሌ ያዩዋቸዋል።

**3. በሰይጣን ላይ ቋሚ ድል አላቸው።** እነዚህ አማኞች ቅዱስ የሆነ ሕይወት አላቸው። ሰይጣን የሚያመጣባቸውን ልዩ ልዩ ፈተናዎች ይቋቋማሉ።

**4. የእግዚአብሔርን ቃል ያውቃሉ።** እውነትን ብቻ ማወቅ ሳይሆን፣ በሕይወታቸው ውስጥ እንዴት ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያውቁና በመታዘዝ የሚኖሩ ናቸው። በተጨማሪም የሚያውቁትን ነገር በቤተ ክርስቲያን ይሁን፣ በሰንበት ትምህርት ቤት ይሁን ወይም በሚያማክሩበት ጊዜ በንቃት ያስተላልፋሉ።

**ለ. መንፈሳዊ መስፈርትን የሚያሟላ መሪ በቤተሰቡ ውስጥ መሪነቱ ይታያል።** ሽማግሌ ከሚስቱ ጋር ያለው የጠለቀ ግንኙነት ያለምንም ጥርጥር መሪ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት እንደሚያሳድገው የሚያሳይ ነጸብራቅ ነው። በትዳራቸው ውስጥ ንጹሕ ለመሆን የገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅ መቻሉ ለቤተ ክርስቲያንም ምን ያህል ታማኝ እንደሚሆን ያሳያል። ለእርሷ የገባውን ቃል ኪዳንም ብዙውን ጊዜ የሚጠብቅ ከሆነ፣ ለቤተ ክርስቲያን አባላት የገባውን ቃል ኪዳንም ይጠብቃል። ሽማግሌ ሰዎች ከኢየሱስ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የማድረጉ እውነት የሚገለጠው ልጆቹ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በተቀበሉበት መንገድ ነው። ልጆች አብዛኛውን ጊዜ የሚያምኑት የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ከመማር ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ የተነቃቃ ግንኙነትን በማየት ስለሆነ፣ የልጆች እምነት ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የቅርብ ግንኙነት ያንጸባርቃል።

**ሐ. መንፈሳዊ መስፈርትን የሚያሟሉ መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ጥሩ ግንኙነት ይታወቃሉ።** ከሁሉ ነገር በላይ እግዚአብሔርን ይወድዳሉ። የእግዚአብሔር ቃል

ጥናታቸው፣ ጸሎታቸውና አገልግሎታቸው ይህን ፍቅር ያንጸባርቃል።

**መ. መንፈሳዊ መስፈርትን ያሟሉ ሽማግሌዎች በርኅሩኅነታቸው ይታወቃሉ።** ለሰዎች ፍላጐቶች ያዝናሉ፣ ሰዎች ሲቸገሩ ሲያዩዋቸው፣ ይረዷቸዋል። ይህ በተለይ የሚታየው በመንፈሳዊ ሕይወት ለጠፉና ወደ ገሃነም በሚሄዱት ላይ ነው።

**ሠ. መንፈሳዊ መስፈርትን ያሟሉ ሽማግሌዎች በሳል ባሕሪን አዳብረዋል።**

1\. ምንም እንኳን ፍጹም ባይሆኑም፣ ሕይወታቸውን በቋሚነት የሚመሩት በመጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ እናም ቅኖች ከመሆናቸው የተነሣ በብዙ ሰዎች ዘንድ ይከበራሉ።

**2. ራስን መቆጣጠር ተምረዋል።** ሰው የመሆንን (የሰውነታቸውን) ጨለማ ክፍል፤ ቁጣቸውን፣ እንደበታቸውን፣ ለገንዘብና ክብር ያላቸውን ፍቅር፣ ወዘተ. . . መቆጣጠርን ተምረዋል። ያሟቸውን ወይም በአሳብ ያልተስማሟቸውን ሰዎች አይበቀሉም። የሥራ ጉዳይን በተመሰከተም ያስ ነቀፋ በመሆናቸው፣ በሚዛናዊነታቸውና በታማኝነታቸው ይታወቃሉ። ፈቃዳቸውንም መቆጣጠር ተምረዋል። ያለ በቂ አሳብ የሚፈልጉትን ከማድረግ ይልቅ፣ ሕይወታቸውንና ጊዜአቸውን በመርሖዎች ይመራሉ። ሥርዓትን የጠበቀ የጸሎትና የቃል ጥናት ሕይወት አላቸው።

**3. ደፋሮች** ናቸው። ሰዎችን ወይም የመገለልን ሥቃይ አይፈሩም። ልክ እንደ ፖለቲከኞች ሰዎች በሚፈልጉት መንገድ ውሳኔአቸውን አይለውጡም። ይልቁንም፣ ሌሎች ባይሰማሙ እንኳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ኑሮን ይመራሉ።

4\. እግዚአብሔር ከእነርሱና ከሌሎች ስለሚፈልገው ነገር ራእይ አላቸው። እናም የእግዚአብሔርን ራእይ ቀስ በቀስ



ለመፈጸም መስጠቱ አላቸው። ዝም ብለው ያለፈውን ብቻ አይከተሉም። ነገር ግን «እግዚአብሔር አሁን ከእኛ የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው?» ብለው ይጠይቃሉ።

**5. ግትሮች አይደሉም።** ጊዜና ሁኔታ ሁልጊዜም ስለሚለወጥ፣ ከሚለወጠው ጊዜ ጋር ራሳቸውን ያስተካክላሉ። ነገር ግን አዲስ የሆነውን በሙሉ አይቀበሉም፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ መሆን አለመሆኑን ይገመግማሉ።

**6. የሌሎች ሰዎችን አሳብ ያዳምጣሉ።** እውቀቱን በሙሉ እውቀው እንደ ጨረሱ አያስቡም። ሌሎችን ለሙ ማለት እነርሱ ጥሩ ያልሆኑ መሪዎች ናቸው ማለት ነው ብለው አይፈሩም። አማኞች ሁሉ በልባቸው መንፈሰ ቅዱስ እንዳለና ከዚያ የተነሣ መንፈስ ቅዱስ መልካም ምክር እንደሚሰጣቸው ይገነዘባሉ።

**7. ከሌሎች የሚመጣን ትችት ለመቀበል ይችላሉ።** ሰዎችን ሁሉ ማስደሰት የማይቻል በመሆኑ፣ መሪዎች ሁልጊዜ ይተቻሉ። ስለዚህ ሽማግሌዎች ሲተቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ትችትን ሊፈሩት አይገባም። ሊቆጡም አይገባም። ይልቁንም፣ እያንዳንዱን ትችት በጥንቃቄ መስማት አለባቸው። ራሳቸውንም፣ «ከዚህ ትችት ውስጥ የትኛው ነው ልለውጠው የሚገባው እውነት»? እንዲሁም፣ «የትኛው ነው እውነት ያልሆነውና ልጨነቅበት የማይገባው» ብለው ይጠይቃሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ሰዎች ጌታቸው እንዳልሆኑ፣ የሚገመገሙትም በእርሱ እንጂ በእነርሱ እንዳልሆነ ያውቃሉ። ነገር ግን መሆን የሚችሉትን ያህል ጥሩ ለመሆን ስለሚፈልጉ፣ ሁልጊዜ ሰዎች የሚሉትን ይሰማሉ።

**ረ. መንፈሳዊ መስፈርትን የሚያሟሉ መሪዎች ሽማግሌ ሆነው እግዚአብሔርን ለማገልገል ፈቃደኛ ናቸው።** ሽማግሌ እንዲሆኑ በሰዎች አይገፋፉም። ሽማግሌ እግዚአብሔር ሕዝቡን በእረኝነት እንዲመራ እንደ ጠየቀው ያውቃል። ሌሎች አማኞች

በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው እንዲያድጉ ጊዜውን፣ ገንዘቡን፣ መንፈሳዊ ጸጋውንና የመሳሰሉትን በነፃ ይሰጣል::

| |
|---|
| 32ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንተ የትኞቹን መመዘኛዎች ታሟላለህ? ለ) በየትኞቹ መስፈርቶች ነው ደካማ የሆንከው? ሐ) እግዚአብሔር ሕዝቡን የማገልገልን አደራ ይሰጥህ ዘንድ በመንፈሳዊ ሕይወትህ በሳል ለመሆን ምን ማድረግ አለብህ? |

## አራተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ

# ሳምንታዊ ስብሰባ

## የመወያያ ጥያቄዎች:-

*1. ሀ) ምን ያህል ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ጥናት እንደማያከብሩ ግለጽ:: የእግዚአብሔርን ቃል ከማጥናት ይልቅ ምን ዓይነት ነገሮችን ይመርጣሉ? ይህ በመንፈሳዊ ብስለታቸው ስላለው መመጣጠን ምን ያሳያል? ለ) ምን ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መምራት እንደሚፈልጉ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ስማንበብ ምንም ጥናት እንደማያደርጉ አብራራ:: ሐ) ስምንድን ነው አብዛኛዎቹ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል በቁም ነገር የማያጠኑት? መ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል እንዲጠናና የእግዚአብሔር ቃል ተፈጻሚ እንዲሆን ምን ሊሰወጥ የሚገባ ይመስልሃል? ሠ) ከላይ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓይነቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች የማያደርጓቸው የትኞቹ ናቸው?*

*2. ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች ሲመረጡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እንደሚችሉ ታሳቢ በማድረግ ነው? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ካለማወቃቸው የተነሣ ለአማኞች ትክክለኛ ያልሆነ ትምህርት ሲሰጡ እንዴት እንዳየህ ግለጥ? ሐ) ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መሄድ የማይችሉ ሽማግሌዎች ማስተማር ይችሉ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል እውቀታቸው ስማደግ የሚችሉባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው? መ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የሚገኙ ሽማግሌዎች ሁለቱን በእግዚአብሔር የተሰጡ የማስተማርና ምሳሌ የመሆን መሣሪያዎች በምን ያህል መጠን ይጠቀማሉ? እንዴት አድርገው ነው እነዚህን መሣሪያዎች በተሻለ መንገድ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉት? ሠ) መጽሐፍ ቅዱስ የማያተኩርባቸው ነገር ግን እነርሱ የሚጠቀሙባቸው ምን ዓይነት ሌሎች የመሪነት መሣሪያዎች አሉ? ረ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አንድ ሰው ሽማግሌ፣ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ስመሆን ስለሚያስፈልገው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ያወጣቸውን መመሪያ ማውጣት ይኖርበት ወይም አይኖርበት እንደ ሆነ ተወያዩበት::*

*3. የአብዛኛዎቹ ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና የወንጌላውያን ቤተሰቦች በመልካም ሥነ ምግባርና በመንፈሳዊነት መልካም ዝና ያላቸው ናቸው? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) ጳውሎስ ሽማግሌ እግዚአብሔርን የሚወድና የሚታዘዝ ቤተሰብ ሊኖረው ይገባል ያለው ለምንድን ነበር? ሐ) እንደ አባት በቤት ውስጥ መንፈሳዊ መሪ እንደ መሆኑ መጠን ልጆቹ በእግዚአብሔር እንዲያምኑ፣ እንዲወድዱትና እንዲታዘዙት ለማበረታታት ምን ምን ማድረግ እንዳለበት ዘርዝር:: መ) ኢየሱስ ማንም ሰው ባልና ሚስትን ማፈታት እንደሌለበት ተናግሯል (ማቴ. 19:4-6፤ 1ኛ ቆሮ. 7:1-6):: ይህ ጥቅስ ከሚስቶቻቸው ተለይተው በሚኖሩ ወንጌላውያን ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የሚሠራ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ:: ሠ) ሚስትና ልጆች የአባታቸውን አገልግሎት መደገፋቸው በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?*

*4. ያለፉትን ሁለት ቀናት ትምህርቶች ከልስ:: ሀ) ከእነዚህ ባሕሪዎች ውስጥ በኢትዮጵያ ያሉ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚስማሙዱት የትኛውን ነው? ለ) ከእነዚህ ባሕሪዎች*

ውስጥ አብዛኛዎቹን መሪዎች የሚፈታተነው የትኛው ይመስልሃል? ከዚያ ባሕሪ ጋር ለምን የሚታገሉ ይመስልሃል? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የሚደረግ የሽማግሌ ምርጫን ለመቆጣጠር ዕድል ቢሰጥህ፣ ሰዎች እንደ ትምህርት ደረጃና በሕዝብ ፊት የመናገር ችሎታ ካሉ ነገሮች ይልቅ በባሕሪ ላይ እንዲያተኩሩ ምን ታደርጋለህ?

# ትምህርት አራት

**የመጀመሪያ ቀን፡-** ለመንፈሳዊ አመራር የሚያስፈልጉ ቁልፍ ባሕርያት (ክፍል 3)

«ኑሮ ከጌታ ከኢየሱስ ጋራ፣ በሸለቆ ቢሆን በተራራ፣ አመቺ ነው፣ ደስ ያሰኛል፣ እርካታን ይሰጣል።» የሚለውን መዝሙር ድሮ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እዘምረው ነበር።

| |
|---|
| *1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ መዝሙር እውነት ነው ወይስ ሐሰት? መልስህን አብራራ። ለ) 2ኛ ቆሮ. 11:23-29ን አንብብ። ጳውሎስ ወንጌልን በመላው ዓለም ሲሰብክ የደረሰበትን መከራ ዘርዝር። በጣም የከፋውን ሽክምና መከራ ያመጣበት ምንድን ነበር? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ መሆን አገልግሎት ሲታሰብ ጳውሎስ ስለ ደረሰበት መከራ የገለጠውን ነገር አሁን በሽማግሌዎች ላይ ከሚደርሰው ነገር ጋር ምን ያመሳስለዋል?* |

በብዙ መንገዶች ስናይ ኢየሱስን መከተል ይመቻል። ደቀ መዝሙር መሆን ብዙውን ጊዜ ደስታና የውስጥ እርካታ ይሰጣል። ነገር ግን ይህንን አባባል እንዴት እንደምንረዳው መጠንቀቅ አለብን። ከሰዎች አንጻር ስንመለከተው፣ ይህ መዝሙር በምድራችን ላይ እውነታ የለውም። ኢየሱስን መከተል አብዛኛውን ጊዜ ስደትን ያመጣል (2ኛ ጢሞ. 3:12)። ለዚያ ነው ኢየሱስ ሊከተሉት ለፈለጉት ሰዎች መስቀላቸውን ተሸክመው እንዲከተሉት የነገራቸው (ሉቃ. 9:23)። በምድር ባለው ሕይወታችን ችግሮች፣ ጉስቁልና፣



ረሃብ፣ ሥራ ማጣት፣ በሽታና በመጨረሻም ሞት ያጋጥመናል። ኢየሱስ በምድር እስካላችሁ መከራ አለባችሁ ብሏል (ዮሐ. 16:33)።

ይህ በተለይ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እውነት ነው። እንዲያውም የቤተ ክርስቲያን መሪነት በሰውየው ላይ ብዙ ችግር ያመጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ታላላቅ መሪዎች በሙሉ ይመሩ የነበሩት እየጨመረ በሚሄድ መከራ ውስጥ ነበር። ሙሴ የራሱ ሕዝብ ያነሣ የነበረውን የማያቋርጥ ተቃውሞ ታግሦ ነበር የመራው። ሌላው ቀርቶ የገዛ ወንድሙና እኅቱም እንኳን ሳይቀር በእርሱ ላይ ተነሥተውበታል (ዘኁል. 12:1-9)። ዳዊትም የሳያልን ተግዳሮትና የልጁን የአቤሴሎምን ዐመፅ ተቋቁሟል። ኤርምያስም የጌታን መልእክት በሚያስተላልፍላቸው ሰዎች መከራ ደርሶበታል (ኤር. 37:15)። ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ውስጥ ሁሉም እስርና ሞት ደርሶባቸዋል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሆን ሰው መንገዱ ቀላል እንደሚሆንለት ወይም አስደሳችና እርኪ ነገር መጠበቅ የለበትም። የቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚያመጣውና ሌሎች አባላት የማይሸከሙት መስቀል አለ። እርካታችን የሚመነጨው ሥራው ለእርሱ እንዲሠራለት የጠየቀውን እግዚአብሔርን በማስደሰትና በመታዘዝ ነው። ደስታ የሚመጣው ለእኛ ባይመችን እንኳን እርሱን በማስደስትና በመታዘዝ ነው። ደስታችን የሚፈጸመው አንድ ቀን ስንሞት ኢየሱስ መልካም አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ» (ማቴ. 25:21) ሲለን ነው።

እግዚአብሔርን በቤተ ክርስቲያን መሪነት ለማገልገል በመጀመሪያ ባሕሪያችንንና መንፈሳዊ ብስለታችንን ልናሳድግ ይገባል። ባለፈው ሳምንት ጳውሎስ እንደ ሽማግሌና ዲያቆን ለማገልገል ከአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ያስፈልጋሉ ያላቸውን ባሕሪዎች አጥንተናል። በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታትም አንድ መሪ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲመራ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ባሕርያትን እንመለከታለን። እኛ መሪዎችን በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ መምራት የሚያስችሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ባሕሪዎች አሉ:: በእርግጥ እነዚህን በሙሉ የሚያሟላ አንድም መሪ የለም:: ሆኖም፣ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ባሕሪዎች የተዘረዘሩት ሁሉም መሪዎች እያሳደጓቸው እንዲሄዱ ለማድረግ ነው:: አንዳንዶቹ ባሕሪዎች ከሌሎቹ ይልቅ በጣም አስፈላጊ ናቸው:: ነገር ግን እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ በኃይል እንዲጠቀምብን ከፈለግን ሁሉም አስፈላጊዎች ናቸው:: እንዳስመታደል ሆኖ፣ እያንዳንዱን ባሕሪ በበቂ ሁኔታ መግለጥ አንችልም:: ይሁን እንጂ፣ የምንዘረዝራቸው አመራራችንን ይበልጥ ፍሬያማ ለማድረግ ስለ እነዚህ ባሕሪዎች ማሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: እነዚህን ባሕሪዎች ስታጠና «እኔ እንደዚህ ነኝ?» ወይም «በዚህ የሕይወቴ አቅጣጫ ማደግ አለብኝን?» ብለህ ራስህን ጠይቅ::

በሚቀጥሉት ሁለት ትምህርቶች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ውጤታማ መሪዎች የሚያደርጉ ባሕሪዎችን እንቃኛለን:: እነዚህን ባሕርያት በአራት ምድቦች ከፍለናቸዋል:: <u>የመጀመሪያው</u> ምድብ የሚያያቸው ባሕሪዎች ግለሰባዊ መሪነት ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ግንኙነት ጋር በተያያዘ ነው:: <u>ሁለተኛው</u> ምድብ አመራራችንን በሚያሳድጉ የግል ባሕርያት ላይ ያተኩራል:: <u>ሦስተኛው</u> ምድብ ደግሞ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ባሕርያት ናቸው:: <u>በመጨረሻም</u> እንደ መሪ ልንሠራ በምንችለው ነገር ላይ ተጽዕኖ የሚያመጡ ባሕሪዎችን እንመለከታለን::

ስኬታማ ለሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ባሕርያት:- መሪው ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ግንኙነት የሚመነጩ ባሕርያት (ክፍል 1)

1. **እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደ ጠራን በማወቅ ማገልገል::**



| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ:- ኢሳ. 6፤ ሕዝ. 2:1-8፤ የሐዋ. ሥራ 9:1-19ን አንብቡ:: ሀ) የእነዚህን መሪዎች የአገልግሎት ጥሪ ግለጥ:: ለ) በአገልግሎታቸው መከራ እንደሚገጥማቸው የሚያሳይ እግዚአብሔር የሰጣቸው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? ሐ) የሐዋ. ሥራ 20:28ን አንብቡ:: ጳውሎስ ሽማግሌዎች መሪ እንዲሆኑ ምረጡ ያለው ማንን ነው? |

«ወንጌላዊ እንድሆን ጥሪ አለኝ» የሚለውን ነገር ብዙ ጊዜ እንሰማለን:: ግን እንደዚህ ለንል ምን ማለታችን ነው? <u>«ከእግዚአብሔር የመጣ ጥሪ ማት በአንድ የተለየ መንገድ እግዚአብሔርን እናገለግል ዘንድ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ በልባችን ውስጥ በጥልቀት የሚሰማን ነገር ነው::</u> ሁለት ዓይነት ጥሪዎች አሉ:: ለሁሉም አማኞች የትም ይሥሩ የትም በጋራ የተሰጣቸው ጥሪ አለ:: እናም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ በተለየ ሁኔታ ለሚለያቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጥሪ አለ::

ሀ. ሁሉም አማኞች የሥራ ቦታቸውን እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣቸው አድርገው ማየት አለባቸው:: በአንድ መልኩ፣ ሁሉም አማኝ ባለበት ሆኖ እግዚአብሔርን ለማገልገል «ተጠርቷል»:: ሥራችን ምንም ይሁን ምን፣ በቅድስና ልንኖርና በአካባቢያችን ያሉትን ልንወድ ተጠርተናል:: አማኙ በሆስፒታል የሚሠራ ዶክተር ከሆነ፣ እግዚአብሔር ያንን ሰው የሰዎችን አካላዊ ፍላጐት ለማሟላት ኢየሱስን ወክሎ እንዲደርሳቸው ጠርቶታል:: በሆስፒታል ውስጥ የመሥራቱ ዓላማ እግዚአብሔርን ማገልገልና ሌሎችን በመርዳት በጣም ጥሩ ዶክተር በመሆን እርሱን ማክበር መሆን አለበት:: የሚሠራው ነገር ኢየሱስ በዚያ ሆስፒታል ቢገኝ በሽተኞችን ለመርዳት ሲሠራው የሚችለው መሆን አለበት:: እግዚአብሔር አንድን ሰው 'ገበሬ' ወይም 'ነጋዴ' እንዲሆን ከጠራው፣ ያ ሰው ለእግዚአብሔር ክብር ሲል በጣም ምርጥ ገበሬ ወይም ነጋዴ መሆን ይፈልጋል::

ለ. ነገር ግን አንድን ሰው ሰዎች ከሚሠሯቸው መደበኛ

ዓይነት ሥራዎች ለይቶ ራሱን ለሙሉ ጊዜ ወይም ለትርፍ ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲፈልግ፣ ያንን ሰው በአንድ በተለየ መንገድ እንዲያገለግለው እንደሚጠይቀው መጽሐፍ ቅዱስ ያሳየናል። ይህ በተለምዶ የአገልግሎት «ጥሪ» ይባላል (ለምሳሌ፣ በወንጌላዊነት፣ በመጋቢነት፣ በልማት ሠራተኛነት፣ በሚሲዮናዊነት) ወይም በአመራር (ለምሳሌ፡- በሽምግልና)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለአገልግሎትና ለመሪነት ለሚሰጠው ጥሪ የሚከተሉትን እንማራለን፡-

1) <u>እግዚአብሔር መሪዎችን ይመርጣል</u> (የሐዋ. ሥራ 20:28) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያስታውሱ ከሚገባቸው እጅግ አስፈላጊ እውነቶች አንዱ፣ መሪ እንድንሆን የተመረጥነው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ያለመሆኑን ነው። አዎን፣ ሰዎች በድምጽ ብልጫ መሪ አድርገውን ይሆናል። ነገር ግን፣ ምርጫቸው በልዑል እግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው። ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲናገር፣ መሪ እንዲሆኑ የተመረጡት መንፈስ ቅዱስ ለመሪነት ስለ ሾማቸው እንደ ሆነ ይናገራል። ዳንኤል 4:25 መሪዎች ሁሉ በእግዚአብሔር እንደ ተመረጡ ያስታውሰናል። እግዚአብሔር የአገር መሪዎችን ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንም ይቆጣጠራል። መሪን ወደ ላይ የሚያወጣውም የሚያወርደውም እርሱ ነው (መዝ. 75:6-7)።

እኛን በመሪነት የማንሣትና የማውረድ ኃላፊነት የእግዚአብሔር የመሆኑን እውነት መረዳት ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚከተሉትን አስፈላጊ እውነታዎች እንድንረዳ ያደርገናል፡-

ሀ) <u>እኛ ሳንመረጥ ሌሎች በመሪነት ሲመረጡ ልንቀና አይገባም</u>። እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ እንደሚቆጣጠርና የተወሰኑ ሰዎችን በአገልግሎት የማስነሣትን ሥራ እንደሚሠራ በመረዳት እግዚአብሔር የፈለገውን ሰው የመምረጥና የማስነሣትን ሥራ እንዲሠራ ልንፈቅድ ይገባል። ሰውየው ከየትኛውም ብሔረሰብ ይምጣ፣ ከየትኛውም ቤተሰብ



ይምጣ፣ ወይም ምንም ዓይነት የትምህርት ደረጃ ይኑረው ችግር አይፈጥርም። ኢየሱስ በእውነት የቤተ ክርስቲያን ጌታና ሁሉን የሚቆጣጠር ከሆነ፣ በእርሱ ምርጫ እምነት ሊኖረን ይገባል። በዚህ ጊዜ ስላልመረጠን ልንናደድ አይገባም። በልባችን የሚታይ ማንኛውም የቅናት ምልክት የሚያሳየው በንጹሕ ልቡና ለማገልገል ያለመፈለጋችንን ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን አመራርን እንደሚቆጣጠር አለማመናችንንም ያሳያል።

ለ) <u>ጓደኞቻችንን ወይም የምናምናቸውን ሰዎች ሥልጣን እንዲያገኙ የማድረግ ምንም መብት የለንም።</u> አንዳንድ ጊዜ ሽማግሌዎች ማን መሪ መሆን እንዳለበት በደንብ የሚያውቁ ይመስላቸዋል። ብዙ ጊዜ ይህ የሚሆነው ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው አብረዋቸው መሪ እንዲሆኑ ስለሚፈልጉ ነው። በሌላ ጊዜ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባላት ትክክለኛውን ሰው ይመርጣሉ ብለው አያምኗቸውም። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አመራረጥ ለማምታታት በሽማግሌዎች የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ የሚያሳየው ተገቢውን ሰው በመምረጡ ረገድ እግዚአብሔርን እንደማያምኑት ነው። ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን መሪ ለመምረጥ እግዚአብሔር በአማኙ ሕዝብ ላይ ይንቀሳቀሳል ብለው አያምኑም። እንደ ሽማግሌነታችን፣ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሰዎችን ወደ አመራር ማምጣት እንደሚፈልግ ለሕዝቡ የማስተማር ኃላፊነት አለብን። ለአንድ መንፈሳዊ መሪ የሚያስፈልጉ ባሕርያትን ለሕዝቡ መናገር ኃላፊነታችን ነው። ግን ከዚያ በኋላ በጉዳዩ ላይ ሰዎች እንዲጸልዩበትና ምርጥ ነው ብለው የሚያስቡትን እንዲመርጡ በመፍቀድ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መታመን እናሳያለን። እኛ ጥሩ ነው ብለን ያሰብነውን ሰው ባይመርጡም እንኳን፣ እግዚአብሔር ነገሩን እንደሚቆጣጠር በማመን ምርጫቸውን እንቀበላለን።